በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን

# ሃይማኖትና ሥነ - ምግባር መማሪያ




## ለጀማሪ ሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች

አዘጋጅ፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

፲፱፻፺፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን

# የመጽሐፍ ቅዱስና የሥነ ምግባር ማስተማሪያ ሥርዓተ ትምህርት

## ለጀማሪ ሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች

አዘጋጅ፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ነሐሴ 1999 ዓ. ም.

©ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

1999 ዓ. ም.

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

ALL RIGHTS RESERVED

አድራሻ ፡-

ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ፖ. ሣ. ላ 43200

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

ስልክ +251-911-236767

E-mail:-Kesisolomon@gmail.com

Web Site: http://www.zeorthodox.org

በኢ/ኦ/ተ ቤ/ክ የመጽሐፍ ቅዱስና የሥነ ምግባር

ማስተማሪያ ሥርዓተ ትምህርት ለመዓለ ሕፃናት ተማሪዎች

አንደኛ እትም ነሐሴ 1999 ዓ.ም.

ሁለተኛ እትም ጥቅምት 2007 ዓ.ም

# ምስጋና

ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት በምንማበት ወቅት ሐሳቦችን እና ምንጮችን በማሰባሰብ፣ ለትምህርቱ ተስማሚ የሆኑና በቀለም የሚቀቡ ሥዕሎችን በማዘጋጀት ለተራዳችሁኝ፣ ለኅትመት የሚያስፈልገውን ወጪ በመሸፈን ለሥራው መሳካት ከፍተኛ እገዛ ላደረጋችሁ አቶ ሳሙኤል ተክላይ እና ብሥራተ ገብርኤልን እንዲሁም ስማችሁን በዝርዝር ባልጠቅስም ይህ ሥራ የተሳካ እንዲሆን በነገር ሁሉ ያበረታችሁኝን የወላጆች ኮሚቴ አባላት በሙሉ ዋጋን የሚከፍል እግዚአብሔር እንደ ፈቃዱ የእናንተንም ሐሳብና ፈቃድ ይፈጽምላችሁ እያልኩ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በዚሁ አጋጣሚ የእረፍት ጊዜያቸውን ሳይቀር በመሠዋት ረቂቁን በማረም ገንቢ አስተያየታቸውን የሠጡኝን አባቶቼንና ወንድሞቼን በእግዚአብሔር ስም ከልብ አመሰግናለሁ።

# ማሳሰቢያ

ከዚህ መጽሐፍ ሥርጭት የሚገኘው ገቢ በአጠቃላይ በአሁኑ ጊዜ በቦሌ ደብረ ሳሌም መጥምቁ ዮሐንስ መድኃኔዓለምና አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን ለሚካሄደው ለልጆች ጉባኤ ማጠናከሪያና ወደፊትም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በዚሁ ጉባኤ አማይነት ለሚያከናወኑት በርካታ መንፈሳዊ ተግባራት ብቻ የሚውል ይሆናል።

በተጨማሪም ይኸን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ዋና ምንጭ የሆኑኝ በግብፅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን Sunday School Curriculum - Kindergarten በሚል የተዘጋጀ ማስተማሪያ፣ በቤተክርስቲያናችን የሚገኙ መጻሕፍት፣ በተለያዩ ጊዜያት ለታላላቅ በዓላት የተዘጋጁ አጫጭር ጽሑፎችና ከቤተክርስቲያን ያገኘኋቸው ትምህርቶች ናቸው።

# መታሰቢያነቱ

በምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት በአምቦ መሠረተ ሕይወት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን የክርስትና ቤት ውስጥ ባለች መጠመቂያ አጠገብ እያሳደሩ በመንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት ለቀረጹኝ፣ እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ በነገር ሁሉ ፈጣሪን ማክበርንና ከጥቃቅኖቹ ነገሮች አንስቶ በቅዱሳት አማላጅነት መጠቀምን እንደ ታላቅ ቅርስ በውስጤ ትተው ላለፉ፣ በዕለቱ የነበረውን አገልግሎታቸውን በሙሉ ፈጽመው በዚያው በቤተ መቅደስ ውስጥ በክብር በማረፍ የጻድቅ ሰው ሞቱ ክቡር መሆኑን እግዚአብሔር በዚህ ክፍለ ዘመን ለመሰከረላቸው፣ እስከ ዛሬም ድረስ በቤክርስቲያን ላለኝና ለማኖረኝ ሕይወቴ ሁሉ እያስቀደምኩ ለምከተላቸውና፣ ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ብቻ መቀበልን በሕይወታቸው ላስተማሩኝ ለአባ የሺጥላ ዕርገተ ቃል ይሁንልኝ።

# መቅድም

በአሁኑ ወቅት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ልጆች ቤተክርስቲያናቸውን እያወቁ በመልካም ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚያደርግና ችግሮቻቸውን የሚፈታ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት አስፈላጊነቱ በብዙዎቻችን ዘንድ ይታመንበታል። ቤተክርስቲያንም በዚሁ ዙሪያ በርካታ ተግባራትን እንደምታከናውን እምነቱ ነው። ሁሉም ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ቤተክርስቲያን በመላክ ለተስተካከለ ዕድገታቸው አስተዋጽኦ ለማድረግ ፍላጎቱ ቢኖራቸውም በአንዳንድ ሁኔታዎች አለመመቻቸት የተነሣም ይሁን በሌላ ምክንያት በተግባር ልጆቻቸውን ይዘው ወደ ቤተክርስቲያን የሚያቀርቡ ምዕመናን እጅግ ጥቂቶች  መሆናቸውን ለሥራ የምውልበት ቤተ ሰቦች ታላቅ ማሳያዎቹ ሆነውኛል።

ከአንድ ዓመት በፊት በእግዚአብሔር ፈቃድ በምሠራበት መሥሪያ ቤት በኩል ለተዘጋጀ ሞያዊ ሥልጠና ከአገር ውጪ ባደረግሁት ጉዞ ዘወትር አብረውኝ የሚቆሙ ቤተሰቦቼ ምክንያት ሆነው ግብጽንና ገዳማቱን የመጎብኘት ዕድል አገኘሁ። ይህም የተቀደሰ አጋጣሚ ዘወትር ስለ ልጆች፣ ቅድመ ጋብቻ ስላሉ ወጣቶችና በትዳር ስለሚኖሩ ኦርቶዶክሳዊያን የተናጠል መርሐ ግብር እንዳስብ አደረገኝ። በእግዚአብሔር ፈቃድም በቦሌ ደብረ ሳሌም መጥምቁ ዮሐንስ መድኃኔዓለምና አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን በብፁዕ አቡነ ሳሙኤልና በቤተክርስቲያኒቱ አስተዳደር ጽ/ቤት መልካም ፈቃድ የልጆች መርሐ ግብሩ በኅዳር ወር 1999 ዓ. ም. በ 24 ልጆች ተጀመረ። አሁን በየሳምንቱ ቅዳሜ ከ 4 -6 ሰዓት ከ መዋለ ሕፃናት እስከ 10 ኛ ክፍል የሆኑ ከ 300 በላይ ልጆች የመርሐ ግብሩ ተሳታፊዎች ናቸው። ይሁን እንጂ ሁሉንም ልጆች በየትምህርት ደረጃቸው በመመደብ ማስተማር የሚያስችል ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀቱ አስፈላጊ በመሆኑ ለጊዜው መነሻ የሚሆኑኝን  የተለያዩ ጽሑፎችን ማገላበጥ ጀመርኩና በመጨረሻ ከመዋለ ሕፃናት እስከ አምስተኛ ክፍል የሚገኙ ወጣቶችን ማስተማር የሚያስችል ጥራዝ ለማሰባሰብ እድል ገጠመኝ። ቀጥሎም ለማሳተም የሚያስፈልጉ ወጪዎችንና ተጨማሪ ቁሳቁሶች በማሟላቱ ሂደት የወላጆች እገዛ ታክሎበት አሁን የመዋለ ሕፃናት ተማሪዎችን ማስተማሪያ ሥርዓተ ትምህርት ለማሳተም የሚያስችል ደረጃ ላይ ደረስኩ።

ለዚህ ዝግጅት የኑሮና የትምህርት ደረጃ፣ የመረጃ ምንጮች፣ የመኖሪያ ሥፍራዎችና የባሕል ልዩነቶች እንዲሁም በምዕራብ አገሮች እና በአገር ውስጥ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መካከል ያሉ ልዩነቶች ከግንዛቤ ውስጥ ገብተዋል። ለዚህ ሥራ ቀጥተኛ ምንጮች የሆኑኝን የግብፅ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አባቶችና በዚያም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን መነኮሳትን እግዚአብሔር በቸርነቱ ጠብቆ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን እያልኩ ፣ ከአንደኛ እስከ አምስተኛ ክፍል ድረስ ላሉ ወጣቶች ማስተማሪያ የሚሆን ሥርዓተ ትምህርት በየደረጃው በዚህ ዓመት አሳትሞ ለማሰራጨት የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶች እየተጠናቀቁ ሲሆን ከስድስተኛ እስከ ኮሌጅ መሰናዶ (12ኛ ክፍል) ያሉ መጻሕፍትም በአዲሱ ዓመት (ዕሥራ ምዕት) በእግዚአብሔር ፈቃድ ለኅትመት የሚበቁ መሆናቸውን ልገልጽ እወዳለሁ።

«እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል።» 1ኛ ሳሙኤል 7 ፥ 12

# መግቢያ

ይህ ሥርዓተ ትምህርት የመጀመሪያ ሙከራ ሲሆን በርካታዎቹ ትምህርቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከቤተክርስቲያን መጻሕፍትና ከትውፊተ ቤተክርስቲያን ተወስደው ለሚቀጥሉት የትምህርት ደረጃዎች እንደ መግቢያ ሆኖ የተዘጋጀ ነው። አንዳንዶቹ ትምህርቶች ልጆች ትምህርቶቹን ማስታወስ እንዲችሉ በአንደኛ ክፍል ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በድጋሚ ተካተተዋል።

ትምህርቶቹ በየወሩ ተከፋፍለው በቤተክርስቲያን ከሚከበሩ በዓላትም ጋር እየተቀራረቡ እንዲዘጋጁ ለማድረግ የተሞከረ ሲሆን በየመካከሉ ለሚኖሩ ክፍተቶች የማሟያ ትምህርቶቹ ተወስደው በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በቅደም ተከተል አገልግሎት ላይ ቢውሉ ተመሳሳይነት እንዲኖረው የሚረዳ መሆኑን አሳስባለሁ።

በሙዓለ ሕፃናት የሚገኙ ልጆች በጣም አጫጭር ታሪኮችን ብቻ ሰምተው ጥቂቶቹን ብቻ ማስታወስ የሚችሉ ናቸው። ማንበብም ስለማይችሉ በወላጆች ወይም በመምህራን መታገዝ ያስፈልጋቸዋል። በሕልምና በእውነታ መካከል ያለውን ልዩነት ማገናዘብ አይችሉም። በጣም ፈጠራ የታከለባቸው የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች የሚያስፈልጉአቸው ቢሆኑም መምህራኖቻቸውን በሚዘምሩት መዘመርም ሆነ በሚገኙበትም ሁኔታ መምሰልና ማስመሰል ይችላሉ። በዚህ ደረጃ የሚገኙ ልጆች የሚንቀሳቀሱና የተለያዩ ድምፆች ያሉባቸውን ነገሮች እንዲሁም ከሌሎች ጋር መጫወትንና ያዩትን በተግባር ማሳየትን ይወዳሉ። ልጆቹ ቤተክርስቲያን መምጣታቸው ደስታን ሊፈጥርላቸውና ፈጽመውም የሚወደዱ መሆናቸውን እንዲሰማቸው ማድረግ አንዷ ቱሉ ሊያስደነግጣቸው ወደ ሚችል ከባድ ቅጣት ማዘንበል አይገባም።

በዚህ ደረጃ የሚገኙ ልጆችን የሚያስተምሩ መምህራን በተፈጥሮ ለልጆች ፍቅር ያላቸውና ፍቅራቸውንም መግለጽ የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል። የዚህ ትምህርት ውጤትም በሚቀርቡላቸው መርጃዎችና በመምህሩ ጥረት ላይ የተመረኮዙ ናቸው። መምህሩ ልጆችን ለመሳብ ደመቅ ያለ ቀለማትን፣ ድምጽና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ቢጠቀሙ መዝሙራትንም ቢያዘምሩአቸው ለትምህርቱ ታላቅ ኃይል ይሆናሉ። መምህሩ በየዕለቱ የትምህርት መርሐ ግብሮች መዝሙራትን ሊዘምሩላቸውና ሊያስጠኑአቸው ያስፈልጋል። አንዳንድ ጊዜም ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሥዕላት ቢሰጡአቸውም ስለ ተማሩት ትምህርት ወላጆቻቸውን ለማስረዳት የበለጠ ዕድል ይፈጥርላቸዋል። አንዳንድ ጊዜ ቤተሰቡ ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጣ ልጆች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።

በዓመቱ ውስጥ ባልተቋረጠ ሁለት ሳምንታትም ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን መጎብኘታቸውና ክትትል ባለበት ሁኔታ በማኅበራዊ ነገሮች ተሳታፊ መሆናቸውም እጅግ ጠቃሚ ነው። ከሁሉም በላይ ግን መምህሩ ለዚህ አገልግሎት በትጋት መጸለይና በየመካከሉ የሚቀሩ ወይም ጨርሰው ያልመጡ ልጆችንም መጎብኘት ይጠበቅባቸዋል። መምህራንን ማግኘት በማይቻልባቸው ሥፍራዎች ወላጆች በሥርዓተ ትምህርቱ በመመራት ልጆችን ማስተማር ይችላሉ። በዚህ ደረጃ የሚገኙ ልጆች ቀለም በመቀባት የሚቀስሙት ትምህርት የበለጠ ስለሚሆን የተዘጋጁትን ሥዕሎች በአግባቡ ቀለም እንዲቀቡአቸው የወላጆች እገዛ እጅግ አስፈላጊ ነው። ልጆች በመንፈሳዊው ትምህርት እስካሁን ድረስ ያደጉበት ሁኔታ ያልተመጣጠነ ስለሆነ የክፍል ደረጃቸው ከፍ ቢልም ከዚህ መጽሐፍ ደረጃ ጀምረው መማራቸው ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በዚህ አጋጣሚም በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተከፈቱ ትምህርት ቤቶችም ይህንን ሥርዓተ ትምህርት መጠቀማቸው ልጆችን በየደረጃው ቤተክርስቲያናቸውን እያወቁ በበጎ ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚረዳቸው ይሆናል ብዬ አምናለሁ።

በመጨረሻም ይኽን ዝግጅት የበለጠ ለማሻሻል የሁሉም አስተያየትና ምክር በጣም አስፈላጊ ስለሆነ እባካችሁ እንዳይለየኝ እያልኩ አስቀድሞ በተጠቀሱት አድራሻዎች እንድትልኩልኝ ስል በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ።

እግዚአብሔር ይኽን ሥርዓተ ትምህርት የሚጠቀሙበትን አገልጋዮች ሁሉ በቸርነቱ ይርዳቸው።

## ኦርቶዶክሳዊ ሥርዓተ ትምህርት
## ለሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች

ማውጫ


**መስከረም ... 3**

- ዘመን መለወጫና ዐውደ ዓመት ... 4
- የበለስ ዛፍ ... 5
- መስቀል ... 8
- እመቤታችንና ኤል ሻዳይ ተራራ ... 11
- ዓለም እንዴት ተፈጠረ? ... 12

**ጥቅምት ... 14**

- እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ፈጠረ ... 15
- የኖኅ መርከብ ... 19
- አሮጊቷ ሣራ ልጅ ወለደች ... 21
- የያዕቆብ ሕልም ... 23
- ይስሐቅና ርብቃ ... 25

**ኅዳር ... 27**

- ያዕቆብና ዔሳው ... 28
- ዮሴፍና የንጉሡ ሕልም ... 30
- ሕፃኑ ሙሴ ... 33
- ባሕሩን መሻገር ... 35
- የቃል ኪዳን ታቦት ... 38

**ታኅሣሥ ... 40**

- እመቤታችንና ቅዱስ ገብርኤል ... 41
- እመቤታችን ቅድስት ኤልሳቤጥን እንደ ጎበኘቻት ... 43
- ጌታችን ተወለደ ... 45
- እረኞችና የጥበብ ሰዎች ... 47

**ጥር ... 49**

- ጌታችን ወላጆቹን ያከብራል ... 50
- ጥምቀት ... 52

**ከጾመ ነነዌ በፊትና ከጾመ ነነዌ በኋላ ... 55**

- ዮናስና በመርከብ ላይ ... 56
- ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ውስጥ ... 58

**ዐቢይ ጾም ... 60**

- የተመረጡ ወዳጆች (12ቱ ደቀ መዛሙርት) ... 61
- ጴጥሮስ በባሕር ላይ ተራመደ ... 63
- በሽተኛው ሰው ... 66
- የጠፋው በግ ... 69
- ታላቁ ድግስ (ግብዣ) ... 72

- ጠፍቶ የተገኘው ድሪም ........ 73
- ሕፃናት ጌታን በዕለተ ሆሳዕና ተቀበሉት ........ 74

**ትንሣኤና ከትንሣኤ በኋላ ........ 77**

- የደስታ ቀን ........ 78
- ጌታችንና ቅዱስ ቶማስ ........ 79
- በዐለት ላይ የተሠራው ቤት ........ 81
- መላእክት ........ 83
- ጌታችን ለቅዱስ ጳውሎስ ተገለጠለት ........ 85
- ዕርገት ........ 87
- ጰራቅሊጦስ ........ 90

**ጾመ ሐዋርያት ........ 93**

- የቅዱስ ጴጥሮስ የመጀመሪያ ተአምር ........ 94
- በሽማ የተሞሉት እንስሳት ........ 96
- አመሰግናለሁ በሉ ........ 97

**ነሐሴና ጾጉሜን ........ 98**

- ስደት ወደ ምድረ ግብፅ ........ 99
- ዓሣውና በውስጡ የነበረው ገንዘብ ........ 101
- መልአኩ ቅዱስ ጴጥሮስን ነፃ አወጣው ........ 102
- እግዚአብሔር ሳሙኤልን ከተኛበት ጠራው ........ 104

**የማሟያ ትምህርቶች ........ 107**

- ኤልያስና ቁራዎቹ ........ 108
- ዳዊትና ጎልያድ ........ 111
- ዳንኤልና የአንበሳው ጉድጓድ ........ 114
- ኤልያስና ባልቴትዋ ........ 117
- የአሮን በትር ........ 120
- በለአምና አህያው ........ 123
- እመቤታችንና ተአምሯ ........ 126

# መስከረም

## 1 ኛ ሳምንት

## ዘመን መለወጫ - እንቁጣጣሽ

**ዓላማ**

- ስለ ዘመን መለወጫ ወይም ስለ እንቁጣጣሽ እና ስለ ዐውደ ዓመት መማርና ከቅዱሳን መካከል የተወሰኑትን ስም ማጥናት።

**ጥቅስ**

- "ፈቃድህ ሁሉ በምድር ባሉት ቅዱሳንና ክቡራን ላይ ነው።" የዳዊት መዝሙር 15፥3።

**ምንባብ**

- የመስከረም 1 ቀን ስንክሳር።

**መግቢያ**

- መስከረም አንድ ቀን የምናከብረው በዓል ምን እንደ ሆነ በመጠየቅ የቅዱሳንን ሥዕላት አዘጋጅተው ያሳዩአቸው።
- ዐውደ ዓመት ምንድን ነው? በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ስንት ወራት ይገኛሉ? እንቁጣጣሽ ምንድር ነው?

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- መስከረም ከአሮጌ ወደ አዲስ ዓመት መሸጋገሪያ ነው። እንቁጣጣሽ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ታላቅ በዓል ነው።
- በመስከረም ወር ሜዳውና ተራራው ሁሉ በወርቅማ ቀለም የአደይ አበባ ያሸበርቃል።
- በዚህ ወቅት ኢትዮጵያዊቷ ንግስት ሳባ (ማክዳ) ንጉሥ ሰሎሞንን ጎብኝታ ስትመለስ ወገኖቿ ኢትዮጵያውያን ዕንቁ ወይም ጌጣጌጥ በመስጠት ስለ ተቀበሏት በዓሉ እንቁጣጣሽ ተብሏል። እንቁጣጣሽ ማለትም የዕንቁ ወይም የጌጣጌጥ ስጦታ ማለት ነው። በእንቁጣጣሽ ዋዜማ ሕፃናትና ወጣቶች እየዘመሩ ችቦ ይበራል።
- መስከረም አንድ ቀን ጠዋት ልጆች ባሕላዊ ልብሳቸውን በመልበስ አዲሱን ዓመት በምስጋና ለመቀበል ሁሉም ወደ ቤተክርስቲያን ይጓዛሉ። ከዚያም ሲመለሱ ሴቶች ልጆች ከቤት ወደቤት በመሄድ ..... ለምለም...... እያሉ በመዘመር ወንዶችም በወረቀት ላይ የሳሉአቸውን የተለያዩ ሥዕላት በየቤቱ በማዞር ከየቤቱ ስጦታ ይቀበላሉ። ስጦታውን በተቀበሉበትም ሥፍራ ሁሉ እነርሱም በአጸፋው ያመሰግናሉ።
- በእንቁጣጣሽ - ወላጆች በአዲሱ ዓመት ስላላቸው ተስፋ ሲወያዩ ሕፃናቱ ደግሞ በአገኙት ሳንቲም ደብተር፣ እስክርቢቶ፣ ከረሜላ ... ወዘተ በመግዛት ይደሰታሉ።
- በተጨማሪም መስከረም አንድ ቀን የመጥምቁ የቅዱስ ዮሐንስና የሌሎችም ቅዱሳን መታሰቢያ በዓል ይከበራል። በዓሉ በከተማና በገጠር አብያተ ክርስቲያናት በደመቀ ሁኔታ ይከበራል።
- በአጠቃላይ በኢትዮጵያውያን አዲስ ዓመት - መስከረም አንድ ቀን በሰማይ ያሉ ቅዱሳንን ከአምላካችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እናከብራለን። ቅዱሳን በምድር ሳሉ ጌታችን እንድናደርግ ያዘዘውን ያደረጉና ብዙ በጎ ሥራ የሠሩ ናቸው።
- እግዚአብሔር ያዘዘውን መልካም ሥራ የሠሩ ቅዱሳን ይባላሉ። ሲያርፉም ከአምላካችን ጋር ለመኖር ወደ ሰማይ ይወሰዳሉ።
- ዘወትር የአምላካቸውን ፊት እያዩም ደስ ይላቸዋል። እነዚህ ቅዱሳን ዘወትር ወዳጆቻችን መሆን ይችላሉ።
- እያንዳንዳችን የምንወዳቸውን ቅዱሳን መርጠን ወዳጆቻችን እንዲሆኑ ማድረግ እንችላለን።
- አቡነ ተክለሃይማኖት፣ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፣ አቡነ አረጋዊ፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ቅዱስ መርቆሬዎስ፣ አቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ፣ ቅድስት አርሴማ፣ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ... ከቅዱሳን መካከል በጣም ጥቂቶቹ ናቸው።
- በሚመለከቱአቸው የቅዱሳን ሥዕሎች ላይ የሚገኙት ምን እንደ ሆኑ ይጠይቁአቸው። ለምሳሌ በአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሥዕል ላይ የሚገኙ አንበሶችና ነብሮችን ወይም በአቡነ አረጋዊ ሥዕል ላይ የሚገኘውን ዘንዶ።
- በክፍሉ ውስጥ የሚገኙትን ልጆች ከቅዱሳን የሚመርጡትን ወዳጅ እንዲያደርጉ ያግዙአቸው።
- የቅዱሳንን ሥዕል አዘጋጅተው ለእያንዳንዳቸው የመረጡትን ቅዱስ ሥዕል በየልብሳቸው ላይ ይለጥፉላቸው።

**ማጠቃለያ**

- ልጆች እግዚአብሔር ስለሚወድደን በሥዕሉ እንደ ተመለከትናቸው ቅዱሳን እንድንሆን ይፈልጋል ።

**ተግባር**

- የቀን መቁጠሪያ አዘጋጅተው ይስጡአቸውና የሚወዷቸው ቅዱሳን የሚከብሩበትን ዕለት በቀይ ቀለም ምልክት እንዲያደርጉባቸው ይዘዙአቸው። የሚወዱአቸውን የቅዱሳን ሥዕልም ወደ ቤታቸው እንዲወስዱ ይስጡአቸው።

## 2 ኛ ሳምንት

## የበለስ ዛፍ

**ዓላማ**

- እግዚአብሔር ዘወትር የሚመለከተን መሆኑን መማር፡፡
- እግዚአብሔር ዘወትር ትክክለኛ ሥራ እንድንሠራ የሚፈልግ መሆኑን መረዳት፡፡

**ጥቅስ**

- "ዙሪያዋን እስክኮተኩትላትና ፋንድያም እስካፈስላት ድረስ በዚች ዓመት ደግሞ ተዋት፡፡" ሉቃስ 13፥8፡፡

**ምንባብ**

- የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 13 ከቁጥር 6 እስከ 9፡፡

**መግቢያ**

- ያለፈውን ትምህርትና ጥቅስ መከለስ፡፡
- ለትምህርቱ ተስማሚ የሆነውን ሥዕል ያዘጋጁ፡፡

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- አንድ ሰው ብዙ ዛፎችና ዕፅዋት የሚገኙበት የአትክልት ሥፍራ ነበረው፡፡
- ከዕለታት አንድ ቀን በዚህ የአትክልት ሥፍራ የበለስ ዛፍ መትከል ፈልጎ ተከለም፡፡
- ዛፉ አድጎ ፍሬ እስኪያፈራ ድረስ ለአንድ ዓመት ጠበቀ፤ ነገር ግን ፍሬ አላፈራም፡፡
- ሁለተኛውን ዓመትም ፍሬ ያፈራል ብሎ ጠበቀ አላፈራም፡፡ በሦስተኛውም ዓመት ቢጠብቅ ፍሬ አላፈራም፡፡
- በጣም ተቆጥቶ ሦስት ዓመት ሙሉ ፍሬ ያፈራል ብዬ ጠበቅሁት ነገር ግን አላፈራም ቁረጣት ቦታውን ከሚበላሽ ለሌላ እንጠቀምበት ብሎ ሠራተኛውን አዘዘው፡፡
- የአትክልቱ ሠራተኛ ግን ተክሉ እንዲቆረጥ አልፈለገም፡፡
- ተጨምሬ እንክብካቤ እንዲያደርግላትና ሌላ ዕድል እንዲሰጠው ለመነ፡፡
- የተክሉም ባለቤት ተጨማሪ ዓመት ሰጠው፡፡ ፍሬ ባታፈራ ግን ተቆርጣ ቦታውም ለሌላ ይሆናል አለው፡፡
- በዚህ ታሪክ የተክሉ ባለቤት እግዚአብሔር ሲሆን እኛ ደግሞ ተክሎች ነን፡፡
- ሁል ጊዜ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ለመሆን ቢመጣም የሚወደውን ሥራ ስለማንሠራ ይመለሳል፡፡
- እግዚአብሔር ሠራተኞቹን ልክ እንደ ተክል ባለቤት መጥፎ ሥራ ስንሠራ ይቆጣናል፡፡ ለምሳሌ ወላጆቻችን ስንዋሽ ይቆጣል፡፡
- እግዚአብሔር በእኛ ደስ እንዲለው በጎ ሥራ ሁል ጊዜ መሥራት ይገባናል፡፡
- እግዚአብሔር ስህተታችንን እንድናርም በርካታ ዕድሎችን ይሰጠናል፡፡
- እናታችን የነገረችንን በመስማት ስናጠፋም ይቅርታ ብለን ያዘዘችንን ሥራ መሥራት ይኖርብናል፡፡

**ጥያቄ**


1. ያ ሰው ተክል ለምን ተከለ?
2. አድጋ ፍሬ እስክታፈራ ስንት ዓመት ጠበቀ?
3. የአትክልት ሠራተኛውን ምን እንዲያደርግ አዘዘው?
4. የአትክልት ሠራተኛው ምን አለ?
5. እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንዲሆን ምን ማድረግ አለብን?

**ማጠቃለያ**

- መልካም ሥራዎችን ለመሥራት እንዲረዳንና መልካም ሰዎችም እንዲያደርገን ዘወትር ወደ እግዚአ መጸለይ አለብን፡፡

**ተግባር**

- ፍሬ ያላቸው ዛፎች ሥዕል አዘጋጅተው ፍሬዎቹንና ቅጠሎቹን በአረንጓዴ ቀለም እንዲቀቡ ያድርጉአቸው።
- እነዚህ በቀለም የቀቡአቸው ዛፎች እነርሱ መሆናቸውንና ወደፊት ምን ያህል ፍሬያማ እንደሚሆኑ በሥዕሉ አማካኝነት ያስረዱአቸው።
- የአዲስ ዘመን ወይም የእንቁጣጣሽ መዝሙሮችን አስጠንተው እንዲዘምሩ ያድርጉአቸው።



የበለስ ዛፍ

## 3 ኛ ሳምንት
## መስቀል

**ዓላማ**

- ለመስቀል በዓል መከበር ምክንያት የሆነውን ታሪክ መማር፡፡

**ጥቅስ**

- "መስቀሉንም ተሸክመህ ና ተከተለኝ፡፡" ማርቆስ 10፥21፡፡

**ምንባብ**

- የመስከረም 17 ቀን ስንክሳር፡፡
- የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 10 ቁጥር 38፡፡

**መግቢያ**

- ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ፡፡
- መስቀል እንዴት እንደሚሳል የሚያውቁ ሕፃናትካሉ ይጠይቁ፡፡ ደመራ ምንድር ነው? ችቦስ ምንድር ነው?
- መስቀል እንዴት እንደሚሠራ የማያውቁ ለሆኑ ሕፃናት እንዴት እንደሚሳል ያሳዩአቸው፡፡

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- በየዓመቱ መስከረም 17 ቀን የመስቀል በዓል ይከበራል፡፡ በመስቀል ዋዜማ ደግሞ የደመራ በዓል ይከበራል፡፡
- ለደመራው ረጃጅም እንጨቶችና ችቦዎች ተዘጋጅተው በአግባብ ተደራርበው ይቆማሉ፡፡ ዙሪያቸውም አደይ አበባ ይደረግባቸዋል፡፡ ከላይም የመስቀል ምልክት ይደረጋል፡፡ ይኸም በመስቀል አደባባዮች ይፈጸማል፡፡
- ዝግጅቱ ሲፈጸም በቤተክርስቲያን አባቶች ጸሎት ከተደረገ በኋላ በዓሉን የተመለከተ ትምህርት ተሰጥቶ ደመራው ይለኮሳል፡፡ በተጨማሪም የደመራ በዓል በየመንደሩ በተመሳሳይ ሁኔታ ሽማግሌዎች ነዋሪዎች ተሰብስበው ችቦ እየበራ ይከበራል፡፡
- መስቀል በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት መሠረት ታላቅ ደስታና ዝማሬ እየተደረገ በደማቅ ሁኔታም ይከበራል፡፡
- ኢትዮጵያ የጌታችን መስቀል የሚገኝባት አገር ስለሆነች መስቀሉ በሚገኝበትና ባረፈባቸው መንናትና ገዳማት ሁሉ በደመቀ ሁኔታ ይከበራል፡፡
- ይኸን ቀን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል ኃይልና ክብር እናስታውስበታለን፡፡
- ጌታችን ከተሰቀለ በኋላ በተሰቀለበት መስቀልና በተቀበረባት መቃብር ብዙ ተአምራት ተደርገዋል፡፡
- አይሁድም በመስቀሉ የሚደረገውን ተአምር ሲሰሙ ተቆጡ፡፡
- በከተማዋ ዙሪያ የሚኖሩትን ሁሉ የቤታቸውን ቆሻሻ እየሰበሰቡ የመስቀሉ ተአምር በሚደረግበትና መስቀሉን በቀበሩበት ቦታ እንዲጥሉ አዘዙ፡፡
- ይኸንንም እያደረጉ ከ200 ዓመት በላይ ቆዩ፡፡
- ቦታውም ተራራ እስኪሆን ድረስ ከ200 ዓመት በላይ ቆሻሻ ጣሉበት፡፡
- እሌኒ የምትባለው ቅድስት በመስቀሉ ተማረከች፡፡
- ንግሥት እሌኒ የቆስጠንጢኖስ እናት ናት፡፡
- ልጅዋ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ለጦርነት ከመሄዱ በፊት የመስቀል ምልክት ስለ ተገለጠለት መስቀሉን ወደደችው፡፡
- እርሱም የመስቀሉን ምልክት ካየ በኋላ ተዋግቶ አሸነፈ፡፡
- እናቱ ቅድስት እሌኒም ጌታችን የተሰቀለበትን መስቀሉን ለመመልከት ወደ ኢየሩሳሌም ሄደች፡፡
- መስቀሉ የሚገኝበትንም ቦታ እንዲነግሩዋት ብዙ ሰዎችን ጠየቀች፡፡ የሚያውቀው ግን አልነበረም፡፡
- በመጨረሻም ኪራኮስ የሚባል ሽማግሌ መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ ያውቅ ስለ ነበር ነገራት፡፡

- ኪራኮስም እሳትና እጣን አድርጋ እንድታቀጣጥል ጢሱም ወደ ላይ ወጥቶ ተመልሶ መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ እንደ ሚያመላክታት ነገራት:: የደመራን በዓል የምናከብረውም በዚሁ የተነሳ ነው::
- እርስዋም እንደ ተነገራት አደረገች:: ወታደሮችዋንም ጠርታ ቦታውን ቆፍረው እንዲያጸዱ አደረገች::
- ቅድስት (ንግሥት) እሌኒም መስቀሉን አስቆፍራ አወጣችው::
- በቦታውም ላይ በመስቀል ስም ቤተክርስቲያን አሠራች::

**መምህር**


- ለሕፃናቱ ታሪኩን ደግመው ይተርኩላቸውና የንጉሡንና የእናቱን ስም ይጠይቁአቸው::
- ይኽ ታሪክ የተደረገበትን ቀን ያስታውሱ እንደሆነ ሕፃናቱን መልሰው ይጠይቁአቸው::
- በትምህርቱ መግቢያ የተጠቀሰውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ያስታውሱ እንደሆነ ይጠይቁአቸው::

**ማጠቃለያ**

- እኛ ሁላችንም መስቀልን እንወደዋለን?
- የእግዚአብሔርን ዕርዳታ በምንፈልግበት ቦታ ሁሉ በመስቀል ምልክት እናማትባለን?
- መስቀልም ብርቱ፣ ኀበዝ፣ ኃያል ያደርገናል::
- መስቀል ምንም እንዳንፈራ ድፍረት ይሰጠናል::

**ተግባር**

- የመስቀልን በዓል ከወላጆቻችሁ ጋር በመስቀል አደባባዮችና በቤተክርስቲያን በመገኘት አክብሩ ::
- የመስቀል ምልክት ያለበት ወረቀት ይስጡአቸውና በፈለጉት ቀለም እንዲቀቡት ያድርጓቸው:: ወይም ባዶ ወረቀት ይስጡአቸውና መስቀል እንዲስሉ ያድርጉ::
- አንድ መስቀል በትልቁ እና በትምህርቱ መግቢያ የተጠቀሰውን ጥቅስ በኮምፒዩተር ጽፈው ያዘጋጁ::
- መስቀሉን ከወረቀቱ ላይ ቀደው ያውጡ:: ጥቅሱንም እንደዚሁ ቀድደው ያዘጋጁት::
- መስቀሉን ከላይ ጥቅሱን ከሥር አድርገው በፊታቸው በሚገኝ ግድግዳ ወይም ጠረጴዛ ላይ ይለጥፉት::
- ሕፃናት የፈለጉትን ነገር በመስቀሉ አጠገብ እንዲጽፉ ወይም ጥሩ መልእክት ያለው ስቲከር እንዲለጥፉ ይፍቀዱላቸው::
- የሕፃናቱን ስም በመስቀሉ አጠገብ ወይም ሥር ይጻፉ::



**መስቀል**

## 4 ኛ ሳምንት
## እመቤታችንና የኤል ሞካታም ተራራ

**ዓላማ**

- ❖ እርዳታን ስንፈልግ እመቤታችን ትረዳናለች።

**ጥቅስ**

- ❖ በእምነት አድናችኋልና። ኤፌሶን 2፡8።

**መግቢያ**

- ❖ ያለፈውን ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- ❖ ተራራ ምን እንደ ሆነ ሕፃናትን ይጠይቋቸው። ተራራ ትንሽ ወይስ ትልቅ? አጭር ወይስ ረጅም ነው?
- ❖ ተራራ ላይ ወጥታችሁ ታውቃላችሁ? ከእናንተ መካከል ተራራ ማንቀሳቀስ የሚችል አለ?
- ❖ ለትምህርቱ መርጃ የሚሆን የተራራ ሥዕል ያሳዩአቸው።
- ❖ በትእምርተ መስቀል ማማተብ ምንድር ነው?
- ❖ ገዳም ምንድር ነው? ኪርያላይሶን ማለትስ ምን ማለት ነው ?

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- ❖ በአንድ ወቅት ክርስቲያኖችን የሚያስጨንቃቸው አንድ ንጉሥ ነበር።
- ❖ ክርስቲያኖችንም ችግር ውስጥ ሊከታቸው ፈለገ።
- ❖ በግብፅ ኤል ሞካታም የሚባል ትልቅ ተራራ ነበር፤ አሁንም በካይሮ ከተማ ይገኛል።
- ❖ ይኸ ክፉ ንጉሥ በመጽሐፍ ቅዱስ የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል እምነት ቢኖራችሁ ይህንን ተራራ ከዚህ ተነስተህ ወደዚያ ሂድ ብትሉት ይሄዳል። ማቴዎስ 17፡20 የሚለውን ቃል አገኘ።
- ❖ የክርስቲያኖቹን አባት ጠርቶ እምነት ካለህ አሁን ያለበትን ቦታ አልወደድኩትምና ይህን ተራራ ከዚህ ሥፍራ አንስተህ ከከተማው ውጪ ውሰደው ፤ አለዚያ ግን ክርስቲያኖች ሁሉ ከባድ ቅጣት ይቀጣሉ አለው።
- ❖ የቤተክርስቲያኒቱም አባት የሆኑትና ክርስቲያኖቹ እንዴት አድርገው ይኸን ትልቅ ተራራ ማንቀሳቀስ እንደሚችሉ እያሰቡ አዘኑ።
- ❖ እርሳቸውና ክርስቲያኖቹም ሁሉ ለሦስት ቀን እየጾሙ ጸለዩ። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለቤተክርስቲያኒቱ አባት ተገልጻ ስምዖን የሚባል ሰው አለ፤ እርሱም የጸና እምነት አለው፤ ይኸንንም ተራራ አንስቶ ወደ ሌላ ሥፍራ በመውሰድ ይረዳችኋል አለችው።
- ❖ የቤተክርስቲያኒቱም አባት ስምዖንን አስፈልገው አግኝተው ተራራውን አንስቶ በመውሰድ እንዲያግዛቸው ጠየቁት።
- ❖ የቤተክርስቲያኒቱ አባት፣ ስምዖንና ክርስቲያኖች ሁሉ በተራራው ፊት ለፊት ተሰብስበው አቤቱ ይቅር በለን፤ አቤቱ ይቅር በለን፤ አቤቱ ይቅር በለን (ኪርያላይሶን፣ ኪርያላይሶን ፣ ኪርያላይሶን) እያሉ በትእምርተ መስቀል ምልክት እያማተቡ ጸለዩ።
- ❖ ሲጸልዩም በጥቂት በጥቂቱ ተራራው ተንቀሳቀሰ። እንዲህም እያለም ተራራው ሙሉ በሙሉ ተነስቶ ወደ ሌላ ሥፍራ እስኪሄድ ድረስ ጸለዩ።
- ❖ ተራራውም ተነስቶ ስለ ሄደ ክርስቲያኖች ሁሉ ሳይቀጡ ተረፉ።
- ❖ ዛሬ ይኸ ተራራ በካይሮ ከተማ ገዳም ተመስርቶበት መንፈሳዊ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

**ማጠቃለያ**

- ❖ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የቤተክርስቲያኒቱ አባት ከስምዖን ጋር እንዲገናኙ ረድታቸዋለች።
- ❖ ስለ እመቤታችን አንድ መዝሙር አስጠንተው እንዲዘምሩ ያድርጉአቸው።

## 5 ኛ ሳምንት

## ዓለም እንዴት ተፈጠረ?

**ዓላማ**

- የሥነ ፍጥረትን አፈጣጠር መማር።

**ጥቅስ**

- እነሆም እጅግ መልካም ነበረ። ኦሪት ዘፍጥረት 1፡31።

**ምንባብ**

- ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ።

**መግቢያ**

- ያለፈውን ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- የፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ ዛፎች፣ እንስሳት፣ አዕዋፋት፡ እንዲሁም ዓሣና ወዘተ... ሥዕሎች ያዘጋጁላቸው።
- የፍጥረትን አፈጣጠር በሚተርኩበት ወይም በሚያስረዱበት ጊዜ ሥዕሎቹን የሚለጥፉበት ስሌዳ ያዘጋጁ።
- ዓለምን የፈጠረው ማን እንደሆነ ሕፃናቱን ይጠይቁአቸው።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**


- ሕፃናቱ ዓይኖቻቸውን እንዲጨፍኑ ይንገሩአቸው። አሁን ጨለማ ይሆንባቸዋል።
- ሕፃናቱ ጆሮአቸውን በእጃቸው እንዲደፍኑ ይንገሩአቸው። አሁን ደግሞ ጸጥታ ይሆናል።
- ከረጅም ዘመናት በፊት፣ ዓለምም ከመፈጠሩ አስቀድሞ ሁሉም ጨለማና ጸጥ ያለ ነበር።
- አዕዋፋትም፣ ሰዎችም፣ እንስሳትም ሁሉ አልነበሩም።
- በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር "ብርሃን ይሁን አለ። ብርሃኑንም ቀን ብሎ ጠራው። ፀሐይም በቀን ታሽብርቅ። አለ።
- ብርሃን ምን ያህል መልካም ነበረ?
- እግዚአብሔር ጨለማን ሌሊት አለው። ጨረቃንና ከዋክብትን በጨለማ እንዲታዩ አደረጋቸው።
- የሆነው ሁሉ መልካም ነበረ።
- በመቀጠልም እግዚአብሔር ሰማይ፣ መሬት፣ ባሕር፣... ይሁን አለ። ሁሉም ሆኑ።
- እስከዚህ ድረስ ግን ምድር ባዶ ነበረች፣ ጸጥታም ነበረባት።
- ቀጥሎ እግዚአብሔር ዕፅዋትን፣ ዛፎችን እና አትክልትን ፈጠረ።
- እነርሱም ለመብላት መልካም የሆኑትን ፍሬዎች ሁሉ አፈሩ። አበቦቹም መዓዛቸው ለማሽተት የሚወደድ ነበር።
- ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር በባሕር ውስጥ እንዲዋኙ ዓሣን፣ በአየር እንዲበሩ አዕዋፋትን ጠፈረ።
- ዓለምም ጸጥታ ወይም ዝምታ የሰፈነባት መሆንዋ ቀረ። ውሻ "ው፣ው፣ው" ድመት "ሚያው፣ ሚያው፣ ሚያው" አይጥ "ሲክ፣ ሲክ፣፣ ሲክ ላም "እምቧ፣ እምቧ፣ እምቧ" ወዘተ ይሉ ጀመር።
- በሥነ ፍጥረት የተነሳ ዓለም በድምጽ ደመቀች እግዚአብሔርም በፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ደስ አለው።
- እግዚአብሔር የፈጠረውም ሁሉ እጅግ መልካም ነበር።

**ማጠቃለያ**

- በዚህ ዓለም ያለውን ሁሉ ፍጥረት የፈጠረው እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር የፈጠረውም ሁሉ መልካም ነበረ።

**ተግባር**

- የበርካታ እንስሳት፣ ዛፎች፣ ዓሣ፡ ፀሐይ እና ጨረቃ ሥዕሎች ያዘጋጁ።
- ለሕፃናቱ ባዶ ወረቀት ይስጡአቸው ማጣበቂያም እንዲሁ። የሚሰጡአቸውን ሥዕሎች በባዶ ወረቀቶች ላይ እንዲለጥፉ ያድርጉአቸው። በወረቀታቸው ላይ የሚገኙትን ሁሉ ማን እንደፈጠራቸው ይጠይቁአቸው።
- የሚያውቁአቸውን እንስሳት ድምፅ እንዲያሰሙ ያድርጉአቸው።



ሥነ ፍጥረት

# ጥቅምት

## 6 ኛ ሳምንት

## እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ፈጠረ

**ዓላማ**

❖ እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰው አዳምንና የመጀመሪያዋን ሴት ሔዋንን እንደፈጠረ መማር።

**ጥቅስ**

❖ "እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ።" ኦሪት ዘፍጥረት 1፥27።

**ምንባብ**

❖ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እና ምዕራፍ 2 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ።

**መግቢያ**

❖ ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
❖ እንስሶችን፣ ዛፎችን፣ ፀሐይን፣ ጨረቃንና አእዋፋትን ማን እንደ ፈጠራቸው ሕፃናቱን ይጠይቁአቸው።
❖ ባለፈው ጊዜ ለማስተማሪያነት የተጠቀሙባቸውን ሥዕሎች በማሳየት እኛን ማን ፈጠረን ? ብለው ይጠይቁአቸው።
❖ ወንድ እና ሴት አሻንጉሊቶች(Dolls) አዘጋጅተው የአዳምንና የሔዋንን አፈጣጠር ይተርኩላቸው።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

❖ እግዚአብሔር ሌሎቹን ፍጥረታት ሁሉ ከፈጠረ በኋላ ሁሉም መልካም እንደሆነ አየ
❖ ሆኖም ግን አንድ ነገር ይቀር ነበር። እስኪ ገምቱ! ምንድር ነበር የቀረው?
❖ አዎ ሰው ይቀር ነበር።
❖ እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት ሰውን በመፍጠር ማጠናቀቅ ፈለገ።
❖ ከምድር አፈር ወስዶ ሰውን ፈጠረው።
❖ የሕይወትንም እስትንፋስ እፍ አለበት። ሰውም ሕያው ፍጥረት ሆነ።
❖ አዳምም እጁን፣ እግሩን፣ ጭንቅላቱን ማንቀሳቀስ ጀመረ (አሻንጉሊቱን በማንቀሳቀስ ያሳዩአቸው)።
❖ አዳም ለእንስሳቱ ሁሉ ስም እንዲሰጣቸው እግዚአብሔር አዘዘው።
❖ ባለፈው ጊዜ የተጠቀሙባቸውን የእንስሳት ሥዕሎች እያሳዩ አዳም ይኽን ምን ብሎ ጠራው ብለው ይጠይቁአቸው።
❖ አዳም ለእንስሳቱ ሁሉ ስም ካወጣላቸው በኋላ እንደርሱ ብቻውን የሆነ እንደሌለ ተመለከተና አዘነ።
❖ እግዚአብሔርም በአዳም ላይ ከባድ እንቅልፍ አመጣበት።
❖ ከጐኑም አንዲት አጥንት ወስዶ ሴት አድርጐ ሠራት።
❖ አዳምም ውበቷን እና መልካምነቷን አይቶ ደስ አለው። ስሟን ሔዋን ብሎ ጠራ።
❖ በዚህ ጊዜ ሴት አሻንጉሊትዋን(Doll) ወደ ወንዱ አሻንጉሊት(Doll) አስጠግተው ያሳዩአቸው።

**ጥያቄ**

1. የሴትዋ ስም ማን ነበረ ?
2. ይህችን ሴት ማን ፈጠራት ?
3. እግዚአብሔር ሔዋንን ለምን ፈጠራት ?

❖ እግዚአብሔር የፈጠራትን ሔዋንን ለአዳም ሰጠ።


- አዳም በሚሠራው ሥራ ሁሉ ሔዋን ትረዳው ነበር፡፡
- አዳምም በሔዋን በጣም ደስ ይለው ነበር፡፡ ምክንያቱም ማንኛውንም ሥራ አብረው ይሠሩና ይረዳዱ ስለነበር ነው፡፡

**ማጠቃለያ**


- እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ፈጠረ፡፡
- በዓለም ያለ ሕዝብ ሁሉ የተገኘው ከአዳምና ከሔዋን ነው፡፡

**ተግባር**

- የወንድ(አዳም) እና የሴት(ሔዋን) ሥዕሎችን አዘጋጅተው በማጣበቂያ አድርገው ሕፃናቱ ካለፈው ሳምንት ሥዕሎች ጋር እንዲለጥፉ ወይም በቀለም እንዲቀቡ ያድርጉአቸው፡፡



እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋን ፈጠረ



አዳምና ሔዋን ከገነት ሲወጡ

# 7 ኛ ሳምንት

## የኖኅ መርከብ

**ዓላማ**

- ❖ ስለ ኖኅና ስለ መርከቡ ታሪክ መማር።
- ❖ እግዚአብሔርን ስለ መፍራት እና ስለ ማክበር መማር።

**ጥቅስ**

- ❖ "መርከብን ለአንተ ሥራ።" ኦሪት ዘፍጥረት 6፥14።

**ምንባብ**

- ❖ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 6 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ።

**መግቢያ**

- ❖ ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- ❖ የመርከቢቱን ሥዕል ያዘጋጁ።
- ❖ የተለያዩ እንስሳትን ሥዕልም ያዘጋጁ ወይም በተንቀሳቃሽ ምስል ያሳዩአቸው።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**


- ❖ በመዶሻ ኳ፣ኳ፣ኳ እያደረገ ኖኅ ታላቂቱን መርከብ ሠራ።
- ❖ የሠራው መርከብ ለቤተሰቡ እንዲሁም ከእንስሳትና ከአእዋፋትም ሁለት ሁለት አድርጐ ለወሰዳቸው በቂ ነበር።
- ❖ በዚያ ዘመን በዚህ ዓለም የነበሩት ሰዎች በሚሠሩት ሥራ እግዚአብሔር ደስ አላለውም ነበር።
- ❖ ምክንያቱም ሥራቸው ሁሉ መጥፎ ነበርና ነው። ኖኅ ግን የእግዚአብሔር ወዳጅ የሆነ ብቸኛ ሰው ነበር።
- ❖ እግዚአብሔርም ከባድ ዝናብ በምድር ላይ እንደ ሚያዘንብ ለኖኅ ነገረው።
- ❖ ዝናቡም በምድር ላይ ለአርባ ቀንና ሌሊት ሁሉም ነገር እስኪጥለቀለቅ ድረስ ዝናብ ይዘንባል አለው።
- ❖ እግዚአብሔር ኖኅን ታላቅ መርከብ እንዲሠራና በውኃው ላይ እንድትንሳፈፍ የሚያደርጋት መሆኑን ነገረው።
- ❖ ኖኅም ለእግዚአብሔርን ታዝዞ ታላቅ መርከብን ሠራ።
- ❖ ኖኅም ከእንስሳትና ከአእዋፋት ሁሉ ሁለት ሁለት እያደረገ ወደ መርከቡ አስገባቸው።
- ❖ እንስሳቱም ተደስተው እምቧ፣ ባአ፣ ውው ወዘተ... ይሉ ነበር።
- ❖ ኖኅም ከቤተሰቡ ሁሉ ጋር ሆኖ ወደ መርከቡ ገባ። ቁጥራቸውም ስምንት ነበር። ስምንቱ እነማን ነበሩ?
- ❖ ሁሉም ወደ መርከቡ ከገቡ በኋላ ኖኅ የመርከቢቱን በር ዘጋ።
- ❖ ከባድ ዝናብም በምድር ላይ መዝነብ ጀመረ። አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ሙሉ ዘነበ።
- ❖ ውኃም በመሬት ሁሉ ሞልቶ መፍሰስ ሲጀምር የኖኅ መርከብም በውኃው ላይ ተንሳፈፈች።
- ❖ ኖኅና ቤተሰቡ እንስሳቱና አእዋፋቱ ሁሉ በመርከቢቱ ውስጥ ሆነው ከጥፋት ውኃ በእግዚአብሔር ኃይል ተረፉ ፣

**ማጠቃለያ**

- ❖ ቃሉን የሚሰሙትን ትዕዛዙንም የሚጠብቁትን ልጆቹን እግዚአብሔር ከክፉ ነገር ሁሉ ይጠብቃቸዋል።
- ❖ እግዚአብሔር የሚወደውን የምንሠራ ከሆንን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ይሆናል ይጠብቀናልም።

**ተግባር**

- ❖ ለወደፊቱ ከፍ ያለ የመርከብ ምሥል (Model) ሠርተው በውስጣቸው እንስሳትንና(Model) አእዋፋትን(Model) አድርገው ሕፃናቱ በመካከላቸው እንዲቀመጡ ያድርጉአቸው።
- ❖ ለሕፃናቱ ከተቻለ ተቆራርጦ የተዘጋጀ ወረቀት ሰጥተዋቸው የየራሳቸውን መርከብ ወይም ጀልባ ገጣጥመው እንዲሠሩ ይርዱአቸው።



እንስሳትና አዕዋፋት ወደ ኖኅ መርከብ ሲገቡ

## 8 ኛ ሳምንት

## አሮጊቷ ሣራ ወለደች

**ዓላማ**

- እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር በወደደው በማንኛውም ጊዜ እንደሚያደርግ መማር።

**ጥቅስ**

- "እግዚአብሔር ሳቅ አድርጐልኛል።" ኦሪት ዘፍጥረት 21፥6።

**ምንባብ**

- ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 18 እና ምዕራፍ 21 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ።

**መግቢያ**

- ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- የሕፃናትን ሥዕል ወይም ፎቶግራፍ ያሳዩአቸው።
- ሕፃናት ምን እንደሚሠሩ ወይም ምን እንደሚያደርጉ ይጠይቁአቸው።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**


- አንድ ቀን እግዚአብሔር አብርሃምን ሊያነጋግረው ፈልጐ ተገለጠ።
- በመነጋገር ላይ እያሉም እግዚአብሔር አብርሃምን "ወንድ ልጅ በቅርቡ ትወልዳለህ።" አለው።
- ሣራም እግዚአብሔር(ሥላሴ) ከአብርሃም ጋር ሲነጋገሩ ትሰማ ነበር።
- "አሁን በታላቅ እርጅና እያለሁ እንዴት ልወልድ እችላለሁ? " እያለች በራስዋ ሳቀች።
- እግዚአብሔርም አብርሃምን "ሣራ ስለምን ሳቀች? እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ እንደሚችል አታምንምን? " አለው።
- እግዚአብሔርም ኃይሉን በአብርሃምና በሣራ ፊት ገለጠ።
- ሣራም ወንድ ልጅ ወለደች።
- ስሙንም ይስሐቅ አለችው።
- የመጀመሪያ ልጃቸውን ሲወልዱ አብርሃም የ100 ሣራ ደግሞ የ90 ዓመት ዕድሜ ነበራቸው።
- ይስሐቅም የመጀመሪያ ልጃቸው ነበርና አብርሃምና ሣራ ደስ አላቸው።
- እግዚአብሔር ያደረገላቸውንም ለሰዎች ሁሉ ነገሩ።

**ማጠቃለያ**

- እግዚአብሔር ልጆቹን ለመርዳት ማንኛውንም ነገር ያደርጋል።
- እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በጊዜው እንዲሁም ከመሆኑም አስቀድሞ ያውቃል።
- ልጆች እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ የነገረንን ሁሉ ልናምን ይገባል።

**ተግባር**

- የአብርሃምንና የሣራን ታሪክ የሚያስረዳ ፊልም ወይም ሥዕል ያሳዩአቸው።
- ለትምህርቱ ተስማሚ የሆነውን ሥዕል በከለር እንዲቀቡ ያድርጉአቸው።



ሣራ በእርጅናዋ ልጅ ወለደች

## 9 ኛ ሳምንት
## የያዕቆብ ሕልም

**ዓላማ**

- ስለ መላእክት መማር።
- ሰማይና ምድር እንዴት እንደተገናኙ መረዳት።

**ጥቅስ**

- "የእግዚአብሔር መላእክት ይወጡበት ይወርዱበት ነበር።" ኦሪት ዘፍጥረት 28፥12።

**ምንባብ**

- ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 28 ከቁጥር 10 እስከ 22።

**መግቢያ**

- ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- ሕፃናቱ የመላእክትን ሥዕል አይተው ያውቁ እንደሆነ ይጠይቁአቸው።
- ሕፃናቱን መላእክት ምን እንደሚመስሉ መሰላልም ምን እንደ ሆነ ይጠይቁአቸው።
- የዛሬው ትምህርት ብዙ መላእክት ሲወጡበት ሲወርዱበት የነበረውን መሰላል የተመለከተ ነው።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- ያዕቆብ የአባቱን የይስሐቅን በረከት ተቀበለ።
- ከወንድሙ ከዔሳው ፊት ሸሽቶ ከቤርሳቤህ ወደ ካራን አመለጠ።
- ከቤርሳቤህ እስከ ካራን ያለው መንገድም በጣም ሩቅ ነበር። ያዕቆብም ፀሐይ እስክትጠልቅ ድረስ ሙሉ ቀን ተጓዘ።
- ስለ ደከመውም ዕረፍት ለማድረግ ወሰነ። በራሱ ሥር ድንጋይ እንደ ትራስ አድርጐ ተኛ።
- ወዲያውም እንደተኛ ሕልም ማየት ጀመረ። ሕልም ምን እንደሆነ ጠይቀው ያብራሩላቸው።
- ያዕቆብም ከምድር እስከ ሰማይ የተዘረጋ መሰላል ተመለከተ።
- በመሰላሉም ጫፍ ላይ እግዚአብሔር ለያዕቆብ ታየው። ዘርህን አበዛዋለሁ ብሎ ያዕቆብን ባረከው።
- ወደዚህች ሥፍራ ተመልሶ እስኪመጣ በመንገዱ ሁሉ ከርሱ ጋር እንደሚሆን እግዚአብሔር ለያዕቆብ ነገረው።
- ያዕቆብም ተገርሞ ከእንቅልፉ ሲነቃ እርሱ በተኛበት ሥፍራ እግዚአብሔር እንደነበረ ተረዳ።
- የተኛበትንም ድንጋይ ወስዶ ሐውልት አድርጎ አቁሞ ይህ የእግዚአብሔር ሥፍራ ነው ብሎ ዘይት አፈሰሰበት።
- ከመንገዱም በሰላም ተመለሰ።
- ያዕቆብም በእግዚአብሔር እንደሚተማመንና ከአሥር አንድ ከሚያገኘው ሁሉ ለእግዚአብሔር ሊሰጥ ቃል ገባ።

**ማጠቃለያ**

- እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን አገናኝቶአቸዋል። ያዕቆብ በሕልመ ያየው መላእክትን ነው።
- መላእክት በምንሄድበት ሁሉ ይረዱናል፣ ያግልዱናል፣ ያግዙናል።
- መላእክት እጅግ መልካም ናቸው።
- መላእክት እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ሁሉ ይፈጽማሉ።

**ተግባር**

- የመላእክትን ሥዕል አዘጋጅተው ወደ ቤታቸው እንዲወስዱ ይስጡአቸው።
- ሕፃናት በፈለጉት መንገድ የመላእክት ሥዕል እንዲስሉ ያድርጉአቸው። እርስዎም ከኮምፒዩተር በፕሮጀክተር ያሳዩአቸው።
- ሁላችንም እንደ ያዕቆብ በእግዚአብሔር እንታመን።



**የያዕቆብ ሕልም**

## 10 ኛ ሳምንት
## ይስሐቅና ርብቃ

**ዓላማ**

- ❖ የይስሐቅንና የርብቃን ታሪክ መማር፡፡
- ❖ እግዚአብሔር በውሳኔአችን ሁሉ የሚመራን መሆኑን መማር፡፡

**ጥቅስ**

- ❖ "ስለ ስምህ መንገዴን አቅና ምራኝም፡፡" መዝሙር 30፥3፡፡

**ምንባብ**

- ❖ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 24 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ፡፡

**መግቢያ**

- ❖ ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ፡፡
- ❖ ሕፃናትን ሠርግ ምን እንደ ሆነ ያውቁ እንደ ሆነ ይጠይቁአቸው፡፡
- ❖ ሠርግ ማለት አንድ ወንድና አንዲት ሴት ቤተሰብ ለመመስረት ፈቃደኞች ሲሆኑ ተጋብተው የሚፈጸም የደስታ ሥነ ሥርዓት መሆኑን ለሕፃናት ይግለጹላቸው፡፡
- ❖ የአብርሃም አገልጋይ ለይስሐቅ ፍጹም የሆነች ሚስት ለማግኘት እርዳታን ፈልጎ ወደ እግዚአብሔር እንደ ጸለየ በአጽንኦት ያስረዱአቸው፡፡

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- ❖ ይስሐቅም ለአቅመ አዳም ሲደርስ ይስሐቅ ማግባት የሚችል መሆኑን አብርሃም ወሰነ፡፡
- ❖ ሲሞትም ይስሐቅ ብቸኝነት እንዳይሰማው አባቱ አብርሃም አሰበለት፡፡
- ❖ አብርሃም ለልጁ የምትሆን መልካም ሚስት እንዲፈልግ ጥሩ አገልጋዩን ላከው፡፡
- ❖ አገልጋዩ የሚመርጣት ሚስት እግዚአብሔርን የምትወድድ የተለየች መሆን ይገባታል፡፡
- ❖ ለይስሐቅ የምትመረጠው ልጃገረድ በተጨማሪ የእግዚአብሔርን ሕግ የምታከብር መሆን ይጠበቅባታል፡፡
- ❖ አብርሃም ራቅ ብሎ በመሄድ ከወገኖቻቸው መካከል አንዲቱን ልጃገረድ እንዲፈልግለት አገልጋዩን አዘዘው፡፡
- ❖ ወላጆቿን ጥላ ይህን ያህል የራቀ መንገድ ተጉዛ በፈቃደኝነት የምትመጣ ልጃገረድ ትኖራለች? ብሎ አገልጋዩ አዘነ፡፡
- ❖ አብርሃም እግዚአብሔር ነገሩን ሁሉ ስለ ሚያከናውን በአንድም ነገር እንዳይጨነቅ አገልጋዩን አሳሰበው፡፡
- ❖ አገልጋዩም ረጅም መንገድ ተጉዞ ሲደክመው በጣም ተጠማ፡፡ ግመሎቹንም እረፍት እንዲያገኙ ካደረጋቸው በኋላ ውኃ የሚሰጠው ሰው ተቀምጦ ጠበቀ፡፡
- ❖ አንዲት መልካም ልጃገረድ ውኃ በእንስራዋ ቀድታ ስትመለስ ታጠጣው ዘንድ ለመናት፡፡
- ❖ እርስዋም እንስራዋን አውርዳ አጠጣችው፤ ለግመሎቹም ሁሉ እስኪረኩ ድረስ በእንስራዋ ውኃ እያመላለሰች አጠጣቻቸው፡፡ ታዲያ መልካም ሴት አይደለችም?
- ❖ ይኸንንም ሲመለከት እግዚአብሔር ለይስሐቅ ያዘጋጃት ጥሩ ልጃገረድ መሆንዋን አወቀ፡፡
- ❖ ከዚች ልጃገረድ ጋር እንዲገናኝ ስላደረገው እግዚአብሔርን አመስግነው እጅግም ደስ አለው፡፡
- ❖ ወዲያውኑም የማን ልጅ ነሽ? ብሎ ጠየቃትና የአብርሃም ወገን መሆንዋን አወቀ፡፡
- ❖ እርሷም የአብርሃምን አገልጋይ ወደ ቤቷ አምጥታ ከላባ ጋር አገናኘችው፡፡ የሆነውንም ሁሉ አስረዳችው፡፡
- ❖ ላባም እግዚአብሔር መልካም ሚስት ለይስሐቅ እንዲሰጠው አገልጋዩ የጸለየውን ጸሎት እና የሆነውን ነገር ሁሉ ከሰማ በኋላ ርብቃ ለይስሐቅ ሚስት ትሆን ዘንድ ወዲያውኑ ፈቀደ፡፡
- ❖ አገልጋዩም ያመጣውን ጌጥና ጥሩ ስጦታ በሙሉ ለርብቃ ሰጠ፡፡

- በማለዳም ተነስተው ርብቃና አገልጋዩ በአንድ ላይ ሆነው ከይስሐቅ ጋር ሲገናኙ ወጡ።
- ርብቃ እግዚአብሔርን አብዝታ የምትወድ እጅግ መልካም ሴት ስለ ነበረች ይስሐቅ ሲገናኛት እግዚአብሔር ፍጹም ሚስት እንደ መረጠለት ተረዳ።

**ጥያቄ**

1. አገልጋዩ መሥራት የሚገባው ሥራ ምንድር ነበር?
2. አገልጋዩ ለሚሠራው ሥራ እርዳታን ከማን ጠየቀ? እንዴት አድርጎ ጠየቀ?
3. አገልጋዩ ለይስሐቅ የምትሆነውን ሚስት እንዴት አገኘ?
4. ለይስሐቅ የምትሆነው ሚስት ስምዋ ማን ነበር?
5. አገልጋዩ ርብቃ ለይስሐቅ የምትሆን ሚስት መሆንዋን በምን አወቀ?

**ማጠቃለያ**

- ከእግዚአብሔር እርዳታን በምንፈልግበት ጊዜ ሁሉ መጸለይ ይገባናል።
- እግዚአብሔር ማድረግ ወደ ሚገባን ትክክለኛ ሥራ ወደ ተስተከከለም መንገድ ሁሉ ይመራናል።

**ተግባር**

- ለሕፃናት ከገባኤ፣ ከምግብ፣ ከጥናት ... ወዘተ በፊትና በኋላ እንዲጸልዩ ያሳስቡአቸው።
- በቀን የምንጸልይባቸው ሰባት ጊዜያት እንዳሉ ያስረዱአቸው።
- የይስሐቅን፣ የርብቃ፣የአልጋዩንና የግመሎቹን ሥዕል የሚያገኙ ከሆነ ስጦታ አድርገው ይስጡአቸው ወይም በቀለም እንዲቀቡ ያድርጉአቸው።

# ኅዳር

## 11 ኛ ሳምንት
## ያዕቆብና ዔሳው

**ዓላማ**

- የያዕቆብና የዔሳው ታሪክ መማር።

**ጥቅስ**

- "እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ።" ቆላስይስ 3፥9።

**ምንባብ**

- አሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 25 ከቁጥር 25 እስከ 34።

**መግቢያ**

- ያለፈውን ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- መንታ ማለት ምን እንደ ሆነ እንዲሁም በምን እንደሚመሳሰሉና እንደሚለያዩ ለሕፃናት ያስረዱአቸው።
- ርቦአቸው ያውቁ እንደ ሆነ ሕፃናትን ይጠይቁአቸው? ሲርባቸው ምን አደረጉ?
- የጠጉራሙ ዔሳውንና ጠጉር የሌለውን የያዕቆብን ሥዕል አዘጋጅተው ለትምህርቱ መርጃ እንዲሆን ያሳዩአቸው።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**


- ዔሳው በመጀመሪያ የተወለደ ታላቅ ቢሆንም ዔሳውና ያዕቆብ መንትያ ነበሩ። ነገር ግን ዔሳወና ያዕቆብ እጅግ ይለያዩ ነበር።
- ዔሳው በሰውነቱ ላይ ብዙ ጠጉር የነበረው እንስሳትን የሚያድን አዳኝ ነበር።
- ያዕቆብ በሰውነቱ ላይ ጠጉር ያልነበረው ብዙውንም ጊዜ ቤት መሆን የሚመርጥ ነበር።
- አንድ ቀን ዔሳው አደን ውሎ ደክሞትና ርቦት ወደ ቤት መጣ።
- ወደ ቤቱም ሲገባ ያዕቆብን ጥሩ የምስር ወጥ ሲሰራ አገኘው።
- ዔሳውም ወደ ምግቡ አየና እጅግ በጣም ጣፋጭ እንደ ሆነ ተረዳ። አሽተተውም ከረሃቡም ለመገላገል ፈለገ።
- ያዕቆብም ከሠራው የምስር ወጥ እንዲሰጠው ጠየቀው።
- ያዕቆብም በመጀመሪያ ታላቅነትህን ሽጥልኝ በአንተ ፋንታ እኔ ታላቅ ልሁን ብሎ ዔሳውን ጠየቀው።
- ዔሳውም እኔ በረሃብ ልሞት ነኝ ታላቅነቱ ለእኔ ምንድር ናት?ውሰዳት አለው።
- ያዕቆብም በመጀመሪያ ማልልኝ ብሎ ዔሳውን ጠየቀው ዔሳውም ማለለት።
- ያዕቆብም ለዔሳው የምስር ወጥ ሰጥቶ የዔሳውን ታላቅነት ወስዶ እንደ ታላቅ ልጅ ሆነ።
- ዔሳውም እስኪጠግብ ድረስ እንጀራን በምስር ወጥ በላ።
- ከዚያ በኋላ ዔሳው ታላቅነቱ ተወስዶበት ለታላቅ ልጅ የሚደረገውም ልዩ ስጦታ ሁሉ ሳይደርሰው ቀረ።

**ማጠቃለያ**

- እግዚአብሔር እንደ ዔሳው ልዩ በረከት ሲሰጠን በጥንቃቄ ልንጠብቀው፣ ልንደሰትበት ልናሳድገው ያስፈልገናል።

**ተግባር**

- ምስር አምጥተው ለልጆች ያሳዩአቸው። እነርሱም በእጃቸው አድርገው ምስሩን ይመልከቱ።
- የዔሳውን ሥዕል አዘጋጅተው ጠጉር የሚመስል ነገር በሥዕሉ ላይ እንዲያደርጉ ይርዱአቸው።



ያዕቆብና ዔሳው

## 12 ኛ ሳምንት
## ዮሴፍና የንጉሡ ሕልም

ዓላማ

❖ እግዚአብሔር ዮሴፍን እንዴት እንደረዳው መማር።

ጥቅስ

❖ "እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበር።" ኦሪት ዘፍጥረት 39፥2።

ምንባብ

❖ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 41 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ።

መግቢያ

❖ ያለፈውን ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
❖ ሕልም ማለት ምን እንደሆነ የሚያውቁ ከሆነ ሕፃናትን ይጠይቁአቸው።
❖ የሚናገሩት ሕልም ካላቸው ሕፃናትን ይጠይቁአቸው።
❖ የሰባት የወፈሩና የሌሎች ሰባት የከሱ ላሞች ሥዕልና እንዲሁም የሰባት መልካም የበቆሎ ተክሎችና የሰባት የጠወለጉ የበቆሎ ተክሎች ሥዕል አዘጋጅተው የትምህርቱ መርጃ አድርገው ያሳዩአቸው።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

❖ በአንድ ወቅት የግብፅ ንጉሥ ተኝቶ ሕልም አለመ።
❖ በመጀመሪያ ሰባት የወፈሩ ላሞችና እነርሱንም ተከትለው ሰባት የከሱ ላሞች ከወንዝ ሲወጡ በሕልም አየ።
❖ እነዚያም የከሱ መልካቸው የማያምር ላሞች ወፍራሞቹንና መልካቸው የሚያምሩትን ላሞች በሉአቸው።
❖ ንጉሡ ያየው ሕልም ትርጉም ምን እንደሆነ አላወቀም።
❖ በሁለተኛውም ቀን ንጉሡ ተኝቶ ሰባት የሚያምሩና መልካም የሆኑ እሸቶች ሲወጡ አየ።
❖ ከዚያም በኋላ በነፋስ የተመቱ የጠወለጉ ሰባት እሸቶችን አየ።
❖ በነፋስ የተመቱትና የጠወለጉት እሸቶች የሚያምሩትንና የዳበሩትን እሸቶች ሲውጡአቸው አየ። ትርጉሙን ስላላወቀው ንጉሡ ተጨነቀ።
❖ ንጉሡ ሕልሙን የሚተረጉምለት ሰው ፈጽሞ አጣ። በመጨረሻም ዮሴፍን አገኘው።
❖ እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ስለ ነበር ሕልሙን የሚተረጉምበት ችሎታ ሰጠው።
❖ ለንጉሡም የሕልሙን ትርጉም ሁሉ ነገረው።
❖ ዮሴፍም በግብፅ ምድር ሁሉ ላይ ብዙ ምግብ ፍሬፍሬ አትክልትና ጥራጥሬ የሚኖርበት ጥጋብ የሚሆንባቸው ሰባት ዓመታት ይመጣሉ ብሎ ለንጉሡ ነገረው።
❖ ነገር ግን እነዚህ ሰባት ዓመታትን ተከትለው ዝናብ የማይኖርባቸው እህል ሁሉ የማይበቅልባቸው ሰባት የረሃብ ዓመታት ደግሞ ይመጣሉ አለው።
❖ ዮሴፍም ንጉሡን በሰባቱ የጥጋብ ዘመናት ለሰባቱ የረሃብ ዘመናት የሚሆን ምግብ በጎተራ እናከማች አለው።
❖ ንጉሡም በዮሴፍ ሐሳብ በጣም ደስ አለው።
❖ ንጉሡም ከራሱ ቀጥሎ ያለ ታላቅ ሰው አድርጎ ዮሴፍን በግብፅ ሾመው።
❖ ዮሴፍ ለሰባቱ የረሃብ ዓመታት የሚሆን ምግብ እየሰበሰበ ግብፃውያንን ረዳቸው።
❖ የዮሴፍም ዕቅድ መልካም ሆነ። ግብፃውያንም ለሰባቱ የረሃብ ዓመታት የሚሆን በቂ ምግብ አከማቹ።
❖ ንጉሡና ግብፃውያንም በተመረጠ ሐሳቡ የተነሣ ዮሴፍን እጅግ አመሰገኑት።

**ጥያቄ**


1. ንጉሡ የሚኖረው በየት ሀገር ነበር?
2. ያለመው ሕልም ምንድን ነበር?
3. ስለ ሕልሙ ዮሴፍ የሰጠው ትርጉም ምንድን ነበር?
4. የሕልሙን ፍቺ ከተናገረ በኋላ ዮሴፍ ምን ሆነ?
5. ለዮሴፍ ታላቁን ሐሳብ የሰጠው ማን ነው?

**ማጠቃለያ**

- እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር እንደ ነበር ከእኛም ጋር አለ።
- ራሳችንንና ሌሎችንም መርዳት የሚያስችል ሐሳብ እግዚአብሔር ይሰጠናል ያፈልቅልናል።

**ተግባር**

- ሕፃናቱ የተማሩትን ታሪክ በድራማ መልክ ተዘጋጅተው እንዲሠሩት ያድርጉአቸው።



ዮሴፍ ለፈርዖን ሕልሙን ሲተረጉምለት

# 13 ኛ ሳምንት
# ሕፃኑ ሙሴ

**ዓላማ**

- እግዚአብሔር ሕፃኑ ሙሴን ጠብቆ ለነቢይነት እንዳደረሰው እኛንም እንደማይረሳንና ሁልጊዜ ቃል ኪዳኑን የሚጠብቅ መሆኑን መማር፡፡

**ጥቅስ**

- "ከውኃ አውጥቼዋለሁና ስትልም ስሙን ሙሴ ብላ ጠራችው፡፡" ኦሪት ዘጸአት 2፥10፡፡

**ምንባብ**

- ኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ 2 እና 3 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ፡፡

**መግቢያ**

- ያለፈውን ትምህርትና ጥቅስ መከለስ፡፡
- እግዚአብሔር ለዓላማው ሙሴን መረጠው፡፡
- ሙሴ በፈርዖን ቤተመንግሥት ቢያድግም እግዚአብሔር ግን የኖረበትን በረሃ ሁሉ ቤተ መንግሥት አድርጎለታል፡፡
- ሙሴ እስራኤልን ከግብፅ ምድር አውጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዲያስገባቸው የተሰጠው ሥራ ነበረው፡፡

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- እግዚአብሔር ለሙሴ ያዘጋጀው ዕቅድ ነበረው፡፡
- ሙሴ በተወለደ ጊዜ የነበረው የግብፅ ንጉሥ ጨካኝ ነበር፡፡ ንጉሡ ፈርዖን የተወለዱ የእስራኤል ወንዶች ልጆችን ሁሉ መግደል ስለ ፈለገ የሙሴ እናት ሙሴን ለማዳን ፈጠነች፡፡
- ሙሴንም ወስዳ በቅርጫት ውስጥ አድርጋ በወንዝ ላይ ጣለችው፡፡
- የሙሴ እናት ዮካብድ ሕፃኑ ሙሴ የተጣለበትን ቅርጫት ተከትላ እንድትሄድ እህቱ ማርያምን አዘዘቻት፡፡
- የፈርዖን ልጅም በባሕሩ ዳርቻ ሆና ቅርጫቱን አምጥተውላት በቅርጫቱ ላይ የነበረውን መሸፈኛ ስትከፍት ሕፃኑ ሙሴን አየችው፡፡ ወደ ቤተመንግሥትም ወስዳ እንደ ራስዋ ልጅ አድርጋ ተንከባከበችው፡፡
- በፈርዖን ቤተመንግሥት ውስጥ እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር ነበር፡፡
- እግዚአብሔር ወገኖቹን ከግብፅ አውጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዲያስገባቸው ሙሴን ጠራው፡፡
- ፈርዖን ግን የእስራኤልን ሕዝብ ለመልቀቅ የማይፈልግ ጨካኝ ነበር፡፡
- እግዚአብሔርም የተለያዩ ተአምራትን በማድረግ ፈርዖንን አስጨነቀው፡፡
- በፈርዖን ላይ ዝንብ፣ ቅማል፣ በረሮ ... እግዚአብሔር አመጣበት፡፡
- በመጨረሻም የፈርዖን የመጀመሪያ ልጁ ሞተበት፡፡ ያን ጊዜ ፈርዖን የእስራኤልን ሕዝቦች ለቀቃቸው፡፡
- ከዚህም በኋላ እስራኤል ከግብፅ ወጥተው ቀይ ባሕርን ሲሻገሩ ፈርዖንና ሠራዊቱ ሁሉ በባሕር ሰጥመው ቀሩ፡፡
- እግዚሐብሔር ሕዝቦቹን በበረሃ ሲጓዙ ከሰማይ መና እያወረደ መግቦአቸዋል ውኃም እያፈለቀ አጠጥቶአቸዋል፡
- በኋላም እኛ እስከ ዛሬ ድረስ የምንጠብቀውን አሥርቱን ትዕዛዛት ለሙሴ እግዚአብሔር ሰጠው፡፡

**ማጠቃለያ**

- ሕፃኑ ሙሴን ከወንዝ ውስጥ ያወጣው ማን ነበር? ፈርዖን በእስራኤል ላይ ክፉ የሆነው ለምን ነበር?

**ተግባር**

- የፈርዖን ልጅ ሙሴን ከባሕር ስታወጣው፣ ሙሴ በፈርዖን ቤት ሆኖ፣ እስራኤል የቀይ ባሕርን ሲሻገሩ እና አሥርቱ ትዕዛዛት የሚገኙበትን ሁለቱን ጽላቶች ሙሴ ከእግዚአብሔር ሊቀበል የሚያሳዩ ሥዕሎችን አዘጋጅተው ቀለም እንዲቀቡአቸው፣ እንዲመለከቱአቸው ወይም በስቲከር መልክ እንዲለጥፉአቸው ያድርጉ፡፡



ሕፃኑ ሙሴ ከባሕር ተጥሎ ሲገኝ

## 14 ኛ ሳምንት

## ባሕሩን መሻገር

**ዓላማ**

- እግዚአብሔር ሁሉንም ማድረግ የሚችል አምላክ መሆኑ መማር።

**ጥቅስ**

- "እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል።" ኦሪት ዘጸአት 14፥14።

**ምንባብ**

- ኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ 13 እና 14 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ።

**መግቢያ**

- ያለፈውን ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- ለትምህርቱ ተስማሚ የሆኑ ሥዕሎችን ያዘጋጁ።
- ባሕር ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ ሕፃናቱን ይጠይቁአቸው።

**ጥያቄ**

- ሰው ያለ ጀልባ ባሕርን መሻገር ይችላል?
- በባሕር ውስጥ ምን አለ?
- ከባሕር የሚመጣው ውሃ ጣፋጭ ነው ወይስ ጨው ጨው የሚል?

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- በአንድ ወቅት ፈርዖን የሚባል በግብፅ የነገሠ ንጉሥ ነበር።

**ጥያቄ**

1. የንጉሡ ስም ማን ነበር?

- የእስራኤል ሕዝቦች እግዚአብሔርን እንዲያመልኩና ከግብፅም መውጣት እንዲችሉ አይፈቀድላቸውም ነበር።
- ከብዙ ተአምራት በኋላ ንጉሡ የእስራኤል ሕዝቦችን ለቀቃቸው።

**ጥያቄ**

1. የእግዚአብሔር ሕዝቦች የተባሉት እነማን ናቸው?

- ሙሴ የእስራኤል ሕዝቦች ነፃ በመውጣቸው ደስ አለው።
- የነበራቸውን ብር፣ወርቅ፣ ዶሮዎች፣ ፍየሎች፣ ጥንቸሎች እና ንብረታቸውንና ልብሳቸውን ሁሉ ሰብስበው ከግብፅ ለመውጣት ተዘጋጁ።
- ግብፅንም ለቅቀው ሲወጡ ሌሊት በእሳት ቀን በደመና ይመራቸው የነበረውን እግዚአብሔርን ተከትለው ተጓዙ።
- በመጨረሻ ቀይ ባሕር ፊት ለፊት ደረሱ።

**ጥያቄ**

1. ቀይ ባሕር ስፋቱ ምን ያህል ነበር?

- ቀይ ባሕር በጣም ትልቅ ሰፊ ባሕር ነበር። የእግዚአብሔርም ሕዝቦች እንዴት አድርገው ባሕሩን እንደሚያቋርጡ አያውቁም ነበር።

**ጥያቄ**

1. ባሕሩን ሊሻገሩ የሚችሉበትን ዘዴ ታውቃላችሁ?

- ልጆች የሚሰጡትን መልስ ይስሙአቸው።
- ፈርዖን ከሠራዊቱ ሁሉ ጋር መማሪያውን ታጥቆ እስራኤላውያን የበለጠ ለማስጨነቅ ተከተላቸው።

**ጥያቄ**

1. እስራኤላውያን አሁን ምን ማድረግ አለባቸው?


- ❖ እግዚአብሔር ሙሴንና ሕዝቡን ሁሉ እንዳይፈሩ ነገራቸው።
- ❖ እግዚአብሔርም ሙሴን በትሩን በባሕሩ ላይ አሳርፍ አለው፡
- ❖ ሙሴም በትሩን በባሕር ላይ ሲያሳርፈው ባሕሩ መሐል ለመሐል ለሁለት ተከፈለ።
- ❖ ውኃውም በሁለት በኩል እንደ ግድግዳ መሐሉ ደግሞ እንደ ደረቀ መሬት ሆነ። ሥዕል ወይም ፊልም አዘጋጅተው ባሕሩ ሲከፈል ያሳዩአቸው።
- ❖ የእግዚአብሔርም ሕዝቦች ደስ ብሎአቸው ውሃው ምንም ሳያረጥባቸው ባሕሩን አቋረጡ።
- ❖ ንጉሡ ፈርዖንና ሠራዊቱ እስራኤልን ተከትለው ወደ ባሕሩ ገቡ፤ ሙሴ ግን በትሩን በውኃው ላይ አደረገው። ውኃውም በንጉሡና በሠራዊቱ ላይ ተመለሰባቸውና አሰጠማቸው።
- ❖ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ግን በሌላኛው የባሕሩ ዳርቻ ደህና ሆነው ተሻገሩ።

**ማጠቃለያ**

- ❖ እግዚአብሔር ልጆቹ የሚድኑበትንና የሚጠበቁበትን መንገድ ያዘጋጃል።
- ❖ የእግዚአብሔርን ልጆች ሊጎዳቸው የሚችል የለም።

**ተግባር**

- ❖ ለሕፃናት ታሪኩን የተመለከተ ፊልም ያሳዩአቸው ታሪኩን የተመለከተ ሥዕል ይስጡአቸው።
- ❖ የባሕሩን፣ የሰማዩንና፣ በባሕሩ ውስጥ ያልፉ የነበሩትን የእስራኤልን ሕዝቦች ሥዕል አዘጋጅተው በከለር እንዲቀቡ ያድርጉአቸው።



በእግዚአብሔር ኃይል ባሕሩ ለሁለት ተከፍሎ እስራኤላውያን በደረቅ መንገድ ሲሻገሩ

## 15 ኛ ሳምንት
## የቃል ኪዳኑ ታቦት

**ዓላማ**

- ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት መማር::
- በቃል ኪዳኑ ታቦት ውስጥ ባለው በጽላቱ ላይ ስለ ተጻፉት አሥርቱ ትዕዛዛት መማር::

**ጥቅስ**

- "በዚያም ከአንተ ጋር እገናኛለሁ ::" ኦሪት ዘጸአት 25፥22::

**ምንባብ**

- ኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ 25 ከቁጥር 10 እስከ 22::

**መግቢያ**

- ያለፈውን ትምህርትና ጥቅስ መከለስ::
- የጽላቱንና የኪዳኑን ታቦት ሥዕል ያሳዩአቸው:: በቤተክርስቲያን ታቦት ሲወጣ ተመልክታችሁ ታውቃላችሁ ?
- እግዚአብሔር አሁን በምን እንደሚያነጋግረን ይጠይቁአቸው ዛሬም በታቦቱና በቅዱስ መጽሐፍ አማካኝነት እግዚአብሔር ያነጋግረናል::

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- ከረጅም ዘመናት በፊት እግዚአብሔር ሙሴን ለተሰበረው ምትክ አድርጎ ጽላት እንዲሠራና በቃል ኪዳኑ ታቦት ውስጥ እንዲያኖረው በኋላም በታቦቱ አማካኝነት እንደሚያነጋግረው ነገረው::
- እግዚአብሔር በደመና ተሸፍኖ በታቦቱ ላይ ሆኖ ሙሴን ያነጋግረው ነበር::
- የቃል ኪዳኑ ታቦት ከእንጨት የተሠራ ሆኖ ከውስጥና ከውጭ ወርቅ የለበሰ ነበር::
- በቃል ኪዳኑ ታቦትም ውስጥ አሥርቱ ትእዛዛት የተጻፉባቸው ሁለት ጽላቶች ነበሩ:: አሥርቱ ትእዛዛት እነማን እንደሆኑ ይዘርዝሩላቸው::
- በታቦቱም የላይኛ ክፍል የሥርየት መክደኛ ነበረ::
- የሥርየት መክደኛውም በሁለት የኪሩቤል ሥዕል ተከብቦ ነበር::

  **ጥያቄ** 1. ታቦቱ የተከበበው በምን ነበር?

- እግዚአብሔር በሙሴንና በአሮን አማካኝነት ሕዝቡን ሁሉ ማነጋገር ሲፈልግ ደመና ለብሶ በሥርየት መክደኛው ላይ በሁለቱ የኪሩቤል ሥዕል መካከል ሆኖ ያነጋግራቸው ነበር::
- ዛሬም በቤተክርስቲያናችን በመንበሩ ላይ የሚገኘው ይህ የቃል ኪዳን ታቦት ነው::
- ይህም የቃል ኪዳን ታቦት ዛሬ በኢትዮጵያ በአክሱም ከተማ በምትገኘው የእመቤታችን ቤተክርስቲያን ውስጥ ይገኛል::

**ማጠቃለያ**

- እግዚአብሔር ሁልጊዜ ሊያነጋግረን ይፈልጋል::
- የእስራኤልን ሕዝቦች በታቦቱ ላይ ሆኖ ያነጋግራቸው ነበር ዛሬም በታቦቱ ላይ ሆኖ እንዲሁም ከታቦቱ በተጨማሪ በመጽሐፍ ቅዱስ ያነጋግረናል:: እኛም በጸሎት ሁል ጊዜ ልናነጋግረው ያስፈልገናል::

**ተግባር**

- ልጆች የታቦቱንና የጽላቱን ሥዕል እንዲመለከቱ ያድርጉአቸው::
- በየቀኑም ወላጆቻቸው አንድ አንድ ምዕራፍ እንዲያነብቡላቸው ይሁን::
- ሁልጊዜ ታቦት ሲወጣ በቤተክርስቲያናችን ተገኝታችሁ ነጭ ልብስ ለብሳችሁ እልል እያላችሁ ከካህናትና ከወላጆቻችሁ ጋር እየዘመራችሁ አክብሩ::



አሥርቱ ትእዛዛት የተጻፉበት የእግዚአብሔር ጽላት

# ታኅሣሥ

## 16 ኛ ሳምንት

# እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምና መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል

**ዓላማ**

- ስለ ቅዱስ ገብርኤል ብሥራት መማር።
- እንደ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በእግዚአብሔር መታመን እንደሚገባን መማር።

**ጥቅስ**

- "ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ።" ሉቃስ 1፥28።

**ምንባብ**

- የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ከቁጥር 26 እስከ 38።

**መግቢያ**

- ያለፈውን ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- ስለ መላእክት የሚያውቁ ልጆችን ይጠይቁአቸው።
- መላእክት ሥራቸው ምንድር ነው? ብሥራት ማለት ምን ማለት ነው?
- መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለእመቤታችን ሲያበስራት የሚያሳየውን ሥዕል ያዘጋጁ።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ እየዘመረች ሐርና ወርቅ አስማምታ ትፈትል ነበር።
- በድንገት ቅዱስ ገብርኤል ተገለጠላት።
- ቅዱስ ገብርኤልን ወደ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የላከው እግዚአብሔር ነበር።
- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም ቅዱስ ገብርኤልን ስታየው ተደነቀች።
- ቅዱስ ገብርኤልም "ደስታ ይገባሻል እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ቢሆን ባለሟልነት አግኝተሻልና፣ እነሆ ትጸንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል መንግስቱም ለዘላለም አያልፍም አላት።"
- እመቤታችንም "ይህ እንዴት ይደረጋል?" አለችው።
- ቅዱስ ገብርኤልም "መንፈስ ቅዱስ ይጠብቅሻል አብም ያድርብሻል ይህ የሚወለደውም ከሦስቱ ቅዱስ አንዱ ቅዱስ ነው ። እነሆ ዘመድሽ ኤልሳቤጥ ከሸመገለች በኋላ ጸንሳለች ይኸም ስድስት ወር ሆኖታል። መካን ሲሏት ነበር ። ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?" አላት።
- እመቤታችንም "እኔ ለእግዚአብሔር ባርያው ነኝ እንደ ቃልህ ይደረግልኝ ። " አለችው።

**ማጠቃለያ**

- ቅዱስ ገብርኤል ለእመቤታችን ስሙ ኢየሱስ የሚባል ሕፃን ትወልጃለሽ ብሎ የምስራች ነገራት።
- እመቤታችንም ለእግዚአብሔር የተመረጠች ስለ ነበረች የቅዱስ ገብርኤልን ቃል ሰምታ እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን የነበረውን በእርሷም በኩል ያለውን ዕቅድ ተቀበለች።

**ተግባር**

- ሕፃናት እንደ ቅዱስ ገብርኤልና እንደ እመቤታችን ሆነው በድራማ መልክ በተግባር የተማሩትን ትምህርት እንዲያሳዩ ያድርጉአቸው።
- ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን እንዳበሰራት የሚያሳየውን ሥዕል አዘጋጅተው ልጆች ወደ ቤታቸው እንዲወስዱ ያድርጉአቸው።
- የቅዱስ ገብርኤልን ብሥራት ሥዕል አዘጋጅተው በቀለም እንዲቀቡ ያድርጉአቸው።



መልአከ ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችን በቤተመቅደስ ሆና ሲያበስራት

## 17 ኛ ሳምንት

## እመቤታችን ድንግል ማርያም ቅድስት ኤልሳቤጥን ጎበኘቻት

**ዓላማ**

- ለሌሎች ደግነትን ማሳየት እንደሚኖርብን መማር።

**ጥቅስ**

- "ጽንሱ በማኅፀንዋ ውስጥ ዘለለ።" ሉቃስ 1፥41።

**ምንባብ**

- የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ከቁጥር 39 እስከ 56።

**መግቢያ**

- ያለፈውን ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- ቅዱስ ገብርኤል ስለ ቅድስት ኤልሳቤጥ ለእመቤታችን የነገራት ምን ነበር?
- ባለፈው ጊዜ የተጠቀሙበትን ሥዕልና ከተቻለ የቅድስት ኤልሳቤጥን ሥዕል ያዘጋጁ።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- እመቤታችን ዘመድዋ ቅድስት ኤልሳቤጥ መጽነስዋን ስታውቅ ፈጥና ልትጎበኛትና ልትረዳት ሄደች።
- እመቤታችን ቅድስት ኤልሳቤጥን ለመጎብኘት ወደ ተራራ ላይ ወጣች።
- ቅድስት ኤልሳቤጥ እመቤታችንን አስቀድማ ስትመለከታት በጣም ደስ ብሎአት ልትገናኛት ሮጠች።
- እምቤታችንም ኤልሳቤጥን እንዴት ነሽ? ስትላት በኤልሳቤጥ ማኅፀን ውስጥ የነበረው ጽንስ ደስ ብሎት ዘለለ።
- ቅድስት ኤልሳቤጥ እመቤታችን የጌታ እናት መሆኗንና ጌታችንም ከርሷ የሚወለድ መሆኑን ታውቅ ነበር።
- የእግዚአብሔር እናት እመቤታችን ልትጎበኛትና ልትንከባከባት በመምጣትዋ ቅድስት ኤልሳቤጥ በጣም ደስ አላት።
- ቅድስት ኤልሳቤጥ እመቤታችንን ወደ ቤትዋ እንድትገባ ከጋበዘች በኋላ ባልዋ ካህኑ ዘካርያስ የእግዚአብሔርን መልአክ ማየቱን ነገረቻት።
- ዘካርያስ ዛሬ በቤተክርስቲያናችን እንዳሉት ቀሳውስት ነበር።
- በቤተ መቅደስ ሲጸልይ ሳለ የእግኢአብሔርን መልአክ አየ።
- ሚስቱ ኤልሳቤጥም ስለ ምትወልደው ሕፃን መልአኩ ለካህኑ ዘካርያስ ነገረው።
- ካህኑ ዘካርያስ ግን የመልአኩን ቃል ስላላመነ ሕፃኑ ዮሐንስ እስኪወለድ ድረስ ዲዳ ሆነ መስማትም ሆነ መናገር ተሳነው ብላ ነገረቻት።
- እመቤታችንም ስለ ቅድስት ኤልሳቤጥና እርስዋም ስለ መጽነስዋ እጅግ ደስ አላት።
- ሁለቱም ሕፃናት ጌታችንና ዮሐንስ በመገናኘታቸውም ደስ አላቸው። ቅዱስ ዮሐንስም በማኅፀን ሳለ ዘለለ።

**ማጠቃለያ**

- እመቤታችን ዘመድዋን ኤልሳቤጥን ለመጎብኘትና ለመንከባከብ ረጅም መንገድ ተጉዛለች።
- እኛም ሌሎችን ለመንከባከብ ለመርዳት እንደዚህ ደግነት ማሳየት ይገባናል።
- ቅድስት ኤልሳቤጥ እመቤታችን ልትጎበኛት በመምጣትዋ እጅግ ደስ ብሎአት ነበር። እኛም ጓደኞቻችን ሊጎበኙን ሲመጡ በጣም ደስ ሊለን ይገባል።

**ተግባር**

- ሕፃናቱ የእመቤታችንንና የቅድስት ኤልሳቤጥን ሥዕል አዘጋጅተው በቀለም እንዲቀቡ ያድርጉአቸው።



እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቅድስት ኤልሳቤጥን እንደ ጎበኘቻት

## 18 ኛ ሳምንት

## ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወለደ

**ዓላማ**

- ስለ ሕፃኑ ኢየሱስ የልደት ታሪክ መማር።
- በጌታ ልደት ሐሴት መፍጠር።

**ጥቅስ**

- "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው።" ማቴዎስ 1:23።

**ምንባብ**

- የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 1 እና 2 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ።
- የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 1 እና 2 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ።

**መግቢያ**

- ያለፈውን ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- ሕፃኑ ኢየሱስ በበረት ውስጥ ሆኖ የሚያሳይ ሥዕል ያዘጋጁ።
- የልደትን ትዕይንት በክፍል ውስጥ ለመፍጠር የሚረዱ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት።
- ሥዕሉ ላይ ማን እንዳለ ልጆቹን መጠየቅ።
- በየዓመቱ ለታህሣሥ 28 ወይም 29 ዋዜማ ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ ቅዳሴ በማስቀደስ፣ ቅዱስ ቁርባን በመቀበልና ከካህናቱ ጋር በመዘመር የጌታችንን ልደት እናከብራለን።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**


- እመቤታችን ቅድስት ማርያም ቅድስት ኤልሳቤጥን ጠይቃ ስትመለስ ሆድዋ እየገፋ መጣ።
- ምክንያቱም የጸነሰችው ሕፃን/ኢየሱስ/ በውስጥዋ እያደገ ነበርና።
- ከዚያም ወደ ምትኖርበት ሥፍራ ተመለሰች። እዚያም ስትደርስ የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰ።
- እመቤታችን ማርያምና ቅዱስ ዮሴፍ ሕፃኑ ኢየሱስ የሚወለድበት ቤት ማግኘት አልቻሉም።
- ማንም ሰው ከቤቱ ሊያስገባቸው አልፈቀደም።
- በዚህ የተነሳ ሕፃኑ ኢየሱስ በቤተልሔም በግርግም ውስጥ በከብቶች መሐል ተወለደ።
- በጐቹ ባ... ባ... ባ... ይሉ ነበር። ላሞቹ ደግሞ ሚ... ሚ... ሚ... ይሉ ነበር።
- ሕፃኑ ኢየሱስ ግን ምንም ሳይረበሽና ሳይፈራ ተረጋግቶ ተኝቷል።
- እናቱ ሕፃኑ እንዲሞቀው በጨርቅ ጠቅልላ አስተኝታው ነበር።

**ማጠቃለያ**

- ሕፃኑ ኢየሱስን እንወደዋለን።
- ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኛ በነሳው ሥጋ እኛን መስሎ የመጣው የእግዚአብሔር ልጆች እንዴት መሆን እንዳለብን ሊያሳየን ነው።

**ተግባር**

- ለልጆቹ የእመቤታችን ማርያምን፣ የዮሴፍንና የሕፃኑን ምስል በመቀስ ቆራርጠው በማዘጋጀት ያውጡና በካርቶን ላይ በማጣበቂያ እንዲለጥፉት ይስጡአቸው።
- ልጆቹ የጌታን ልደት ታሪክ በክፍል ውስጥ በድራማ መልክ ያሳዩ።



የጌታችን በከብቶች በረት መወለድ

## 19 ኛ ሳምንት

## እረኞቹና ሰብአ ሰገል

**ዓላማ**

- ሕፃኑ ኢየሱስን ስለ ጎበኙት ሰዎች ታሪክ መማር።
- እረኞቹና ሰብአ ሰገል የኢየሱስን ልደት ሰምተው እንደተደሰቱ መደሰት።

**ጥቅስ**

- "ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን።" ሉቃስ 2፥14።

**ምንባብ**

- የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 1 እና 2 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ።
- የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 1 እና 2 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- ሕፃኑ ኢየሱስ በተወለደበት ጊዜ ከብቶቻቸውን እየጠበቁ የሚያድሩ እረኞቹ ነበሩ።
- መልአኩ ለእረኞቹ ታይቷቸው ሕፃኑ ኢየሱስ መወለዱንና የት ቦታ እንደሚገኝ ነገራቸው።
- ሰማዩም እግዚአብሔርን በሚያመሰግኑና በሚዘምሩለት መላእክት ተሞላ።
- ወድያውኑ እረኞቹ ሕፃኑ ኢየሱስ ዘንድ ሄደው ጎበኙት። ያዩትንም በሙሉ ለሰው ሁሉ ተናገሩ።
- እንዲሁም በምሥራቅ በኩል የሚኖሩ ሦስት የጥበብ ሰዎች /ሰብአ ሰገል/ በሰማዩ ላይ በጣም የሚያበራ ኮከብ አዩ።
- ኮከቡ ታላቅ ንጉሥ መወለዱን የሚያመለክት ነበር።
- ይህን ኮከብ ተከትለው ሕፃኑ ኢየሱስ ወዳለበት ቦታ ደረሱ።
- በጣም ብዙ ተጉዘው ሕፃኑ ኢየሱስን በማግኘታቸው እጅግ በጣም ደስ አላቸው። ለሕፃኑም **ወርቅ፣ እጣንና ከርቤ** ስጦታ አድርገው አበረከቱለት።

**ጥያቄ**

1. ለኢየሱስ ምን ዓይነት ስጦታ ሰጡት?

**ማጠቃለያ**

- ሕፃኑ ኢየሱስን የጎበኘው ሁሉ በጣም ደስተኛ ነው።
- እኛም የሕፃኑ ኢየሱስን ልደት ማክበርና መደሰት አለብን።
- ሁላችንም ከመላእክት ጋር ሆነን "ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን።" ብለን መዘመር ይኖርብናል።

**ተግባር**

- ልጆቹ በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሱትን ገጸ ባህርያት ለብሰው በድራማ መልክ እንዲያሳዩ ያድርጉ።
- በክፍሉ ውስጥ የጌታን ልደት የሚያንጸባርቅ መድረክ እንዲያዘጋጁ ለልጆቹ የተለያዩ ቁሳቁሶች ያቅርቡላቸው።
- የጌታችንን ልደት ነጭ ልብስ በመልበስ፣ ሌሊት ከቤተሰብ ጋር ቤተክርስቲያን በመሄድ ከቤተክርስቲያን ስንመለስም አብረን በመመገብ (ጾም መፍታት) ማክበር ይኖርብናል።



የጥበብ ሰዎች (ሰብአ ሰገል) ለጌታችን ስጦታ ሲያቀርቡ

# ጥር

## 20 ኛ ሳምንት

## ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለወላጆቹ ታዛዥ ነበር።

**ዓላማ**

- ቤተክርስቲያናችንን መውደድና ማክበር እንደሚገባን መማር።
- አባትና እናት የሚሉንን በጎ ነገር ሁሉ መስማት እንደሚገባ መማር።

**ጥቅስ**

- "ይታዘዝላቸውም ነበር።" ሉቃስ 2፥51። "ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ። " ኤፌሶን 6፥1

**ምንባብ**

- የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 2 ከቁጥር 40 እስከ 52።

**መግቢያ**

- ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተጻፈው ጌታችን አሥራ ሁለት ዓመት ሲሆነው ከእመቤታችን ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ለበዓል ሄደው ሲመለሱ ጠፋባቸው።
- አንድ ልጅ ብቻ ያላቸው ወላጆች የልጃቸውን መጥፋት ከሦስት ቀን በኋላ ያስታውሳሉ ብላችሁ ታምናላችሁ?
- ይህ ሁኔታ የተፈጠረው የሃይማኖት በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ ነው።
- በሚኖሩበት አካባቢ በቅርብ የሚገኝ ቤተ መቅደስ አልነበረም።
- በድሮ ጊዜ ብዙ ቤተሰቦች በአንድ ላይ ሆነው ቤተ መቅደስ ለመሄድ በግመል፣ በፈረስና በአህያ ረጅም መንገድ ይጓዙ ነበር።
- ወንዶቹ ከፊት ሆነው ሴቶቹ ይከተሉ ነበር። ልጆቹም በአንድ ላይ ይሰባሰቡ ነበር።
- ስለዚህ ልጆቹ በአንድ ላይ ስለ ሚሆኑ ወላጆቻቸው መኖራቸውን የሚያረጋግጡት ከጉዞ ሲያርፉ ብቻ ነበር።
- ቤተሰቡ ሁሉ ልጆቹ ከሌሎቹ ልጆች ጋር እየተጫወቱ ነው ብሎ ያስብ ነበር።
- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ልጄ ከፊት ከቅዱስ ዮሴፍ ጋር ነው ብላ ገምታለች።
- ቅዱስ ዮሴፍ ደግሞ ኢየሱስ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ይሆናል ብሎ አስቧል።
- በመጨረሻ ግን ከሁለቱም ጋር አለመሆኑን ተገነዘቡ።
- በአይሁድ ዘንድ በኢየሩሳሌም የሚከበሩት ዋና ዋና በዓላት ፋሲካ እና በዓለ ጰንጠቆስጤ ናቸው።
- ለበዓሉ የሚጓዙ ሰዎች ሁሉ በጉዞ ላይ ይጸልዩና ይዘምሩ ነበር።
- ሕዝቡ አእምሮአቸው ተሰብስቦ ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ በዓሉን ለማክበር አዘጋጅተው ይጓዙ ነበር።
- እኛም በመኪና ወደ ቤተክርስቲያን (ገዳማት) ስንሄድ ይኸንን በማድረግ መጓዝ አለብን።
- መጣላትንም ሆነ መጥፎ ነገርን ማሰብ አይገባንም።
- ወደ ቤተክርስቲያን በምንጓዝበት ወቅት በቤተክርስቲያን የተማርናቸውን መንፈሳዊ መዝሙሮች በመዘመር፣ በመጸለይና ደጋግመን ጌታዬ ይቅር በለኝ በማለት ውስጣችን ሰላም እንዲኖረው ማድረግ አለብን።
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህች ዓለም የመጣበት ዋነኛ ምክንያት የሰው ልጆችን ለማዳን ነው።
- ጌታችን ትኩረቱን ሁሉ በዚህ ዓላማ ላይ ነው ያደረገው።
- ሕዝቡ ልማድ ሆኖባቸው ወደ ቤተ መቅደስ ይሄዳሉ እንጂ የሚያስቡት ስለ መሬታቸው፣ እርሻቸው ወይ ከቤተ መቅደሱ ከወጡ በኋላ ስለሚያደርጉት ነገር ነበር።
- ሕዝቡ ሁሉ ጌታችን ኢየሱስ በአሥራ ሁለት ዓመቱ ስለ ነበረው ዕውቀት ይገረሙ ነበር።
- አሥራ ሁለት ዓመት ሲሆነውም እንኳን እንደ አናጢ ልጅ አድርገው ያዩት ነበር።

- ጌታችን ኢየሱስ የሚሰጠው መልስ ሁሉ ትክክል ስለ ነበር እንዴትስ ብሉይ ኪዳን ላይ ያለውን ሁሉ ሊያውቅ ቻለ? ብለው ይጠይቁ ነበር።
- ልጆች በአሥራ ሁለት ዓመት ዕድሜያቸው በብዛት ስለ ጨዋታ ያስባሉ።
- ጌታችን ኢየሱስ ግን በዚህ ዕድሜ ወደ መጣበት ተልዕኮ ማተኮር ጀምሯል።
- ኦርቶዶክሳውያን ልጆች ወላጆቻችሁን ማክበር ይጠበቅባችኋል።
- ከጓደኞቻችን ወይም ከወንድምና እህቶቻችን ብንጣላ እንኳን ክርስቲያን መሆናችንን ተገንዝበን ጌታችን ኢየሱስ እንዳስተማረን እርስ በርሳችን መዋደድ አለብን።
- ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ተሰቀለበት ቀን ድረስ ሁሉንም ወዷል።
- ወላጆቻችን እንደ ሚወዱንና እንደ ሚንከባከቡን ማወቅ አለብን።
- እኛም በበኩላችን ልንወዳቸውና ልናከብራቸው ይገባል።

**ጥያቄ**

1. ጌታችን ኢየሱስ አብሯቸው አለመኖሩን እመቤታችንና ዮሴፍ መቼ አስተዋሉ? /ከኢየሩሳሌም ከተማ ሲመለሱ/
2. ሰዎች በጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተደነቁት በምን የተነሣ ነበር? /በዕውቀቱ/
3. ሕዝቡ በዓል ለማክበር የሄዱባት ከተማ ማን ትባላለች? /ኢየሩሳሌም/
4. በኢየሩሳሌም የሚከበሩ ሁለቱን ዋና ዋና በዓላት ጥቀሱ። /ፋሲካ እና በዓለ ጰንጠቆስጤ/

**ማጠቃለያ**

- ልጆች ጌታችን ኢየሱስ ለእናቱ ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እንደታዘዘው ሁሉ ወላጆቻችሁ የሚሉአችሁን መስማትና መታዘዝ አለባችሁ።

**ተግባር**

- መምህር ለልጆች ሠንጠረዥ አዘጋጅተው ለአባት ወይም ለእናት እንዲሰጡ ያድርጉ። ልጆቹ ታዛዥ በሆኑ ቁጥር አባት ወይም እናት በሠንጠረዡ ላይ ምልክት ያድርጉ።
- በሚቀጥለው ሳምንትም ወላጆቻቸው ምላሽ የሰጡበትን ሠንጠረዥ ልጆች ይዘው እንዲመጡ ያድርጉአቸው።

ምሳሌ        ወላጆች የሚከተለውን ሠንጠረዥ በየወሩ እየሞሉ እንዲልኩልን በትህትና አሳስባለሁ ።

| ቀን | ቤተክርስቲያን ሄደዋል። | ቅዱስ ቁርባን ተቀብለዋል። | ቅዱሳት መጻሕፍትን አንብበዋል። | ቅዳሴ አስቀድሰዋል፤ ጸሎት አድርገዋል። | የታመሙ ወይም የታሠሩ ሰዎችን ጠይቀዋል። |
|---|---|---|---|---|---|
| 22/11/1999 | ✓ | × | ✓ | ✓ | × |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |

## 21 ኛ ሳምንት

## ጥምቀት

ዓላማ

- ጥምቀት ምን እንደሆነ መማር።

ጥቅስ

- "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው።" ማቴዎስ 3፥17።

ምንባብ

- የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ከቁጥር 13 እስከ 18።

መግቢያ

- ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- ልጆች ትምህርቱን በደንብ እንዲረዱት ለማድረግ ሰፋ ባለ ዕቃ ውሃ ያምጡና አንድ ክብደት ያለው ነገር ውሃ ውስጥ ሦስት ጊዜ እየከተቱ ያውጡት።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- የጥምቀት በዓል ጥር 11 ቀን በየዓመቱ ይከበራል።
- በዋዜማው ጥር 10 ቀን ታቦታት ውሃ ወዳለበት በካህናትና በምዕመናን ታጅበው ይወርዳሉ።
- ጥምቀት እግዚአብሔር ወይም ሥላሴ የተገለጡበት በዓል ነው።
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጥምቁ ዮሐንስ ዘንድ ሄዶ ተጠምቋል።
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢያት ስለ ሌለበት መጠመቅ አያስፈልገውም ነበር።
- ነገር ግን እኛ መጠመቅ እንደሚገባን ሊያሳየን ተጠመቀ።
- ክርስቲያን ለመሆን ኦርቶዶክሳዊ ለመባል ለመዳንም መጠመቅ ግዴታ መሆኑን ለማሳወቅ ጌታችን ተጠመቀ።
- መጥምቁ ዮሐንስ ንስሐ ግቡ ተጠመቁ እያለ ይጣራ ነበር።
- ብዙ ሰዎች ወደ እርሱ መጥተው ኃጢአታቸውን ተናዘዙ።
- አንዳንዶቹ አይሁድ ነበሩ ሌሎቹ ደግሞ ቀራጮች ናቸው።
- አንዳንድ የሮም ወታደሮች ጭምር ንስሐ ገብተው ምን ማድረግ ይገባናል ብለው ጠየቁት።
- በትክክለኛው መንገድ እንዲኖሩ፣ እርስ በርሳቸው ክፋት እንዳይሠሩ፣ እንዲሁም ከልክ ያለፈ ቀረጥ ማስከፈል እንደማይገባቸው አስረዳቸው።
- ዮሐንስ ከርሱ በኋላ ከርሱ የሚበልጥ እንደሚመጣ ለሕዝቡ አስተማረ። እርሱ በውሃ እንደሚያጠምቅና ከእሱ በኋላ የሚመጣው ደግሞ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት እንደሚያጠምቃቸው ተናገረ።
- ዮሐንስ በፈለገ ዮርዳኖስ ሰዎችን በማጥመቅና ንስሐ እንዲገቡ በማድረግ ላይ እያለ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እርሱ መጥቶ ተጠመቀ።
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም ኃጢአት የለበትም። ነገር ግን እርሱን የሚከተሉ ሁሉ ትምህርት ይሆናቸው ዘንድ ተጠመቀ።
- ኢየሱስ ክርስቶስ ተጠምቆ ከውሃው ሲወጣ እጅግ በጣም የሚያስደንቅ ነገር ተከሰተ። " ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ ታየ፤እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ።" ማቴዎስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 16 እስከ 17።
- በቤተክርስያናችን ካህናት በውሃው ላይ በመጸለይ አዲስ ተጠማቂዎችን ያጠምቃሉ። ቀድመው የተጠመቁ ምእመናንንም ከቅዳሴ በኋላ ለበረከት ይረጩቸዋል።

**ጥያቄ**


1. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በየት ተጠመቀ? /በዮርዳኖስ ወንዝ/
2. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን ተጠመቀ? /ምሳሌ ለመሆን/
3. መጥምቁ ዮሐንስ ምን ያህል ሰው አጠመቀ? /በጣም በርካታ ሰዎች/

**ማጠቃለያ**

- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው እኛ እሱን ተከትለን እንድንጠመቅና የእግዚአብሔር ልጆች በመሆን ከሚገኘው ስጦታ ተካፋዮች እንድንሆን ነው።

**ተግባራዊ ትምህርት**

- ለጥምቀት በዓል ማስቀደስ አለብን።
- እንደ ፋሲካ፣ ገና (ልደት) ሁሉ ጥምቀት ታላቅ በዓል ነው።
- እነዚህን ታላላቅ በዓላት ስናከብር ብዙ በረከት ከእግዚአብሔር እናገኛለን።
- ሕፃናትና አዋቂዎች ሁላችንም ጥር 11 ቀንም ንጹህና ነጭ ልብስ በመልበስ መዝሙር ባመዘመር ታቦታትን በታላቅ ዝማሬና ደስታ በማጀብ እንዲሁም በጥምቀት ዕለትም ጠበል በመረጨት ይኖርብናል።



ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ዮሐንስ እጅ ሲጠመቅ

# ከጾመ ነነዌ በፊትና በኋላ

## 22 ኛ ሳምንት
## ከነነዌ ጾም በፊት - ዮናስ በመርከብ ላይ

**ዓላማ**

❖ የእግዚአብሔርን ቃል መስማት እንደሚገባን መማር።

**ጥቅስ**

❖ "ዮናስ ይኮበልል ዘንድ ተነሳ።" ትንቢተ ዮናስ 1፥3።

**ምንባብ**

❖ ትንቢተ ዮናስ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ።

**መግቢያ**

❖ ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።

❖ መርከብ አይተው ያውቁ እንደ ሆነ የት እንዳዩም ጭምር ሕፃናትን ይጠይቁአቸው።

❖ የመርከብ ሥዕል እና በመርከቧ ላይ የነበረውን ዮናስን የሚያሳይ ሥዕል ያዘጋጁ።

**የትምርቱ ዝርዝር መግለጫ**

❖ አንድ ቀን እግዚአብሔር ዮናስን ወደ ነነዌ ሰዎች ሄዶ ስለ ክፉ ሥራቸውን እንዲነግራቸው አሊያ ግን የሚቀጣቸው መሆኑን ገልጾ ላከው። ዮናስ ግን እግዚአብሔር ያዘዘውን ሊያደርግ ስላልፈለገ ከእግዚአብሔር ፊት ኮበለለ።

❖ መሮጥ የሚችለውን ያህል ከእግዚአብሔር ለማምለጥ ሮጠ።

❖ ከነነዌ በተቃራኒ አቅጣጫ ረጅም መንገድ የሚሄድ መርከብ አገኘና በመርከቧም ተሳፈረ።

❖ በመርከቧም እየተጓዘ በባሕር መካከል እያሉ እግዚአብሔር ትልቅ ማዕበል አስነሳ።

❖ ማዕበሉ ው ... ው ... ው ... ይል ነበር። መርከቧንም በጣም አናወጣት።

❖ መርከበኞቹ በጣም ደነገጡ እንሰጥማለንም ብለው ፈሩ። ወደ አምላካቸው ጸለዩ ማዕበሉ ግን ው...ው...ው... እያለ ቀጠለ። ማዕበሉ የተቆጣበትንና እንደዚህ የበረታበትን ምክንያት መመርመር ጀመሩ።

❖ እግዚአብሔር የተቆጣው ክፉ ያደረገ አንድ ሰው በመርከባችን ውስጥ ቢኖር ነው አሉ።

❖ ጥፋትን ያደረገው በመርከቧ ውስጥ ያለው ሰው ማን ይመስላችኋል? አዎ ዮናስ ነው።

❖ እግዚአብሔር ያዘዘውን ከማድረግ እምቢ ብሎ እየሸሸ ነበር። ዮናስ ግን ይኸ ሁሉ ሲሆን ከመርከቧ ውስጥ ተኝቶ ነበር። ምንም ነገር አልሰማም። መርከበኛውም ቀስቅሶ ወደ እግዚአብሔር ስለምን አትጸልይልንም? አለው።

❖ ዮናስ ግን ከእግዚአብሔር እየሸሸ ስለ ነበር ለተነሳው ማዕበል ምክንያቱ እኔ ነኝ፤ እግዚአብሔር የተቆጣውም በእኔ ነው ብሎ ነገረው።

❖ ዮናስም እኔን አውጥታችሁ ወደ ባሕሩ ብትጥሉኝ ማዕበሉ ጸጥ ይላል፤ እናንተም ትተርፋላችሁ አላቸው።

❖ እነርሱም ዮናስን ሆድ አድርገው አንስተው ወደ ባሕር ውስጥ ጣሉት። ወዲያውኑ ማዕበሉ ቆመ ባሕሩም ጸጥ አለ።

❖ ዮናስ ታዲያ ምን ሆነ? ሳምንት ዮናስ ወደ ባሕር ከተጣለ በኋላ የሆነውን ስለ ምንማር ሁላችሁም ሳትቀሩ እንድትገኙ ይሁን።

**ማጠቃለያ**

❖ እግዚአብሔር የተናገረውን ስላልሰማ ያዘዘውንም ስላላደረገ ዮናስን ተቆጥቶት ይጓዝበት ወደ ነበረው መርከብ ከፍ ያለ ማዕበል ላከ።

**ተግባር**

❖ ልጆች የዮናስን ታሪክ የተመለከተ መዝሙር እንዲዘምሩና የተጓዘባትን ጀልባ የምትመስል በወረቀት ይስሩ።

❖ ትምህርቱን የተመለከተ ሥዕል አዘጋጅተው በቀለም እንዲቀቡ ያድርጉአቸው።



ነቢዩ ዮናስ በመርከብ ውስጥ ተኝቶ ሳለ

## 23 ኛ ሳምንት

## ከነነዌ ጾም በኋላ - ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ውስጥ

ዓላማ

- እግዚአብሔር ጥፋትን እንኳን ብናደርግ ዘወትር የሚጠብቀን መሆኑን መማር፡፡

ጥቅስ

- "ዮናስም ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በዓሣው ሆድ ውስጥ ነበር፡፡" ትንቢተ ዮናስ 2፥2፡፡

ምንባብ

- ትንቢተ ዮናስ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 22 እስከ ፍጻሜ፡፡

መግቢያ

- በተማሩት ትምህርት በመርከቧ ውስጥ በነበረው ዮናስ ላይ ባለፈው ሳምንት ምን እንደ ሆነና ጥቅሱን ያስታውሱ እንደ ሆነ ይጠይቋቸው፡፡
- ትልቅ ዓሣ ምን እንደ ሆነ? የትልቅ ዓሣ ቀለም ምን ዓይነት እንደ ሆነ? ሌሎች ያዩአቸው ዓሦች ቀለም ምን ዓይነት እንደ ሆነ ይጠይቋቸው፡፡
- እንደ ዮናስ ያሉ ሰዎችን መዋጥ የሚችለውን ትልቁን ዓሣ ምስል አዘጋጅተው በተንቀሳቃሽ ምስል ያሳዩአቸው፡፡

የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ

- ዮናስን በባሕር ውስጥ ከጣሉት በኋላ እግዚአብሔር ትልቅ ዓሣ እንዲውጠው አደረገ፡፡
- ጥርስ ስለ ሌለው ይኸ ትልቅ ዓሣ ዮናስን በሕይወት እያለ ዋጠው፡፡
- ዮናስም በዓሣው ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ቆየ፡፡
- ዮናስም በዓሣው ሆድ ውስጥ በነበሩት ምግቦች ዙሪያውን ተከብቦ ነበር፡፡
- ዮናስ በዓሣው ሆድ ውስጥ ሆኖ በጥቂት በጥቂቱ ይተነፍስ ነበር፡፡
- በዚህ መካከል ዮናስ ምን እያደረገ የነበረ ይመስላችኋል? አዎ ዮናስ ይጸልይ ነበር፡፡
- ከዓሣው ሆድ ውስጥ እግዚአብሔር እንዲያድነው ፈልጎ ይጸልይ ነበር፡፡
- ዮናስ እግዚአብሔር ከዓሣው ሆድ ውስጥ ያድነኛል ብሎ አመነ፡፡
- እግዚአብሔር የዮናስን ጸሎት ሰምቶ ዓሣው ዮናስን እንዲተፋው አዘዘው፡፡
- ዓሣውም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ተቀብሎ በደረቅ መሬት ላይ ዮናስን በሕይወት እያለ ተፋው፡፡
- ዮናስም ከእግዚአብሔር ማምለጥ እንደማይችልና ወደ ነነዌም ሄዶ ሕዝቡን ከጥፋታቸው እንዲመለሱ መንገር እንደሚገባው ተረዳ፡፡ ዮናስም ወደ ነነዌ ሄዶ እግዚአብሔር የነገረውን ለሕዝቡ ነገራቸው፡፡
- ከክፉ ሥራቸው ወደ በጎነት ባይመለሱ እግዚአብሔር ታላቂቱን ከተማቸውን የሚያጠፋት መሆኑን ነገራቸው፡፡
- እነርሱም ክፉ ሥራቸውን ሁሉ ትተው መልካም ሰዎች ሆኑ፡፡ ሦስት ቀንም ሰውና እንስሳቱ ጾሙ፡፡
- እግዚአብሔርም ስለ ክፉ ሥራቸው ይቅር ብሎ ከተማቸውን አዳነላቸው ጠበቀላቸው፡፡

ማጠቃለያ

- እግዚአብሔር ዮናስን በዓሣ ሆድ፤ የነነዌንም ሕዝቦች ከክፉ ሥራቸው መልሶ እንደ ጠበቃቸው ሁሉ እኛንም ይጠብቀናል፡፡

ተግባር

- የዮናስን ታሪክ የሚያሳየውን የቪዲዮ ፊልም አዘጋጅተው ያሳዩአቸው፡፡
- ከተቻለ የዓሣ ሞዴል ወደ መማሪያ ክፍሉ አምጥተው ያሳዩአቸው፡፡
- ታሪኩን የተመለከተ ሥዕል አዘጋጅተው በቀለም እንዲቀቡት ያድርጉአቸው፡፡



ነቢዩ ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ውስጥ ሆኖ ሲጸልይ

# ዐቢይ ጾም

## 24 ኛ ሳምንት

## የተመረጡ ወዳጆች

**ዓላማ**

- ለሕፃናት ስለ አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ማስረዳት::

**ጥቅስ**

- "ሥልጣን ሰጣቸው::" ማቴዎስ 10፥1::

**ምንባብ**

- የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 10 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ::

**መግቢያ**

- ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ::
- የ12ቱን ደቀ መዛሙርት ሥዕል አዘጋጅተው ሕፃናቱ እንዲቆጥሯቸው ያድርጉ::
- ሕፃናቱ እስከ 12 ድረስ እንዴት መቁጠር እንዳለባቸው ያስረዱቸቸው::
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስንት የተመረጡ ወዳጆች እንደ ነበሩት ይጠይቁአቸው?

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱን ሲጀምር ለሥራው አገልጋዮች እንደሚያስፈልጉት ወሰነ::
- ከእናንተ መካከል ጥሩ ወዳጅ ወይም ጓደኛ ያለው ማነው? ስንት ጓደኛ አላችሁ?
- ጌታችንም በሚሄድበት ሁሉ አብረውት የሚሄዱ ወዳጆች መረጠ::
- ጌታችን 12 የተመረጡ ወዳጆች ነበሩት:: እነሱም ደቀ መዛሙርት ይባሉ ነበር::
- አንድ ቀን በባህር ዳርቻ ቆሞ ዓሣ አጥማጆች መረባቸውን ሲያጥቡ ተመለከታቸው::
- ጴጥሮስንና እንድርያስን ጠርቶ "ዓሣ ሳይሆን ሰው እንድታጠምዱ አደርጋችኋለሁ ተከተሉኝ::" አላቸው::
- እነርሱም ወዲያውኑ ጀልባቸውንና መረባቸውን ትተው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ተከተሉት::
- ቀጥሎ ያዕቆብንና ዮሐንስን ጠራቸው፤ እነርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ተከተሉት::
- ጌታችን ጴጥሮስን፣ እንድርያስን፣ ዮሐንስንና ያዕቆብን ጠራቸው::
- ልጆች የደቀ መዛሙርቱን ስም ከመምህሩ ተከትለው ይጥሩ::
- ጌታችን ኢየሱስ ግብር ይሰበስብ የነበረውን ማቴዎስን ተመለከተው::
- ከማቴዎስ ጋር እራት ሊበላ ገባ:: ማቴዎስም ያለውን ገንዘቡን ሁሉ ትቶ ጌታችንን ተከተለው::
- አሁን ጌታችንን ስንት ደቀ መዛሙርት ተከተሉት?
- አዎ አሁን አምስት ናቸው:: እነርሱም ጴጥሮስ፣ እንድርያስ፣ ዮሐንስ፣ ያዕቆብና ማቴዎስ ናቸው ::
- ሌሎችንም እንደገና 12 እስኪሆኑ ድረስ መረጠ::
- ሁሉም የብርሃን ወንጌልን ለመስበክ በጌታችን ለአገልግሎት ተመረጡ::


**ጥያቄ፡-** የጌታችን ወዳጆች ማን ተብለው ተጠሩ? /ደቀ መዛሙርት/

**ማጠቃለያ**

- ማንኛውም ሰው እንደ ጌታችን ጓደኞች (ወዳጆች) አሉት::
- እኛና ጓደኞቻችን እግዚአብሔር የሚወደውን ሥራ ሁል ጊዜ መሥራት ይገባናል::

**ተግባር**

- መምህር ያዘጋጁትን የሐዋርያት ሥዕል ያሳዩአቸው:: ከእርስዎም ቀጥሎ ሕፃናቱ እንዲቆጥሩአቸው ያድርጉ::
- ሕፃናት እያንዳንዳቸው ተነስተው በክፍል ውስጥ ለሚገኙት በሙሉ የጓደኞቻቸውን ስም እንዲናገሩ ያድርጉአቸው::



ጌታችንና ደቀ መዛሙርቱ

## 25 ኛ ሳምንት

## ቅዱስ ጴጥሮስ በውሃ ላይ ተራመደ

**ዓላማ**

- እግዚአብሔር ዘወትር ከእኛ ጋር ስለሆነ መፍራት እንደሌለብን መማር፡፡

**ጥቅስ**

- "አትፍሩ፡፡" ማቴዎስ 14፥26፡፡

**ምንባብ**

- የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 14 ከቁጥር 22 እስከ 32፡፡

**መግቢያ**

- ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ፡፡
- የዛሬውን ትምህርት ለማስተማር ይረዳዎ ዘንድ ለምሳሌ፡- ከፍ ያለ የውሃ ማጠራቀሚያ አዘጋጅተው ውሃ ይሙሉባቸው፡፡
- የጀልባና የሁለት ወንድ አሻንጉሊቶች ምስል ያዘጋጁ፡፡
- አንዱን አሻንጉሊት እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሌላውን እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ አድርገው ይጠቀሙበት፡፡

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- የዛሬው ትምህርታችን ... ሹ ... ሹ ይል በነበረ ጠንካራ ነፋስና በተቆጣ ባሕር መካከል የተደረገውን ታሪክ የሚመለከት ነው፡፡
- የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት በጀልባ በተቆጣው ባሕር ላይ ሆነው ይጓዙ ነበር፡፡
- ደቀመዛሙርቱ ባሕሩን በጀልባ ለማቋረጥ በመንገድ ላይ ነበሩ፡፡
- ነገር ግን ከተቆጣውና ... ሹ ... ሹ ይል ከነበረው የጠነከረ ነፋስና ... ሸው -- ሸው ... ከሚለው ከባድ ማዕበል የተነሳ ደክመውና ፈርተው ነበር፡፡
- በመካከሉ ግን ጌታችን በውሃው ላይ እየተራመደ መጣ፡፡
- ጌታችን ሲመጣ ምን ሆነ ብላችሁ ታስባላችሁ? አዎ ማዕበሉም ሆነ ነፋሱ አላወዛወዘውም ነበር፡፡ ማዕበል ምንድር ነው?
- ደቀ መዛሙርቱም በባሕር ላይ ሲሄድ ተመልክተው ተደነቁ ፡፡ ምትሐትም መሰላቸው፡፡ ምትሐት ምንድር ነው?
- ጌታችንም "እኔ ነኝ አትፍሩ" አላቸው፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስም "አንተ ከሆንክ ወደ አንተ እንድመጣ እዘዝ፡፡" አለ፡፡
- ጌታችንም "ወደ እኔ ና፡፡" አለው፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስም ከጀልባው ወርዶ በውሃው ላይ እየተራመደ ወደ ጌታችን ሄደ፡፡
- ማንኛውም ሰው በውሃ ላይ መራመድ ይችላል? አይችልም፡፡ ጌታችንና እርሱ የፈቀደለት ብቻ ይሄዳል፡፡
- ቅዱስ ጴጥሮስ ዳግመኛ ራሱንና የጠነከረውን ነፋስ እንዲሁም ከባዱን ማዕበል ተመለከተና መፍራት ጀመረ፡፡
- መፍራት ሲጀምር በባሕሩ ውስጥ እየሰጠመ መራመድ አቃተው፡፡
- ጌታችን ግን እጁን ዘርግቶ ይዞ ከውሃው ውስጥ አወጣው እንጂ ቅዱስ ጴጥሮስን ዝም ብሎ አልተመለከተውም፡፡
- ጌታችንም ጴጥሮስን ለምን ፈራህ? ስለፈራህ በውሃ ውስጥ ሰጠምክ አለው፡፡
- ጌታችን ቅዱስ ጴጥሮስን ከውሃ ውስጥ አውጥቶ አብሮት ወደ ጀልባው ሄደ፡፡
- ጌታችንና ቅዱስ ጴጥሮስም ወደ ጀልባዋ ሲደርሱ ነፋሱና ማዕበሉ ቆመ፡፡

**ማጠቃለያ**

- መድኃኔዓለም ከእኛ ጋር ከሆነ ሁልጊዜ ደህና እንሆናለን፡፡
- መድኃኔዓለም ዘወትር ከእኛ ጋር ስለሆነ መፍራት አይገባንም፡፡

ተግባር

- መምህር ሕፃናቱ በውሃ ላይ የሚሄዱ አስመስለው እየተራመዱ ለጓደኞቻቸው እንዲያሳዩ ያደርጓቸው፡፡
- ትምህርቱን የተመለከተ ተንቀሳቃሽ ሥዕል ያሳዩአቸው፡፡
- በቀለም የሚቀቡትን ትምህርቱን የተመለከተ ሥዕል ይሰጡአቸውና ሕፃናቱ እንዲቀቡ ያድርጓቸው፡፡



ቅዱስ ጴጥሮስ በውሃ ላይ ተረምዶ ወደጌታችን ሲመጣ

## 26 ኛ ሳምንት

## በሽተኛው ሰው

**ዓላማ**

- እግዚአብሔር ሕሙማንን ፈውሶ ጤነኛ እንደሚያደርጋቸው መማር::

**ጥቅስ**

- "ተነሳ አልጋህንም ተሸከምና ሂድ::" ማርቆስ 2፥9::

**ምንባብ**

- የማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 2 ከቁጥር 1 እስከ 13::

**መግቢያ**

- ያለፈውን ሳምንት ትምህርት እና ጥቅስ መከለስ::
- ታሪኩን ማስተማር የሚያስችሉ ሥዕሎችና መረጃዎች ያዘጋጁ::
- ረጅም ጊዜ ታሞ የነበረ ሰው ታሪክ የምታውቁ ስንት ልጆች አላችሁ?
- የዛሬ ትምህርት ለመራመድና ለመንቀሳቀስ የሚሸከመው ሰው ስለ ሚያስፈልገው አንድ ሰው ታሪክ ይሆናል::
- በተጨማሪም የታመኑ መልካም ጓደኞቹ ምን ያህል እንደረዱትም እንማራን::

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- ሚስት ወይም ልጅ ያልነበረው አንድ ሰው ነበር::
- ይህ ሰው መንቀሳቀስ ስለ ማይችል ዘወትር እርዳታ ይፈልግ ነበር::
- ጓደኞቹ እና ጎረቤቶቹ ከቦታ ቦታ ተሸክመው ያደርሱትና የሚፈልገውንም ያቀርቡለት ነበር::
- በሕይወቱ ሁሉ በሌሎች ላይ ተደግፎ በዚህ ሁኔታ መኖር ለእርሱ ቀላል አልነበረም:: ጌታችን ሰውን ሁሉ እንደሚረዳና እንደሚፈውስ የሚገልፅ መልካም ዜና ተሰማ::
- ለረጅም ጊዜ የታመሙት ብዙዎች ተፈውሰዋል::
- ብዙዎች በጓደኞቻቸው ወይም በቤተሰቦቻቸው በኩል በተሰጣቸው ምክር የተነሳ ለመዳን ወደ በርካታ የሕክምና ባለሞያዎች ዘንድ ሄደዋል ገንዘባቸውንም ጨርሰዋል::
- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በከተማቸው በቅፍርናሆም መሆኑን የሚገልጽ ዜና ሲሰማ ጓደኞቹ በሙሉ እጅግ ደስ አላቸው:: ጓደኞቹም መሄድና መራመድ ወደ ማይችለው ሰው ሄደው የሚከተለውን ተነጋገሩ::
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በከተማችን ይገኛል:: ወደዚያም ልንወስድህ እንፈልጋን እርሱ ሲነካህ ወዲያው ትፈወሳለህ አሉት::
- እርሱም በርካታ ነገሮችን ሞክሬአለሁ አንዱም ግን መፍትሔ አልሆነኝም አለ::
- ጓደኞቹ ግን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሌሎቹ አይደለም:: ብዙዎቹን ረድቶአቸዋል፤ ሁሉም ወደርሱ እየሄዱ ተፈውሰዋል፤ ኢጋንንትን እንኳን ያወጣል አሉት::
- እርሱም ጓደኞቹ አመሰግናችኋለሁ ከዚህ በኋላ ላስቸግራችሁ አልፈልግም አላቸው::
- አይደለም ብዙዎች ዛሬ እርሱን ለማየት ይሄዳሉ ትምህርቱንም ይሰማሉ፤ ከሕመማቸውም ይፈወሳሉ አሉት::
- እርሱም እንግዲህ ምንም ብዙም አላስቸግራችሁም ብዬ አምናለሁ አላቸውና ተስማሙ::
- ይህ በሽተኛ ሰው አራት ታማኝ ጓደኞች ነበሩት:: እነርሱም ልብስ አልብሰውት በአልጋው ተሸከሙት::
- ከቤትም አውጥተው ይዘውት ሔዱ:: በመንገድ ያገኟቸውን ሰዎች ኢየሱስ የሚገኝበት ቤት የቱ ነው? ብለው ጠቋቸው፤ ሰዎቹም የሚገኝበትን ቤት አቅጣጫ ነገሩአቸው::
- ቤቱም ሩቅ ነበር:: ብዙ ሰዎችም ወደ ርሱ ሲሄዱ በመንገድ ላይ አዩአቸው::
- የቤቱም መግቢያ በጣም ተጨናንቆ ነበር:: ቤቱ ዛሬ ካሉን ቤቶች ጋር ሲነጻጸር በጣም ጠባብ ነበር::

- ቤቱ ከመጥበቡ የተነሳ ጓደኞቹ ይኸን የታመመ ሰው ይዘው መግባት አይችሉም ነበር።

**በዚህም የተነሳ የሚከተለውን ተነጋገሩ**

- አስቀድሜ ነግሬአቸዋለሁ መግባት አንችልም እናንተም ባትደክሙ ይሻል ነበር።
- እነርሱም ተፅግስት ይኑርህ እንጂ ጓደኞችን! እንገባለን ታገስ አሉት።
- የቤቱን ንድፍ (ሥዕል) በመሬት ላይ ሥለው መስኮትና በሮቹን ጨመሩአቸው። ነገር ግን ሲመለከቱ በሮቹም መስኮቶቹም በሰው ተሞልተው ነበር።
- አሁን አንድ ሐሳብ አንዱ ጓደኛቸው መጣለትና በቤቱ ጣራ በኩል ይኽ የታመመ ጓደኛችንን ማስገባት እንችላለን አለ።
- እርሱ ግን አይሆንም እንዴት አድርጋችሁ ወደ ጣሪያው ታወጡኛላችሁ? ወደ ቤቱ ወለልስ እንዴት እደርሳለሁ ይኸ በጣም አስቸጋሪ ነው አላቸው።
- እነርሱም ምንም አታስብ በጣም ቀላል ነው አሉት።
- የታመመው ሰው ዛሬ አምቡላንሶች እንዳሉአቸው ዓይነት አልጋ ነበረው።
- ከአራት መልካም ጓደኞቹ አንዱ መሰላል ወስደን ወደ ጣራው እንውጣ፤ ጣራውንም እንክፈተው፤ አልጋውንም በአራት ማዕዘን አስረን ይኸን ሰው ከአልጋው ጋር በገመድ በተቀደደው ጣራ በኩል በጌታችን ፊት እናውረደው አለ። ያሉትንም አደረጉ።
- በቤቱ የነበሩ ሰዎች በሚቀደደው ጣራ ድምፅና የተቀደደውንም በተመለከቱ ጊዜ ተገረሙ። አልጋውም የታመመውን ሰው ይዞ ወረደ።
- ጌታችን እነዚህን ቅን ልቦና የነበራቸውን ሰዎች ተመልክቶ እምነታቸውን አደነቀ።
- ዝም ብሎ ሰው ይዞ ወደ ጣራ ሊወጣ የሚችል ሰው የለም።
- ጌታችን መራመድ የማይችለውን ሰው ጠርቶ ኃጢአትህ ተሰርዮልሃል ተነሳና ሂድ አለው።
- ሰዎችም ሽባ የነበረውን ሰው ተፈውሶ ሲራመድ አይተው አደነቁ።
- ጌታችን ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ በሽተኛውን ሰው ፈወሰው ።

**ጥያቄ :-** 1. የታመመው ሰው ቤተሰብ ነበረው?


2. ስንት መልካም ጓደኞች ነበሩት?
3. የታመመውን ሰው ጌታችን ዘንድ ለማድረስ የሠሩት ሥራ ቀላል ነበር?
4. የታመመውን ሰው በበሩ ወይም በመስኮቱ በኩል ሳይሆን በጣራ በኩል ስለ ምን አወረዱት?

**ማጠቃለያ**

- ሰዎች በጸሎት ሊረዱን ስለ ሚችሉ በሃይማኖት የሚመስሉን ሲጸልዩልን ደስ ይበለን።
- የአራቱ ሰዎች እምነትና ተግባር መራመድ የማይችለውን ሰው ከጌታችን ጋር እንዲገናኝና እንዲፈወስ ረድቶታል።

**ተግባር**

- እኛም በቤተክርስቲያን ወይም በትምህርት ቤት የምናውቃቸው ሁሉ በታመሙና በተቸገሩ ጊዜ ሁሉ በጸሎት እናስባቸው። በዚህም የተነሳ እግዚአብሔር ይፈውሳቸዋልና።



ጌታችን በሽተኛውን ሰው ሲፈውሰው

## 27 ኛ ሳምንት
## የጠፋው በግ

**ዓላማ**

- እግዚአብሔር ሁልጊዜ ከእርሱ ጋር እንድንሆን የሚፈልግ መሆኑን መማር።
- ስለ ጠፋው በግ ታሪክ መማር።

**ጥቅስ**

- "ካልባዘኑት ይልቅ በእርሱ ደስ ይለዋል።" ማቴዎስ 18፥13።

**ምንባብ**

- የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 18 ከቁጥር 11 እስከ 14።

**መግቢያ**

- ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- ለዛሬው ትምህርት ተስማሚ የሆኑ ሥዕሎችን ያዘጋጁላቸው ።
- ሕፃናቱ በግ የሚያውቁ መሆናቸውን ይጠይቁአቸው። በግ ምን እንደሚመስል ሲጮህ ምን ዓይነት ድምፅ እንዳለው ይጠይቁአቸው ። መባዘን ምንድር ነው ?

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- ዛሬ የምንማረው ፎፎ ስለሚባል ነጭ በግ ታሪክ ነው።
- ፎፎ ከብዙ በጎች ጋር መጫወት የሚፈልግና የሚወድ ደስተኛ በግ ነበር። ፎፎ አባትና እናት በጎች ነበሩት።
- ሌሎቹ በጎች ሁሉ ለፎፎ እንደ ወንድምና እህቱ ነበሩ። በጎቹ በአጠቃላይ 100 ነበሩ።

  **ጥያቄ**

  1. በጠቅላላ ስንት በጎች ነበሩ?
  2. 100 ቁጥርን መጻፍ የሚችል ማነው? ልጆች ወጥተው እንዲጽፉ ያድርጓቸው።

- መልካሙ እረኛ 100ውንም በጎች በደንብ መብላታቸውንና መጠጣታቸውን በመከታተል ይንከባከባቸው ነበር።
- በጎቹንም 1፣2፣3፣..... 100 ብሎ እየቆጠረ ሁሉም መኖራቸውን ያረጋግጥ ነበር።
- አንድ ቀን ሲቆጥራቸው 99 በጎች ብቻ አገኘ። ከ100ው በጎች አንዱ ጠፍቶ ነበር።
- እስኪ ገምቱ የጠፋወ ማን ነበር? ፎፎ ነበር የጠፋው። ፎፎ ከእናቱ፣ ከአባቱና ከእረኛው አምልጦ ጠፍቶ ነበር።
- ሩቅ መንገድ መሄዱንም ሳያረጋግጥና ሳያውቅ ፎፎ በተራራው ሁሉ ብዙ መንገድ ሄደ።
- በጣምም ደከመው። ወደ ሌሎቹ በጎችና ወደ እረኛው የሚመለስበትንም መንገድ ማወቅ አቃተው።
- ፎፎ ስለ ጠፋ በጣም ፈራ ማልቀስም ጀመረ። የበጎቹም እረኛ 99ኙን ትቶ ፎፎን ለመፈለግ ሮጠ።
- በተራራው በቁልቁለት ሁሉ ፎፎን እስኪያገኝ ድረስ ሄደ።
- ፎፎ እረኛውን ሲመለከተው በጣም ደስ አለው። ከዚህም በኋላ የሚያስፈራው እንደሌለ ተሰማው።
- ፎፎ ትክክል ነበር። እረኛው ወደ እናቱና አባቱ ሊመልሰው ይፈልግ ነበር።
- እረኛውም ፎፎን ሲያገኘው በጣም ደስ አለው።
- እረኛው ፎፎን ሲያገኘው በትከሻው ተሸክሞ ሌሎቹ በጎች ወዳሉበት መልሶ አመጣው።
- ሌሎቹም በጎች ፎፎን በእረኛው ትከሻ ላይ ተቀምጦ ሲያዩት በጣም ደስ ብሎአቸው ዘለሉ፤ ፈነጠዙ።
- ፎፎ በመጨረሻ ወደቤቱ ተመልሶ ከእናቱ፣ ከአባቱ፣ ከወንድሞቹና ከእኅቶቹ ጋር መኖር ጀመረ።

**ማጠቃለያ**

- እግዚአብሔር ሁልጊዜ ይቆጣጠረናል።
- ከእርሱ በራቅን ቁጥር ፈልጎ ሌሎቹ በጎች (ልጆቹ) ወዳሉበት ወደ ወደ ቤተክርስቲያን ይመልሰናል ።

ተግባር

- መልካሙ እረኛ በጉን በትከሻው ላይ እንደ ተሸከመ የሚያሳየውን ሥዕል ለሕፃናቱ ይስጡአቸው ።
- ከተቻለ የበግ አሻንጉሊት አዘጋጅተው እንዲጫወቱበትና ፎፎም እንዴት እንደጠፋና እንደተገኘ እንዲያሳዩ ያድርጉአቸው።
- የበግ ሥዕል ያለበት ወረቀት፣ ጥጥና ማጣበቂያ አዘጋጅተው ጥጡን በበጉ ሥዕል ላይ እንደ በግ ጠጉር እንዲለጥፉ ያድርጉአቸው ።



ጠፍቶ የተገኘው በግ

## 28 ኛ ሳምንት
## ታላቁ የእራት ግብዣ

ዓላማ

- ስለ ታላቁ የእራት ዝግጅት ወይም ግብዣ መማር።

ጥቅስ

- "አሁን ሁሉ ተዘጋጅቶአል።" ሉቃስ 14፥17።

ምንባብ

- የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 14 ከቁጥር 15 እስከ 21።

መግቢያ

- ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- ለሕፃናቱ ታላቅ ግብዣ አድርጋችሁ ክፍላቸውን አዘጋጁላቸው።
- ሕፃናቱ ከዚህ በፊት ግብዣ ላይ ተገኝተው የሚያውቁ መሆናቸውን ይጠይቁአቸው። በልደት ግብዣ ላይስ ተገኝተው ያውቃሉ? ተገኝተው የሚያውቁ ከሆነ ምን ያህል ሰዎች በግብዣው ላይ እንደተገኙ ይጠይቁአቸው።

የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ

- ዛሬ የምንማረው እግዚአብሔር ስላዘጋጀውና በርካታ ሰዎችም ስለተጋበዙበት ታላቅ የእራት ግብዣ ታሪክ ነው።
- እግዚአብሔር ለግብዣው ምግብ፣መብራት፣ጌጣጌጥ ወዘተ... ማንኛውንም ነገር አዘጋጅቶ ነበር።
- ግብዣውም የሚደረግበት ሰዓት ደረሰ። አገልጋዮቹንም የተጋበዙትን ሁሉ እንዲጠሩ ላካቸው።
- የመጀመሪያው ተጋባዥ ሰው መሬት ገዝቼ አለሁና ወጥቼ ማየት የግድ ስለ ሚያስፈልገኝ ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ አለ።
- ሁለተኛውም ተጋባዥ አምስት ጥማድ በሬዎች ገዝቼአለሁና ልፈትናቸውም ስለ ምሄድ ይቅር እንድትለኝ እለምናለሁ አለ። ጥማድ በሬዎች ማለት ምንድን ማለት ነው?
- ወደ ሦስተኛውም ሰው ሄደው ቢነግሩት ሚስት አግብቼአለሁ ልመጣም አልችልም አለ።
- አገልጋዮቹም ወደ እግዚአብሔር ተመልሰው አንድ ሰው እንኳን መምጣት አልቻለም ሁሉም ይቅርታ ጠይቀዋል አሉት። በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር በጣም ተቆጣ። እግዚአብሔርም ተቆጥቶ ወደ መንገድ ወጥታችሁ ድሆችንና አካል ጉዳተኞችን አንካሶችንና ዕውሮችን ጥሩ አላቸው።
- አገልጋዮቹም ሄደው እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው ድሆችንና አካል ጉዳተኞችን (አንካሶችንና ዕውሮችን) ቢያመጡም በእግዚአብሔር ቤት ግን ሌሎችንም ሰዎች ማስተናገድ የሚችል ትርፍ ቦታ ነበር።
- እግዚአብሔርም ወደ መንገድ ወጥተው ያገኙትን ሰዎች በሙሉ ወደ ግብዣው እንዲጠሩ ነገሯቸው።
- ወደ መንገድም ወጥተው ቤቱ እስኪሞላ ድረስ ያገኙትን ሁሉ ጋበዙ። የተጋበዙትም ሁሉ ደስተኞች ነበሩ።
- በግብዣው ላይ የነበሩት በሙሉ ታላቅ የደስታ ጊዜ ስላሳለፉ ግብዣው ከተደረገበት መውጣት አልፈለጉም ነበር።
- አስቀድመው የተጋበዙትና ያልመጡት ግን ታላቅ ዕድል አመለጣቸው።

ማጠቃለያ

- እኛ እግዚአብሔር ወደ ጋበዘን ሥፍራ ሁሉ መሄድ ይገባናል።
- ወደ እግዚአብሔር በሄድን ጊዜ የሚጠብቀን እርሱ ያዘጋጀልን ታላቅ ግብዣ አለ።
- በዚያም ታላቅ ደስታና ሐሴት እናደርጋለን። በዚህ ግብዣ ላይ የሚያለቅስም ሆነ የሚያዝን አይኖርም።

ተግባር

- ለሕፃናት የጾም ኬክና የተነፉ ፊኛዎች አዘጋጅተው ግብዣ ያድርጉላቸውና እግዚአብሔር ያዘጋጀውን ግብዣ እንዲረዱ ያድርጉትው። ለእያንዳንዳቸው ወደ ቤታቸው ሲሄዱ የሚወስዱት ፊኛ ይስጡአቸው።

## 29 ኛ ሳምንት
## ጠፍቶ የተገኘው ድሪም

**ዓላማ**

- ጠፍቶ ስለ ተገኘው ሳንቲም ወይም ድሪም መማር።

**ጥቅስ**

- "በእርሱ ተገኙ።" ፊልጵስዩስ 3፥9።

**ምንባብ**

- የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ከቁጥር 8 እስከ 10።

**መግቢያ**

- ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- እስከ 10 መቁጠር የሚችል ማን እንደሆነ ይጠይቁአቸው።
- የተለያዩ (አንድ፣ አምስት፣ አሥር፣ ሃያ አምስትና፣ ሃምሳ) ሳንቲሞችን አሳይተው ስንት ስንት ሳንቲሞች እንደሆኑ ይጠይቁአቸው።
- አሥር ተመሳሳይ መጠን ያላቸውን ሳንቲሞች ለትምህርቱ መርጃ አድርገው ያዘጋጁ።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- በአንድ ወቅት ጌታችን አንድ ታሪክ ለሕዝቡ ነገረ።
- የነገራቸውም ታሪክ አሥር ድሪሞች(ሳንቲሞች) ስለ ነበራት ሴት ነው።
- የነበሯትን ሳንቲሞች አንድ፣ሁለት፣ሦስት.. እያለች ቆጠረች።
- ሴቲቱ ሳንቲሞቿን በጥሩ ቦታ በጥንቃቄ አስቀመጠች።
- በየጊዜውም አንድ፣ሁለት፣ሦስት... እያለች ትቆጥር ነበር።
- ሕፃናቱ ከመምህሩ ጋር ሳንቲሞቹን አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት... እያሉ ይቁጠሩ።
- አንድ ቀን ግን አንድ፣ሁለት፣ሦስት..... እያለች እስከ ዘጠኝ ብቻ ከቆጠረች በኋላ አሥረኛውን አጣችው።
- አሥር ሳንቲሞች ሳይሆን ዘጠኙን ብቻ አገኘች። አሥረኛውን ሳንቲም ወዴት እንደጠፋባት በማሰብ አዘነች።
- በቤቱ ውስጥ ፈለገች ነገር ግን አላገኘችም። በመጨረሻ መብራት አብርታ ቤትዋን በመጥረግ በየቦታው እየተዘዋወረችም አሥረኛውን ሳንቲም እስክታገኝ ድረስ ፈለገች።
- በመጨረሻም አሥረኛውንም ሳንቲም አገኘችው ባገኘችውም ጊዜ እጅግ ተደሰተች።
- ወዳጆችዋንና ጎረቤቶቹዋን ሁሉ ጠርታ የጠፋውን ሳንቲሜን አግኝቻለሁና ደስ ይበላችሁ አለቻቸው።
- ወዳጆችዋና ጎረቤቶችዋም ሁሉ በጣም ደስ አላቸው።

**ማጠቃለያ**

- የጠፋውን ሳንቲምዋን ባገኘች ጊዜ ደስ እንዳላት ሴት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የጠፉ ልጆቹን ሲያገኛቸው ደስ ይለዋል።

**ተግባር**

- ልጆች ለሚቀጥለው ሳምንት አሥር አንድ ዓይነት ሳንቲሞችን አጠራቅመው ወደ አንድ ገዳም ወይም ቤተክርስቲያን ለሚያደርጉት ጉዞ ይዘው እንዲመጡና በዚያም ባለው ሙዳይ ምጽዋት ውስጥ እንዲያኖሩ ያድርጉአቸው።
- በዚህ ሳምንት ወደ ቤተክርስቲያን ወደ ዛሬውም መርሐ ግብር ላልመጡ ልጆች በመርሐ ግብሩ መጨረሻ ላይ ሁሉም ሕፃናት እንዲጸልዩ ያድርጉአቸው።

## 30 ኛ ሳምንት
## ሕፃናት በዕለተ ሆሳዕና ጌታችንን ተቀበሉት

**ዓላማ**

- ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የነገሥታት ንጉሥ መሆኑን መማር፡፡
- ዘወትር ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በደስታ መቀበል እንደሚገባን መማር ወይም መገንዘብ፡፡

**ጥቅስ**

- "በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፡፡" ማቴዎስ 21፥9፡፡

**ምንባብ**

- የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 21 ከቁጥር 1 እስከ 11፡፡

**መግቢያ**

- ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ፡፡
- ጌታችን በአህያ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም የገባበትን ሥዕል ለሕፃናት ለማሳየት ያዘጋጁ፡፡
- ጌታችን ከደቀመዛሙርቱ ጋር የፋሲካን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ዝግጁ ነበር፡፡ ይኸ ጉዞው መሥዋዕት ከመሆኑ በፊት ያደረገው ነበር፡፡
- ሆሳዕና የሕፃናት በዓል ነው፡፡ ሕፃናትም በመዝሙር ያከብሩታል፡፡
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሕፃንነቱ ተጫውቷል፤ ትምህርት ተምሯል «ሕፃናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸውም፡፡» ብሏል፡፡

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- ጌታችን ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ከርሱ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄዱ ጠራቸው፡፡
- ሁለቱን ደቀ መዛሙርትም ጠርቶ "ወደ ቅርብ ከተማ ሄዳችሁ አህያና ውርንጫይቱን ታስራ ታገኙላችሁና ፈታታችሁ አምጡልኝ፡፡ የሚጠይቃችሁም ቢኖር ለጌታ ያስፈልጉታል በሉአቸው፡፡" አላቸው፡፡
- ደቀ መዛሙርቱም የጌታችንን ትዕዛዝ አክብረው አህያይቱንና ውርንጫይቱን አመጡለት፡፡
- ጌታችንም በአህያይቱና በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦባቸው ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ ገባ፡፡
- ጌታችንም ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ አይተው ሕዝቡ ሁሉ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው መናገር ጀመሩ፡፡
- በጎዳናውም ላይ ብዙ ሕፃናት፣ ወንዶች፣ ሴቶች ደስ ብሎአቸው ጌታችንን ሊያዩና ሊቀበሉትም ተሰበሰቡ፡፡
- አንዳንዶች ልብሳቸውን አውልቀው በመንገድ ላይ አነጠፉ፡፡
- ለንጉሥ የሚገባው ነውና ሌሎችም የዘንባባ ዝንጣፊ ወስደው እንደ ምንጣፍ አድርገው በጐዳናው ላይ አነጠፉ፡፡
- ሕፃናት ጌታችንን በማየታቸው በጣም ደስ አላቸው፡፡
- ከሕፃናቱ አንዳንዶቹ በፊቱ ይሮጡ ነበር፡፡ ሌሎቹም ከኋላው "ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ሁሉ የተባረከ ነው፡፡ ሆሳዕና በአርያም፡፡" እያሉ ድምጻቸውን አሰምተው ይዘምሩ ነበር፡፡
- ጌታችንም ከመሞቱ አስቀደሞ ወደ ኢየሩሳሌም የገባበት የመጨረሻ ቀን ይህቺ ዕለት ነበረች፡፡
- ይህችውም ዕለት ዕለተ ሆሳዕና ወይም ጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም የገባበት ዕለት ነበረች፡፡

**ጥያቄ**


- ጌታችን የፋሲካን በዓል ለማክበር ወዴት ይሄድ ነበር?
- ከጌታችን ጋር ወደ ኢየሩሳሌም የሄዱት እነማን ናቸው?
- ጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ በምን ላይ ተቀመጠ?
- ሕዝቡ በጌታችን ፊት በመንገድ ላይ ምን አደረጉ?

**ማጠቃለያ**

- ከካህናት ጋር የሆሳዕናን በዓል ለማክበር፣ ለመዘመር የዘንባባ ዝንጣፊያችሁን በመያዝ በጠዋት ወደ ቤተክርስቲያን መምጣት ይኖርባችኋል።

**ተግባር**

- ለእያንዳንዳቸው ለሕፃናት አንዳንድ የዘንባባ ቅጠል ይስጧቸው።
- ሁሉም ሕፃናት በሁለት መስመር እንዲሰለፉ ያድርጉአቸው።
- እያንዳንዳቸው ሕፃናት በየተራ በሁለቱ መሥመር መካከል የዕለቱን ትምህርት ጥቅስ እየተናገሩ እንዲያልፉ ያድርጉአቸው።
- በዕለተ ሆሳዕና ከሚዘመሩት መዝሙሮች ውስጥ መርጠው አስጠንተው ያዘምሩአቸው።



ሆሳዕና

# ትንሣኤና ከትንሣኤ በኋላ

## 31 ኛ ሳምንት
## ትንሣኤ

**ዓላማ**

- ስለ ጌታችን ትንሣኤ መማር።

**ጥቅስ**

- "ተነሥቶአል እንጂ በዚህ የለም።" ሉቃስ 24፥6።

**ምንባብ**

- ሉቃስ 24 ፥ 1 - 12፤ ማቴዎስ 28 ፥ 1 - 8፤ ማርቆስ 16 ፥ 1 - 8፤ ዮሐንስ 20 ፥ 1 - 10 ።

**መግቢያ**

- ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- ለሕፃናት የትንሣኤውን ሥዕል በማሳየት በሥዕሉ ላይ የሚገኘው እና ከሙታን የተነሳው ማን እንደሆነ ይጠይቁአቸው።
- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥዕሉ ላይ ምን እያደረገ እንደሆነ ይጠይቋቸው።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- ጌታችን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ከሞተ በኋላ ሁለት ባለጠጋ ሰዎች ሥጋውን ወስደው ንጹህና አዲስ በሆነ መቃብር ውስጥ ቀበሩት። የጌታችንን የስቅለት ሥዕል ያሳዩአቸው።
- ጌታችንም በመቃብር ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ቆየ።

  **ጥያቄ**

  1. ጌታችን መቃብር ውስጥ ስንት ቀንና ሌሊት ቆየ?

- እሑድ በማለዳ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምና ሌሎቹም ሴቶች ጥሩ መዓዛ ያለው ሽቶ ይዘው ወደ መቃብሩ ሄዱ። ደርሰውም ባዩት ነገር እጅግ ተደነቁ። ጌታችን በመቃብሩ ውስጥ የለም። የመቃብሩም ድንጋይ ተፈንቅሎ ነበር ። ድንጋዩንም ማን ሊያነሳው ይችላል? ብለው ተገረሙ።
- በመቃብሩም አጠገብ የሚያንፀባርቅ ነጭ ልብስ የለበሱ ሁለት መላእክት አገኙ።
- መላእክቱም ጌታችን ከዚህ በኋላ በዚህ መቃብር ውስጥ አይኖርም አሉአቸው።
- መላእክቱም "እርሱ ሕያው ነው ከዚህ በኋላ በዚህ አይሆንም።" አሉአቸው።
- እነርሱም በጣም ደስ ብሎአቸው ወደ ጌታችን ደቀ መዛሙርት ተመልሰው መላእክቱ የነገሩአቸውን ሁሉ ተናገሩ።

  **ጥያቄ**

  1. መላእክቱ ለሴቶቹ የነገሩአቸው ምን ነበር?

- ልክ በዚህ ሥዕል እንደምታዩት ጌታችን ስለ ተነሣ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ደስ አላቸው።

**ማጠቃለያ**

- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በመቃብር ውስጥ ቆይቶ ከሙታን ተነሥቶአል። ከተነሣ በኋላ አሁንም ሕያው ሆኖ ይኖራል።

**ተግባር**

- የትንሣኤውን ሁኔታ የሚያሳይ ፊልም ያሳዩአቸው።
- የትንሣኤውን ሥዕል ይቀቡ ዘንድ እንዲሁም ሌላ የትንሣኤው ሥዕል ሥጦታ አድርገው ይስጡአቸው።
- ትንሣኤን ነጭ ልብስ በመልበስ፤ ሌሊት ከቤተሰብ ጋር ቤተክርስቲያን በመሄድ ከቤተክርስቲያን ስንመለስም አብረን በመመገብ (ጾም መፍታት) ማክበር ይኖርብናል።

## 32 ኛ ሳምንት
## ጌታችንና ቅዱስ ቶማስ

**ዓላማ**

- ስለ ቶማስ ጥርጥር መማር።

**ጥቅስ**

- "ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን።" ዮሐንስ 20፥27።

**ምንባብ**

- የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 20 ከቁጥር 19 እስከ 29።

**መግቢያ**

- ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- ሕፃናቱን ከሙታን ተለይቶ የተነሣውን የጌታችንን ሥዕል ያሳዩአቸው።
- ሕፃናትን ከእናንተ መካከል በሩና መስኮቱ በተዘጋ ቤት ውስጥ መግባት የሚችሉ ሰው አለ? በማለ ይጠይቋቸው። ስግደት ምን እንደሆነ ያስረዱአቸውና እንዴት እንደሚፈጸም በተግባር እየሰገዱ ያሳዩአቸው።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- የጌታችን ወዳጆች (ደቀ መዛሙርቱ) በጌታችን ተሰቅሎ መሞት አዝነው በአንድ ቤት ውስጥ ተሰብስበ በራቸውን ዘግተው ይጸልዩ ነበር።
- በድንገት ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተዘጋው ቤት ውስጥ በመካከላቸው ተገኘ።
- በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ የተወጉና በብረት የተቸነከሩ እጆቹንና እግሮቹንም ለደቀ መዛሙርቱ አሳያቸው ችንካር ምንድር ነው?
- ሰላም ለእናንተ ይሁን ያላቸው ጌታችን መሆኑን ባወቁ ጊዜ አይተውት እጅግ ደስ አላቸው። ጌታችን ለመጀመሪ ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ ሲታያቸው ደቀ መዝሙሩ ቶማስ ከእነርሱ ጋር አልነበረም።
- ቶማስም ተመልሶ ሲመጣ ጌታችንን ከሙታን ተነስቶ አይተነዋል ብለው ነገሩት።
- ቶማስ ግን "የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጎኑ ካላገባ አላምንም።" አላቸው።
- ከስምንት ቀንም በኋላ ቶማስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሳለ ጌታችን በተዘጋ ቤት ውስጥ ተገለጠላቸው።

**ጥያቄ**

1. ጌታችን ወደ ቤቱ እንዴት ገባ? በመስኮት በኩል? በበር በኩል?

- ጌታችንም ቶማስን ጠርቶ "ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ . . . ያመንክ ሁን እንጂ ያላመንክ አትሁ አለው።"
- ቶማስም አይቶ "ጌታዬ አምላኬ . . .።" ብሎ አምኖ ለጌታችን ሰገደለት።

**ጥያቄ፡-** ልጆች ስግደት ሰግዳችሁ ታውቃላችሁ? ስግደት እንዴት ነው የሚሰገደው?

**ማጠቃለያ**

- ጌታችን ማንኛውንም ነገር ማድረግ ይችላል። በተዘጋ ቤትም ውስጥ በሩን ወይም መስኮቱን ሳይከፍት መግባት ይችላል።
- እኛም ሳናይ የምንሰማውን ሁሉ ማመን አለብን።

**ተግባር**

- ሕፃናት የትንሣኤውን ሥዕል ይቀቡ ዘንድ ይስጡአቸው።
- ለሕፃናት አነስ ብለው የተዘጋጁ የትንሣኤ ሥዕሎችን ወደ ቤታቸው እንዲወስዱ ይስጡአቸው።



ጌታችንና ቅዱስ ቶማስ

## 33 ኛ ሳምንት
## በዓለት ላይ የተሠራው ቤት

**ዓላማ**

- በዓለት ላይ ስለ ተሠራው ቤት ታሪክ ማስተማር፡፡
- የእግዚአብሔርን ቃል መስማትና ማወቅ እንደሚገባ ማስተማር፡፡

**ጥቅስ**

- "አልወደቀም፡፡" ማቴዎስ 7፥25፡፡

**ምንባብ**

- የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 7 ከቁጥር 24 እስከ 27፡፡

**መግቢያ**

- ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ፡፡
- ቤት ከምን እንደሚሠራ ሕፃናትን ይጠይቁአቸው፡፡
- በማይወድቅ ጠንካራ ቤት ወይስ በቀላሉ በነፋስና በዝናብ በሚፈርስ ቤት ውስጥ ነው መኖር ነው የምትፈልጉት? በማለት ሕፃናትን ምርጫቸውን ይጠይቁ፡፡
- የተለያዩ ቤቶችን ሥዕል እያሳዩአቸው ትንሽ ወይም ትልቅ ቤት መሆኑንና አለመሆኑን የቤቱም ቀለም ምን ዓይነት እንደሆነም ይጠይቋቸው፡፡
- ቤትን፣ ዓለትንና፣ አሸዋን ማሳየት የሚችሉባቸውን የመርጃ መሣሪያዎች ያዘጋጁ፡፡

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**


- በአንድ ወቅት ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤት ሲሠሩ ስለ ነበሩ ሁለት ሰዎች ታሪክ ተናገረ፡፡
- አንደኛው ሰው ጥሩ ጥሩ ዕቃዎችን ዞሮ ፈልጐ አዘጋጀ፤ ቤቱንም የሚሠራበት ጠንካራና ምቹ መሬት አሠናዳ፡፡
- ይኸ ሰው ወደ አንድ ቦታ ሄዶ "ይኸ ቤቱን መሥራት የምችልበት ጥሩ ቦታ አይደለም፡፡" አለ፡፡
- ወደ ሌላም ቦታ ሄዶ "ቤቱን በዚህ ቦታ ላይ ብሠራው ቤቱ ይወድቃል መሬቱ ደካማ ነው፡፡" አለ፡፡
- ጠንካራ ዓለታማ ቦታ እስኪያገኝ ድረስ ብዙ ጊዜ ዞሮ ፈለገ፡፡
- በጣም ጠንካራና የተረጋጋ መሬት ሲያገኝ እጅግ በጣም ጥሩ ትልቅ ቤት በዚያ ቦታ ላይ ሠራ፡፡
- ሌላኛው ሰው አሸዋማና በጣም ረግረግ የበዛበት ቦታ አገኝና ቤቱን በዚያው ቦታ ላይ ሠራው፡፡
- ዝናብ ዘነበ ነፋስም ሹ ሹ ሹ (ሸው፣ ሸው) ... እያለ ነፈሰ፡፡
- ሕፃናት የትኛው ቤት እንደሚወድቅና የትኛው ቤት ምንም ሳይሆን መቆየት እንደሚችል ገምቱ፡፡
- በዓለት ላይ የተገነባው ቤት ምንም አልሆነም አልፈረሰምም፤ በአሸዋ ላይ የተሠራው ቤት ግን ወደቀ ፈራረሰም፡፡

**ማጠቃለያ**

- ሕፃናት የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰሙና በእግዚአብሔርም የሚያምኑ ከሆኑ ቤቱን በዓለት ላይ እንደሠራው ሰው ይሆናሉ፡፡
- እግዚአብሔርን የማንሰማ ከሆንን ግን ቤቱን በአሸዋ ላይ ሠርቶ በነፋስ የፈረሰበትን ሰው እንሆናለን፡፡

**ተግባር**

- ሕፃናት የየራሳቸውን ቤት በሥዕል እንዲያዘጋጁ ወይም በመገጣጠሚያ እንዲሠሩ ያድርጉአቸው፡፡
- ሕፃናት በድንጋይ (በጠጠርና) በአሸዋ እንዲጫወቱ ያድርጉአቸው፡፡



በዐለት ላይ የተሠራው ቤት

## 34 ኛ ሳምንት
## መላእክት

**ዓላማ**

❖ ስለ መላእክት ሥራ ወይም አገልግሎት መማር፡፡

**ጥቅስ**

❖ "ድንገትም ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከመልአኩ ጋር ነበሩ፡፡" ሉቃስ 2፥13፡፡

**መግቢያ**

❖ ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ፡፡
❖ የተለያዩ መላእክትን ሥዕል አዘጋጅተው ለሕፃናት ያሳዩአቸው፡፡
❖ ሕፃናትን ስለ መላእክት የሚያውቁት ትምህርት ካለ እንዲያስረዱ ይጠይቁአቸው፡፡

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

❖ በሰማይ ብዙ መላእክት አሉ፡፡ መላእክት እንደ እኛ በቀላሉ የሚጨበጥና የሚታይ አካል የላቸውም፡፡
❖ ነገር ግን እግዚአብሔር ከፈቀደልን እናያቸዋለን፡፡
❖ እግዚአብሔር ለእኛ ለልጆቹ በጎ ነገርን ያደርጉልን ዘንድ መላእክቱን ይልካቸዋል፡፡
❖ መላእክት ከክፉ ነገር ሁላችንንም ሊጠብቁን ይችላሉ፡፡
❖ ከእግዚአብሔርም መልእክት ያመጡልናል፡፡
❖ መላእክት በእግዚአብሔር ፊት ዘወትር ያመሰግናሉ፣ ይዘምራሉ፣ ይደሰታሉም፡፡
❖ መላእክት የተለያየ ማዕረግ አላቸው፡፡ መላእክትና ሊቃነ መላእክት ተብለውም ይጠራሉ፡፡
❖ ሕፃናት የሰባቱን ሊቃነ መላእክት (ሚካኤል፣ ገብርኤል፣ ኡራኤል፣ ራጉኤል፣ ሩፋኤል፣ ፋኑኤል እና ሳቁኤል) ስም እንዲጠሩ ያድርጉአቸው፡፡
❖ መላእክት ርኅሩኅ፣ ጸጥተኞችና የሚያምሩ ናቸው፡፡
❖ መላእክት ክንፍ አላቸው፡፡ እንደ ሰውም ሊገለጡ ይችላሉ፡፡
❖ ሁላችንንም በሄድንበት ሁሉ የሚከተሉንና የሚጠብቁን ከክፉ ነገርም ሁሉ የሚከልሉን መላእክት አሉ፡፡

**ማጠቃለያ**

❖ እግዚአብሔር የሚወደውን መሥራት የምትፈልጉ ከሆነ የማትረብሹ፣ ደግና፣ ርኅሩኅም ሁኑ፡፡
❖ እግዚአብሔር እንደሚወደው የምንኖር ከሆነ እንደ መላእክት እንሆናለን፡፡

**ተግባር**

❖ የተለያዩ መላእክትን ሥዕል አዘጋጅተው ይስጡአቸው፡፡
❖ የመላእክትን ሥዕል ገጣጥመው የሚሠሩባቸው መሣሪያዎች የሚያገኙ ከሆነ አዘጋጅተው ይስጡአቸው፡፡



የእግዚአብሔር አገልጋዮች የሆኑ ቅዱሳን መላእክት

## 35 ኛ ሳምንት
## ጌታችን ለቅዱስ ጳውሎስ ተገለጠለት

**ዓላማ**

❖ በእግዚአብሔርና በቅዱስ ጳውሎስ መካከል የነበረውን ንግግር መማር።

**ጥቅስ**

❖ "ድንገትም በእርሱ ዙሪያ ከሰማይ ብርሃን አንጸባረቀ።" የሐዋርያት ሥራ 9፥3።

**ምንባብ**

❖ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 9 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ።

**መግቢያ**

❖ ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ ያስታውሱአቸው።

❖ ትምህርቱን የተመለከቱ የማይንቀሳቀሱ ወይም ተንቀሳቃሽ ሥዕሎችን ያዘጋጁ።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

❖ በአንድ ወቅት ሳውል የሚባል ሰው ነበር። ሳውል ክርስቲያኖችንና ቤተክርስቲያንን ይጠላ ነበር።

❖ ክርስቲያኖችን እየያዘ ወደ እስር ቤት ይጥላቸው ነበር።

❖ አንድ ቀን እርሱና ሌሎችም ወታደሮች ክርስቲያኖችን ለመያዝ ሲሄዱ ድንገት በእርሱ አጠገብ ከሰማይ ብርሃን አንጸባረቀ። በኋላም የሚያነጋግረው ድምፅ ሰማ። ያ ድምፅ የማን ድምፅ ይመስላችኋል?

❖ አዎ ያነጋገረው የነበረው ድምፅ የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

❖ ጌታችንም እኔንና ክርስቲያኖችን የምትቃወም አንተ ማን ነህ? አለው።

❖ ሳውልም የሚያንጸባርቀውን ብርሃን ሲያይና ድምፁንም ሲሰማ በምድር ላይ ወደቀ።

❖ ሳውልም የተቃወምኩህ አንተ ማን ነህ? አለ። ጌታችንም "እኔ ኢየሱስ ነኝ።" አለው።

❖ ሳውልም ተንቀጠቀጠ። መምህር የመንቀጥቀጥን ድርጊት በተግባር ያሳዩአቸው።

❖ አብረውትም የነበሩት የሚያንጸባርቀውን ብርሃን ቢያዩም ድምፁን ግን መስማት አልቻሉም ነበር።

❖ ሳውልም "ጌታ ሆይ ምን አደርግልህ ዘንድ ትወዳለህ?" አለው።

❖ ጌታም ሂድና ሐናንያ ከሚባል ሰው ጋር ተገናኝ፤ እርሱም ማድረግ የሚገባህን ሁሉ ይነግርሃል፣ ያሳይሃል አለው። ሳውልም ጌታችንና ብርሃኑን ከዚያ በኋላ ማየት አልቻለም።

❖ ሳውል የሚያንጸባርቀውን የጌታችንን ብርሃን ካየ በኋላ ለሦስት ቀን ታወረ ማየትም አይችልም ነበር?
**ጥያቄ :** ዕውር (ዓይነ ስውር) ማለት ምን ማለት ነው? የታወረው ማነው? ለስንት ቀን ታወረ?

❖ ጌታችን ሐናንያ ለሚባል ሰው ተገልጦ ሳውልን የት እንደሚያገኘው ነገረው።

❖ ሐናንያም ጌታችን እንደነገረው በፍጥነት ወጥቶ ሳውልን ተገናኘው።

❖ ሐናንያም እጁን በሳውል ዐይኖች ላይ ጫነ፤ ልክ እንደ ዓሣ ቅርፊት ያሉ ነገሮች ከሳውል ዓይኖች ወደቁ፤ ሳውልም እንደ ገና ማየት ቻለ። ሳውልም ክርስቲያን ሆነ፤ ተጠምቆ ስሙ ተለውጦ ጳውሎስ ተባለ።

**ማጠቃለያ**

❖ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ማንኛውንም ሰው ከመጥፎነት ወደ በጎነት መለወጥ ይችላል።

**ተግባር**

❖ የተወሰኑ ሞዴሎችን ወይም ሥዕሎችን በመጠቀም ታሪኩን ያስገንዝቡአቸው።

❖ በቤቱ ጥግ ብርሃን (በባትሪ) በማንጸባረቅ ሕፃናት በቅዱስ ጳውሎስ ፊት የተንጸባረቀውን ብርሃን እንዲረዱ ያድርጉአቸው።

❖ በሚቀጥለው ገጽ የሚገኘው ሥዕል ሕፃናት በቀለም እንዲቀቡ ያድርጉአቸው።



ጌታችን ለቅዱስ ጳውሎስ እንደ ተገለጠለት

## 36 ኛ ሳምንት
## ዕርገት

**ዓላማ**

- ስለ ዕርገት በዓል ምንነት መማር።

**ጥቅስ**

- "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ።" የሐዋርያት ሥራ 1፥8።

**ምንባብ**

- የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ።

**መግቢያ**

- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እንዲሁም አምስቱ (ግብፅ፣ ሶርያ፣ ሕንድ፣ አርመንና ኤርትራ)፣ አብያተ ክርስቲያናት የዕርገትን በዓል ከትንሣኤ በኋላ በ40ኛው ቀን ሐሙስ ያከብራሉ።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ በ40ኛው ቀን ወደ ሰማይ ዐርጓል።
- ለእኛ መልካም የሆነውን ሥፍራ ሊያዘጋጅልንና ከእርሱም ጋር ለዘላለም በዚያ እንድንኖር ወደ ሰማይ ወጥቷል።

  **ጥያቄ:**

  1. ይኸ ምን ይባላል? /ዕርገት ይባላል።/
- እግዚአብሔር በሰማይ ብቻ ሳይሆን በየትኛውም ሥፍራ እንደሚገኝ መዘንጋት የለብንም። እግዚአብሔር በሰማይም በምድርም አለ።
- ሰማይ ዙፋኑ ናት ቅዱሳኑ እንዲሁም መላእክትም የሚኖሩት በዚያ ነው።
  - ወደ ሰማይ የወጣው ማነው? /ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ።/
  - የዕርገት በዓል በየዓመቱ በምን ቀን ይከበራል? /ሐሙስ ከትንሣኤ በኋላ በ40ኛው ቀን/
  - ጌታችን ወደ ሰማይ ያረገው ከትንሣኤው በኋላ በስንተኛው ቀን ነው? /በ40ኛው ቀን/
- ከዕርገቱ በፊት ከሙታን ከተነሣ በኋላ በ40ኛው ቀን ጌታችን የሐዋርያትን እምነት ለማጽናት ተገልጾላቸዋል።
- በዚያም ቀን ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ በተራራ ተሰብስበው እያሉ ጌታችን ኃይልን እስክትለብሱ ድረስ ከኢየሩሳሌ[ም] ከተማ አትውጡ አላቸው። ደቀ መዛሙርቱም ጌታችንን ከፍ፣ከፍ፣ከፍ ሲል ተመለከቱት ከደመናትም በላ[ይ] ወጣ።
- ወደ ሰማያዊቷም ሰማይ እስኪደርስ ድረስ ወጣ... ወጣ... ወጣ... ።
- በኋላም ከእይታቸው ተሠወረ ሊያዩትም አልቻሉም።
- ተደንቀው ወደ ላይ እየተመለከቱ ሳሉ የእግዚአብሔር መልአክ ተገለጸ።
- መልአኩም አሁን ወደሰማይ ሲወጣ እንደ አያችሁት በደመና ከሰማይ ተመልሶ ሲመጣ ታዩታላችሁ አላቸው።
- ነገር ግን መቼ እንደሚመጣ ማንም ቢሆን አያውቅም።
- ሐዋርያቱም በማርቆስ እናት በማርያም ቤት በኢየሩሳሌም ቆዩ።
- መንፈስ ቅዱስንም እስኪቀበሉ ድረስ አብረው ይጸልዩ ነበር።
- ጌታችን ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ያስተምራቸውና እኛንም በሕይወታችን ሁሉ ይመራን ዘንድ መንፈስ ቅዱ[ስን] ላከላቸው።
- መንፈስ ቅዱስም ጌታችን ባረገ በአሥረኛው ቀን በሐዋርያቱ ላይ ወረደ።
- ዕርገት በእግዚአብሔር የተደረገ ገቢ ነው።
- ስለዚህ እኛም ዓላማችን ሁሉ ወደ ላይ ወደ እግዚአብሔር መሆን አለበት።

- ስንጸልይም ወደ ላይ ወደ እግዚአብሔር እጃችንን ማንሳት አለብን፡፡
- ወደ እግዚአብሔር የሚደረግ ጉዞ ዘወትር ወደ ላይ ነው፡፡
- የመጀመሪያውም የጌታችን ዕርገት ፍሬ መንፈስ ቅዱስን መቀበል ነው፡፡
- ጌታችን ባረገ ጊዜ የገባው ቃልኪዳን ምን ነበር? /መንፈስ ቅዱስን እሰደድላችኋለሁ፡፡/

**ማጠቃለያ**

- በደመና ሲያርግ ሲሰወር ወደ ሰማይ ሲወጣ እንደታየ ሁሉ ከእልፍ አእላፍ መላእክት ጋር ተመልሶ ይመጣል፡፡

**ተግባር**

- በሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም በቤተክርቲያን በምንጸልይበት ጊዜ ሁሉ ወደ ላይ ቀና ብለን እጃችንን በማንሳት ጭምር መሆን አለበት፡፡
- ወደ ሰማይ ጌታችን ሲያርግ የሚያሳየውን ሥዕል አዘጋጅተው ሕፃናት በቀለም ይቀቡት ዘንድ ይስጧቸው፡፡
- "ዐረገ በስብሐት ዐረገ በእልልታ በስብሐት በእልልታ ዐረገ ዐረገ በእልልታ፤ ሞትን ድል አድርጐ የሠራዊት ጌታ ዐረገ ዐረገ በእልልታ" የሚለውን መዝሙር ሕፃናት እንደዘምሩ ያድርጓቸው፡፡



ኢመቤታችንና ሐዋርያት ጌታችንን በሚያርግበት ወቅት

## 37 ኛ ሳምንት
## ጰራቅሊጦስ

**ዓላማ**

❖ በዓለ ሃምሳ (ጰራቅሊጦስ) የቤተክርስቲያን ልደት እንደሆነ መማር።

**ጥቅስ**

❖ "በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው።" የሐዋርያት ሥራ 2፥4።

**ምንባብ**

❖ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ።

**መግቢያ**

❖ ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።

❖ በዕለተ ጰራቅሊጦስ በሁሉም ደቀ መዛሙርት ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው።

❖ ሁሉም ደቀ መዛሙርት ከላይ ከአርያም የመጣ ኃይልን ተሞልተው ነበር።

❖ በዚያን ቀን ለሁሉም ዓይነት ሕዝብ ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መናገር ይችሉ ነበር።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

❖ ጰራቅሊጦስ ከትንሣኤ በኋላ የሚገኝ ሃምሳኛው ቀን ነው።

❖ በዚያን ቀን ከተለያዩ አገሮች በርካታ ሕዝቦች ተሰብስበው ነበር።

❖ በማርቆስ እናት በማርያም ቤት ደቀ መዛሙርቱ ተሰብስበው እያሉ ዊዊውው... ዊዊውው... (ሸው... ሸው... ሸው...) እያለ ታላቅ ነፋስ መጣ።

❖ ዐውሎ ነፋሱ በበር በመስኮት ገብቶ በሁሉም ላይ በኃይል ነፈሰ።

❖ እሳትም እንደ ትንሽ ምላስ እየሆነ ከነፋሱ ጋር መጣ።

❖ ሁሉም ደቀ መዛሙርት መልካም ዜና የሚናገሩበት ኃይል በእሳት አምሳል በእያንዳንዳቸው ላይ ዐረፈ።

❖ ይኸ በእሳት አምሳል የተገለጸው መንፈስ ቅዱስ ነበር።

❖ ከዚህም በኋላ ደቀ መዛሙርቱ በተለያየ ቋንቋ መናገር ቻሉ።

❖ በዚያ የነበሩት ሁሉ በየራሳቸው ቋንቋ ሲናገሩ ደቀ መዛሙርቱን ሰሙአቸው።

❖ በኢየሩሳሌም የተሰበሰቡት ሕዝብ ሁሉ ሐዋርያት በየቋንቋቸው መናገር ስለተቻላቸው ንግግራቸውንና ትምህርታቸውን ተረዱ።

❖ ደቀ መዛሙርቱ ለሕዝቡ የተናገሩት ስለ ኢየሱስ ነበር።

❖ በዚህም የተነሳ ሁሉም በጌታችን አምነው ክርስቲያን ሆኑ።

❖ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላካችንና መድኃኒታችን የመሆኑ ዜና በዓለም ለሚገኝ የሰው ዘር ሁሉ መድረስ ይኖርበታል።

❖ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስን ከተቀበለ በኋላ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተናገረ፣ በዚህም የተነሳ 3000 ሰዎች ወዲያው አምነው ክርስቲያን ሆኑ።

❖ እኛ መንፈስ ቅዱስን በ40 እና በ80 ቀናችን ተጠምቀን ቅብዐ ሜሮንን ስንቀባ እንቀበላለን።

❖ የቤተክርስቲያናችን ምስጢራት (ጥምቀት፣ ሜሮን፣ ቁርባን፣ ንስሐ፣ ክህነት፣ ተክሊልና ቀንዲል) የሚፈጸሙትና የሚከናወኑት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው።

❖ መንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን በምንሰራበት ጊዜ ሁሉ ለምን ሠራችሁ? እያለ ይወቅሰናል።

❖ መንፈስ ቅዱስ ስህተትንም እንዳንሰራ ያስጠነቅቀናል።

❖ መንፈስ ቅዱስ ልክ እንደተርብ ወዳጅ ከክፉ ነገር ሁሉ ይጠብቀናል።

- እግዚአብሔር ይኽን ሁሉ ስጦታ ስለ ሰጠንና ስለ ጥበቃው ሁሉ ፈጽመን ልናመሰግነውና ልናከብረው ይገባናል።

**ጥያቄ**


1. በዓለ ጰራቅሊጦስን የምናከብረው መቼ ነው?
2. በዓለ ጰራቅሊጦስን ከዕርገት በኋላ በስንተኛው ቀን እናከብራለን?
3. የቤተክርስቲያንን ልደት የምናከብረው በየትኛው ቀን ነው?

**ማጠቃለያ**

- ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች ነን። መንፈስ ቅዱስም በእኛ ውስጥ አለ።
- ቀሳውስትና ኤጲስቆጶሳት በመስቀል እየባረኩ ካጠመቁን በኋላ ቅብዐ ሜሮን ሲቀቡን መንፈስ ቅዱስን እንቀበላለን።

**ተግባር**

- በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሚጠመቁና ቅብዐ ሜሮን የሚቀቡ ሕፃናትን የቪዲዮ ፊልም ያሳዩአቸው። በዚህም መንፈስ ቅዱስን እንዴት እንደ ተቀበሉ ይማራሉ።
- የበዓለ ጰራቅሊጦስ ሥዕሎችን አዘጋጅተው ለሕፃናት ይስጡአቸው።



ጰንጠቆስጤ

# ጾመ ሐዋርያት

## 38 ኛ ሳምንት
## የቅዱስ ጴጥሮስ የመጀመሪያ ተአምር

**ዓላማ**

- ቅዱስ ጴጥሮስ በተወደደችው መልካም በሚሉአት በቤተ መቅደስ ደጅ ያደረገውን ተአምር መማር።

**ጥቅስ**

- "ተነሣና ተመላለስ።" የሐዋርያት ሥራ 3፥6 ።

**ምንባብ**

- የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 1 እስከ 11።

**መግቢያ**

- ያለፈውን ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- የኔ ቢጤ አይታችሁ ታውቃላችሁ? የኔ ቢጤ የሚባሉት እነማን ናቸው?
- የታመመ ሰው ወይም የኔ ቢጤ ብታዩ ምን ታደርጋላችሁ?
- አንዳንድ ሰዎች ሲታመሙ መሥራት ያቅታቸዋል፤ ገንዘብም ስለ ማይኖራቸው በልመና ይሰማራሉ ።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- የዛሬው ትምህርት ከልጅነቱ ጀምሮ መራመድ ስለ ማይችል ሰው ታሪክ ነው።
- በእግሩ ላይ ችግር ስለ ነበረበት ተራምዶ አያውቅም ነበር።
- ይኸ ሰው ሥራ መሥራት ስለ ማይችል እጅግ ደሃ ነበር።
- በቤክርስቲያንም በር ተቀምጦ የሚገቡትንና የሚወጡትን ገንዘብ እንዲሰጡት ይለምን ነበር።
- የቤተክርስቲያኑ መግቢያ መልካም የሚሉት ስም ነበረው።
- አንድ ቀን ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ ወደ ቤተ መቅደስ ሲሄዱ አገኛቸውና ርቦኛልና ገዝቼ እበላ ዘንድ ገንዘብ ስጡኝ አላቸው።
- ቅዱስ ጴጥሮስ ግን ሊሰጠው የሚችለው ገንዘብ አልነበረውም።
- ይኸንንም ሰው አንተ ሰው ብር የለኝም ነገር ግን ጌታዬና አምላኬ ይፈውስህ ዘንድ እለምነዋለሁ ከተፈወስክም በኋላ መሥራት ትችላለህ ገንዘብም አግኝተህ ትመገባለህ አለው።
- ቅዱስ ጴጥሮስም በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለው።
- ይኸም ሰው ወዲያው ዘለሎ እግሩም ጸንቶ ቆመ።
- በጣም ደስ ብሎት እየዘለለ እግዚአብሔርንም እያመሰገነ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ።
- መራመድ የማይችለው ሰው ድኖ የተነሳው ተራምዶም ወደ ቤተ መቅደስ በመግባት ያመሰገነው መንፈስ ቅዱስ በርሱ ላይ ስላደረ ነው።

**ጥያቄ**

1. የኔ ቢጤውን የፈወሰው ማን ነው?
2. የቤተ መቅደስ መግቢያ ምን የሚባል ስም ነበረው?
3. የተጠቀሰውን የመጽሐፍ ጥቅስ በቃላችሁ ተናገሩ?
4. ለየኔ ቢጤ ገንዘብ ወይም ሌላ ነገር ሰዎች ሲሰጡ አይታችሁ ታውቃላችሁ?



ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ ያደረጉት ተአምር

## 39 ኛ ሳምንት
## በሸማ የተሞሉት እንስሳት

**ዓላማ**

- የጴጥሮስንና የቆርኔሌዎስን ታሪክ መማር፡፡

**ጥቅስ**

- "ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ፡፡" የሐዋርያት ሥራ 10፥44፡፡

**ምንባብ**

- የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ፡፡

**መግቢያ**

- ለትምህርቱ መርጃ የሚሆን ሥዕል ወይም ተንቀሳቃሽ ምስል ያዘጋጁ፡፡
- አንድ እንስሳ መርጠው ሕፃናትን ምን ይባላል ? ድምፁስ ምን ዓይነት ነው ብለው ይጠይቁአቸው፡፡
- የተለያዩ እንስሳትን ስምና ድምፅም ይጠይቁአቸው፡፡

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- አንድ ቀን ቅዱስ ጴጥሮስ ተኝቶ እንስሳት የሚገኙበት ሸማ ከተከፈተ ሰማይ ሲወርድ አየ፡፡
- በሬ፣ በግ፣ ፍየል፣ ድኩላ ወዘተ ... ነበሩ፡፡
- በሸማው ውስጥ የነበሩት እንስሳት አራት እግሮች ነበራቸው፡፡
- ያም ሸማ ከእንስሳቱ ጋር ወደ መሬት ወረደ፡፡
- ቅዱስ ጴጥሮስም ሲነቃ ባየው ነገር ተደነቀ፡፡
- ወዲያውም መልካሙ ሰው ቆርኔሌዎስ የላካቸው ሦስት ሰዎች ቅዱስ ጴጥሮስን ፈልገውት ፈልገው መጡ፡፡
- ቅዱስ ጴጥሮስም ከእነርሱ ጋር ወደ ቆርኔሌዎስ ሄደ፡፡
- ወደ ቆርኔሌዎስም ቤት ሲገባ ብዙ ሰዎች ከቅዱስ ጴጥሮስ የእግዚአብሔርን ቃል ሊማሩና ሊሰሙ ሲጠብቁት አገኛቸው፡፡
- ቅዱስ ጴጥሮስም እግዚአብሔር ለሁሉም መልካም እንደ ሆነና ምን ያህልም እንደ ሚወድደን አስተማራቸው፡፡
- የቅዱስ ጴጥሮስንም ትምህርት በመማራቸው እጅግ ደስ ብሎአቸው ክርስቲያኖች መሆን ፈለጉ፡፡
- ልክ እንደ እኛ መሆን ፈለጉ እኛ ምንድን ነን? እኛ ክርስቲያን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ልጆች ነን፡፡
- ድንገትም የቅዱስ ጴጥሮስን ድምፅ ሲሰሙ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው ክርስቲያኖችም ሆኑ፡፡

**ማጠቃለያ**

- እግዚአብሔር ሁሉም የሰው ዘር እንደ እኛ ጥሩ ክርስቲያን እንዲሆኑ ይፈልጋል፡፡

**ተግባር**

- ልጆች የተወሰኑ እንስሳትን ሥዕል በቀለም እንዲቀቡ ያድርጉአቸው፡፡
- ስለ ሃይማኖታችን ከተዘመሩ መዝሙራት መካከል አንዱን እንዲዘምሩ ያድርጉአቸው፡፡

## 40 ኛ ሳምንት
## እግዚአብሔር ይስጥልኝ አመሰግናለሁ በሉ

**ዓላማ**

- ዘወትር እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ ማለት እንደሚኖርብን መማር::
- በሰዎች ሁሉ ፊት ትሑታን በመሆን አመሰግናለሁ ማለት እንደሚገባ መማር::

**ጥቅስ**

- "እግዚአብሔርን እያመሰገነ እያከበረም ተመለሰ::" ሉቃስ 17 ÷ 16::

**ምንባብ**

- የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 17 ከቁጥር 11 እስከ 19::

**መግቢያ**

- ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ::
- መቼ አመሰግናለሁ እንደሚሉና እግዚአብሔር ይስጥልን ብለው የሚመልሱትም መቼ እንደሆነ ሕፃናቱን ይጠይቋቸው::
- አመሰግናለሁ የምንለው ማንን ነው? ብለው ይጠይቋቸው::

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- የዛሬው ትምህርት አመሰግናለሁ ስላለ እና እግዚአብሔር ስለተደሰተበት ሰው ነው::
- አንድ ጊዜ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ መንደር ገባ::
- በዚያም መንደር የሰውነታቸው ቆዳ በጣም የተጎዳ አሥር ለምጻሞችን አገኘ::
- ማንኛውንም ሰው እንዳይነኩ ተከልክለው ነበር::
- አሥሩም ሰዎች ጌታችንን ሲያዩት በሩቅ ሆነው ጌታ ሆይ ማረን ብለው ጮሁ::
- ጌታችንም ወደ ቤተመቅደስ ሄደው ራሳቸውን ለካህናት እንዲያሳዩ ነገራቸው::
- ካህናት ዛሬ በቤተክርስቲያናችን እንደምናያቸው አባቶች ናቸው::
- ወደ ቤተ መቅደስም ሄደው ደህና ሆኑ ተፈወሱ:: የሰውነታቸው ቆዳ ዳነ እንደ ጤናማ ሰውም ሆኑ::
- ከአሥሩ ሰዎች ውስጥ አንዱ ብቻ ጌታ ሆይ ስላዳንከኝ አመሰግናለሁ ለማለት ወደ ጌታችን ተመልሶ መጣ::
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ሰው ደስ አለው::
- ጌታችን ሌሎቹ የዳኑት ዘጠኙ ሰዎች ወዴት ቀሩ? ብሎ ተገረመ::
- ዘጠኙም እናመሰግናለን ለማለት ተመልሰው አልመጡም ነበር::
- ሊያመሰግን የመጣውን አንዱን ሰው ግን ባረከውና ከዚህ በኋላ ከቤተሰብህም ጋር በሰላም ኑር ብሎ ወደ ቤተሰቦቹ ሸኘው::

**ማጠቃለያ**

- መልካም ነገር ሲሰጣቸው አመሰግነዋለሁ የሚሉ ሕፃናትን እግዚአብሔር ይወድዳል::
- ሌሎች ሰዎች ስላደረጉላቸው መልካም ነገር እናመሰግናለን የሚሉ ሕፃናትንም እግዚአብሔር ይወድዳቸዋል::

**ተግባር**

- የአሥሩን ሰዎች ሥዕል አምጥተው ሕፃናቱ እንዲቆጥሩአቸው ያድርጉ::
- ከአሥሩ ተመልሶ በመምጣት ያመሰገነውን ሰው ሥዕል ያሳዩአቸው::
- አሥር የሰው ሥዕሎች የሚገኙባቸው ስቲከሮች አዘጋጅተው በነጭ ወረቀት ላይ እንዲለጥፉ ያድርጉአቸው::
- ሲጸልዩ እግዚአብሔር ሆይ አመሰግናለሁ እንዲሉና ማንኛውንም በጎ ያደረገላቸውን ሰው እግዚአብሔር ይስጥልን እናመሰግናለን እንዲሉ ያሳስቡአቸው::

# ነሐሴና ጳጉሜን

## 41 ኛ ሳምንት

## የጌታችንንና የእመቤታችንን ስደት

**ዓላማ**

- ግብፅና ኢትዮጵያ በጌታችን ዘንድ ልዩ ሥፍራ አላቸው።

**ጥቅስ**

- "የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ አየሁ።" ትንቢተ ዕንባቆም 3፥7።
- "ሕዝቤ ግብፅ የተባረከ ይሁን።" ትንቢተ ኢሳይያስ 19፥25።

**ምንባብ**

- የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 2 ከቁጥር 13 እስከ 23።

**መግቢያ**

- ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- በአህያ ላይ ተቀምጣችሁ ታውቃላችሁ? እመቤታችንና ሕፃኑ ክርስቶስ በአህያ ላይ ተቀምጠዋል።
- ከዚህ በፊት ግብፅን ወይም አክሱም ጽዮንን ጎብኝታችሁ ታውቃላችሁ?
- እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ግብፅን የባረከ መሆኑን የሚያስረዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ሊነግረን የሚችል ማን አለ? ብለው ይጠይቁአቸው።

**ጥያቄ**

1. የጌታችን እናት ማን ነበረች?

- ሁለት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሕፃናት አይታችሁ ታውቃላችሁን? እንዴት እንደሚጫወቱ ተመልክታችኋቸዋል?
- እንግዲህ አሁን ስለ ሕፃኑ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነገር እንማራለን ።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- ሁለት ዓመትና ከዚያ በታች የሆናቸው ሕፃናት ሁሉ ተሰብስበው እንዲገደሉ ንጉሥ ሄሮድስ አዘዘ።
- ንጉሥ ሄሮድስ ይኸን ትእዛዝ ያዘዘው ጌታችን ኢየሱስን ለመግደል ነበር ።
- ሕፃኑ ኢየሱስ አድጎ ንጉሥ ሆኖ ሥልጣኔን ይወስድብኛል ብሎ ይፈራ ነበር።
- አንድ ቀን ቅዱስ ዮሴፍ ተኝቶ እያለ "ንጉሥ ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልጋልና እናቱንና ሕፃኑን ይዘህ ወደ ግብፅ ሽሽ ብሎ።" የእግዚአብሔር መልአክ በሕልም ነገረው።
- ዮሴፍም ተነስቶ አህያ አዘጋጅቶ ሕፃኑንና እናቱን ይዞ ጉዞ ጀመረ።
- ከቤተልሔም ወጥተው ወደ ግብፅና ወደ ኢትዮጵያ ሄዱ። ዮሴፍ አህያይቱን እየመራ በበረሃ ውስጥ በርትቶ ተጓዘ። እግዚአብሔርም ትክክለኛውን አቅጣጫ ይመራቸው ነበር።
- እግዚአብሔር በየ መንገዱ ከሚያገኙአቸው የተለያዩ ነገደ ሕዝቦችና በበረሃ ከሚገኙ የአውሬዎች መርዝ ሁሉ ጠበቃቸው። ከዚያም በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ ሕፃኑን የሚፈልገው ሄሮድስ መሞቱን ነገረው።

**ማጠቃለያ**

- እኛ ጌታችን በተሰደደ ጊዜ ስለ ጎበኘን የተባረክን ነን።
- እርሱ ተሰድዶ የመጣው ከጨካኝ ንጉሥ ሸሽቶ ነበር።

**ተግባር**

- ኢትዮጵያዊ በመሆናችሁ ደስ ይበላችሁ።
- እግዚአብሔር ኢትዮጵያን "ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" ብሎ የባረካት አገር እኛም የተባረክን የጸሎት ሕዝቦች መሆናችንን እንረዳ። መዝሙር 67፥31።
- በቤተክርስቲያናችን ስለ ኢትዮጵያ ከተዘመሩ መዝሙሮች አንዱን መዝሙር እንዲዘምሩ ያድርጉአቸው።



የጌታችንና የእመቤታችን ስደት

## 42 ኛ ሳምንት

## ብር የነበረበት ዓሣ

### ዓላማ

- ከማንኛውም ነገር በላይ በእግዚአብሔር መመካት እንዳለብን መማር፡፡

### ጥቅስ

- "መጀመሪያ የሚወጣውን ዓሣ ውሰድ፡፡" ማቴዎስ 17፥27፡፡

### ምንባብ

- የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 17 ከቁጥር 24 እስከ 27፡፡

### መግቢያ

- ያለፈውን ትምህርትና ጥቅስ መከለስ፡፡
- ሕፃናትን እውነተኛ ዓሣ አይተው ያውቁ እንደ ሆነ ይጠይቁአቸው፡፡ የት አዩ? ምን ዓይነት ቀለም ነበረው?
- የተለያዩ ዓሣዎችን ሥዕል አዘጋጅተው ለሕፃናቱ ያሳዩአቸው፡፡
- ከኘላስቲክ የተሠራ ዓሣ አዘጋጅተው ሳንቲም የሚገኝበት ትንሽ ቦርሳ በዓሣው ውስጥ ይደብቁ፡፡

### የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ

- በአንድ ወቅት ለቤተ መቅደስ ገንዘብ የሚሰበስቡ ሰዎች መጥተው ከጌታችንና ከቅዱስ ጴጥሮስ ገንዘብ መሰብሰብ ፈለጉ፡፡
- አንተና አለቃህ ኢየሱስ ፈጥናችሁ ገንዘቡን አትከፍሉም እንዴ? ብለው ቅዱስ ጴጥሮስን ጠየቁት፡፡
- ቅዱስ ጴጥሮስም ይከፈል እንደ ሆነ ጌታችንን ሊጠይቀው ወደ ቤት ገባ፡፡
- ጌታችንም እንከፍላለን አለው፡፡
- ቅዱስ ጴጥሮስም ገንዘብ የለንም ከየት አምጥተን እንከፍላለን? አለው፡፡
- ጌታችንም ዓሣ ለማጥመድ እንዲሄድ መጀመሪያም ከሚያጠምደው ዓሣ አፍ ውስጥም ገንዘብ እንደሚያገኝ ያንንም ገንዘብ ወስዶ ለቤተ መቅደስ እንዲከፍል ለቅዱስ ጴጥሮስ ነገረው፡፡
- ቅዱስ ጴጥሮስም ልክ ጌታችን እንደ ነገረው አደረገ፡፡
- ያጠመደውን የመጀመሪያ ዓሣ ወስዶ አፉን ሲከፍተው ገንዘብ አገኘ፡፡
- ጌታችንም ስለ ሚሆነው ነገር አስቀድሞ የነገረውን እያሰበ በጣም ደስ አለው ተደነቀም፡፡
- ቅዱስ ጴጥሮስም ያን ገንዘብ ወስዶ የጌታችንና የራሱን ድርሻ ከፈለ፡፡

### ማጠቃለያ

- እግዚአብሔር የአሁኑንም ሆነ የወደፊቱን ስለ ሚያውቅ ማንኛውንም ነገር ለእኛ ያመቻችልናል፡፡
- ሁላችንም ይጠብቀን ዘንድ በእርሱ እንታመናለን እንመካለንም፡፡

### ተግባር

- በትንሽ ዕቃ የተቀመጡ ዓሣዎች የሚያገኙ ከሆነ ልጆች እንዲመለከቱአቸው ወደ መማሪያ ክፍል ያምጡአቸው፡፡
- የዓሣ ሥዕሎችን አዘጋጅተው በቀለም እንዲቀቡ ያድርጉአቸው፡፡

## 43 ኛ ሳምንት
## የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ጴጥሮስን ከእስር ቤት ነፃ አወጣው

ዓላማ

- እግዚአብሔር እንደሚያድነንና መላእክቱን እንደሚልክልን መማር።

ጥቅስ

- "የእግዚአብሔር መልአክ ቀረበ።" የሐዋርያት ሥራ 12፥7።

ምንባብ

- የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 12 ከቁጥር 1 እስከ 9።

መግቢያ

- ያለፈውን ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- የእግዚአብሔርን መልአክ ቢያዩ ምን እንደ ሚያደርጉ ሕፃናትን ይጠይቁአቸው።
- መላእክት ምን ይመስላሉ?
- መላእክት የሚሠሩት ምንድር ነው?
- የቅዱሳን መላእክት ሥዕል ያሳዩአቸው።

የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ

- በአንድ ወቅት ሄሮድስ የሚባል ሰው ነበር።
- ሄሮድስ ክፉ ንጉሥ ነበር፤ የጌታችንን ወዳጆችና ደቀ መዛሙርቱን ያስጨንቃቸው ነበር።
- የጌታችንን ቃል ስለሚያስተምር ቅዱስ ጴጥሮስን ይዞ እስር ቤት ጨመረው።
- ቅዱስ ጴጥሮስም እግዚአብሔር ከርሱ ጋር ስለሆነ በእስር ቤት ሆኖ አይፈራም ነበር።
- ተኝቶ እያለ የእግዚአብሔር መልአክ ቀርቦ በእስር ቤቱ ውስጥ ብርሃን አበራ።
- በመቀጠልም በቅዱስ ጴጥሮስ እጅና እግር ላይ ታስሮ የነበረው ሰንሰለት በመልአኩ አማካኝነት ተፈትቶ ወደቀ።
- ቅዱስ ጴጥሮስም ዳግመኛ ነጻ ወጣ።
- መልአኩም ቅዱስ ጴጥሮስን ከእሥር ቤት አውጥቶ የሚሄድበትን መንገድ አሳየው።
- መልአኩም ወዲያው ከርሱ ተሰወረ፤ ቅዱስ ጴጥሮስም ወደ ቤት ሄደ።
- ቅዱስ ጴጥሮስንም ሲያዩት ስለ እርሱ ይጸልዩ ነበርና ሁሉም ደስ አላቸው።
- እግዚአብሔርም ጸሎታቸውን ሰምቶ መልአኩን ልኮ ቅዱስ ጴጥሮስን ነፃ አውጥቶታል።

ማጠቃለያ

- ቅዱሳን መላእክት እኛን ለመርዳትና በችግራችን ጊዜ ሁሉ እኛን ለማዳን ከእግዚአብሔር ይላካሉ።
- መላእክት ባናያቸውም እንኳን እኛን ለመጠበቅ ዘወትር በዙሪያችን ይኖራሉ።

ተግባር

- ለሕፃናት የመላእክትን ሥዕል አዘጋጅተው ይስጡአቸው።
- የመላእክትን መዝሙር አስጠንተው እንዲዘምሩ ያድርጉአቸው።



የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ጴጥሮስን ከእስር ቤት ነጻ ሲያወጣው

## 44 ኛ ሳምንት
## እግዚአብሔር ሳሙኤልን ከእንቅልፉ ቀስቅሶ ጠራው

ዓላማ

- ስለ ጸሎት መማር።

ጥቅስ

- "አቤቱ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር በለው።" መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 3፥9።

ምንባብ

- መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 1 እስከ ፍፃሜ።

መግቢያ

- ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- ሳሙኤል ተኝቶ ሳለ የሚያሳይ ሥዕል ወይም ታሪኩን የሚገልጹ ተከታታይ ፎቶዎች (Slides) ወይም ከተገኘ ቪዲዮ ፊልም በማዘጋጀት ያሳዩአቸው።
- ልጆችን በየቀኑ ይጸልዩ እንደሆነ ይጠይቋቸው።
- ምንጊዜ እንደሚጸልዩ ይጠይቋቸው። ከመብላታቸው በፊትና ከመኝታ በፊት ይጸልዩ እንደሆነም ይጠይቋቸው።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- ከዕለታት አንድ ቀን ሳሙኤል የሚባል አንድ ትንሽ ልጅ ነበር።
- ከቄሱ ዔሊም ጋር በቤተ መቅደስ ውስጥ ይኖር ነበር።

**ጥያቄ**

1.የልጁ ስም ማነው?
2.የቄሱ ስም ማነው?
3.ሳሙኤል የት ነው የሚኖረው?

- አንድ ቀን ሳሙኤል ሊተኛ ሲዘጋጅ እግዚአብሔር ሳሙኤል... ሳሙኤል... ብሎ ጠራው።
- ሳሙኤልም ቄሱ ዔሊ የጠራው መስሎት እየሮጠ ሄዶ "አቤት ይኸው መጣሁ..." አለው።
- እርሱም "አልጠራሁህም ተመልሰህ ተኛ።" አለው። ሳሙኤል ሄዶ ተኛ።
- በድጋሚ ሳሙኤል...ሳሙኤል... የሚል ድምፅ ጠራው።
- ሳሙኤልም ተነሥቶ ወደ ዔሊ ሄደና "እነሆኝ የጠራኸኝ አለ።"
- ዔሊ ሳይጠራው ሳሙኤል በመምጣቱ በጣም ተገርሞ ልጄ ሆይ አልጠራሁህም ተመልሰህ ተኛ አለው።
- ዔሊም ሳሙኤልን ከዚህ በኋላ የሚጠራህን ድምፅ በድጋሚ ከሰማህ "አቤቱ ባርያህ ይሰማልና ተናገር በለው።" አለው።

**ጥያቄ**

1. ሳሙኤልን የሚጠራው ማን ነበር?
2. ዔሊ ሳሙኤልን ምን አለው?

- ሳሙኤል ጥሩ ልጅ ስለነበረ ዔሊ የነገረውን አደረገ። ተመልሶም ሄዶ ተኛ።
- በድጋሚ እግዚአብሔር "ሳሙኤል... ሳሙኤል... " ብሎ ጠራው።

**ጥያቄ**

1. እግዚአብሔር ሳሙኤልን ስንት ጊዜ ጠራው?


- ሳሙኤልም ለእግዚአብሔር "አቤቱ ባርያህ ይሰማልና ተናገር" ብሎ መለሰለት።
- ከዚያም እግዚአብሔር ለሳሙኤል ወደፊት የሚሆኑ ብዙ ነገሮችን ነገረው።

## ማጠቃለያ

- ሳሙኤል ከመተኛቱ በፊት እግዚአብሔርን እንዳነጋገረ ሁሉ እኛም ከመተኛታችን በፊት በጸሎት እግዚአብሔርን ማነጋገር አለብን።

## ተግባራዊ ትምህርት

- ሁለት ልጆች የዔሊና የሳሙኤልን ገጸ ባህርያት በመወከል ታሪኩን በድራማ መልክ እንዲያሳዩ ያድርጉ።



እግዚአብሔር ሳሙኤልን ከእንቅልፉ ቀስቅሶ ሲጠራው

# ማሟያ ትምህርቶች

## 45 ኛ ሳምንት
## ኤልያስና ቁራዎቹ

ዓላማ

- ፍጥረታት ሁሉ ለእግዚአብሔር እንደሚታዘዙለት ሁሉ እኛም መታዘዝ እንደ አለብን መማር።

ጥቅስ

- "ልጆች ሆይ ለወላጆች በጌታ ታዘዙ፤ ይህ የሚገባ ነውና።" ኤፌሶን 6፥1።

ምንባብ

- *መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ምዕራፍ 17 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ።*

መግቢያ

- የዛሬው ትምህርት ጠንካራና ጀግና ስለ ነበረው ኤልያስ የሚባል ሰው ነው።
- ኤልያስ ሳይጠራጠርና ሳያመነታ እግዚአብሔርን በፍጹም የታዘዘ ሰው ነበር። ክፉውን ንጉሥ አክዓብን ለማውገዝ የደፈረ ቆራጥ ሰው ነበር።
- በዚህ ታሪክ ወፎች እንዴት ለእግዚአብሔር ታዛዥ እንደሆኑ እንመለከታለን። ታሪኩ ወፎች ለራሳቸው ምግብ ከማሳደድ ይልቅ ለሌላው የሚመግቡበት ታሪክ ነው።

የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ

- በድሮ ጊዜ አክዓብ የሚባል ንጉሥ ነበር።
- ኤልዛቤል የምትባል ሚስት ነበረችው።
- ሁለቱም በእስራኤል ሕዝብ ላይ ብዙ በደል ይፈጽሙ ነበር።
- ሕዝቡን ከማገልገል ይልቅ የራሳቸውን ሀብት ብቻ ያካብቱ ነበር።
- የገዛ ሕዝባቸውን ሳይቀር ይነጥቁ ነበር። ኤልዛቤል በአል የሚባል ጣኦት የምታመልክ ነበረች።
- የዘንበሪ ልጅ አክዓብ በእስራኤል ለሃያ ሁለት ዓመታት ነገሠ።
- ለዮአል ጣዖት መሠዊያ ገነባ። ሕዝቦቹም እግዚአብሔርን ትተው በአልን ስላመለኩ እግዚአብሔር ተቆጣ።
- በዚያ ዘመን ለእግዚአብሔር በአግባቡ የሚታዘዝ ሰው ኤልያስ ነበር።
- ኤልያስ እንደ ቤተክርስቲያናችን አባቶች እግዚአብሔርን ስለ መከተልና ስለ ጸሎት ያስተምር ነበር።
- ኤልያስ ለእግዚአብሔር ታዛዥና በማንኛውም ጊዜ "አቤቱ ጌታዬ ሆይ" በማለት ለፈጣሪ ቅድሚያ የሚሰጥ ሰው ነበር።
- እግዚአብሔር ምንም ነገር ቢያዘው ትዕዛዙን ከመፈጸም ወደ ኋላ አይልም። "ለምን እኔ ብቻ?" ወይም "እንዴት ይሄንን ልፈጽም እችላለሁ?" ወይም ደግሞ «ቀስ ብዬ ወደፊት እሠራዋለሁ።»ብሎ ፈፅሞ አያውቅም።
- ለእግዚአብሔር ዘወትር ታዛዥ ሆኖ ይኖር ነበር። ይኸን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዝርዝር የተገለጸ ብዙ ነገር አይገኝም።
- እግዚአብሔርም የእስራኤል ሕዝብ በአል የሚባል ጣዖት እያመለኩ ወደ ተሳሳተ መንገድ ሲያመሩ አያቸው።
- እግዚአብሔር ከግብጻውያን አገዛዝ ነጻ እንዳወጣቸውና ቀይ ባሕርን አሻግሮ ወደ ተስፋ መሬታቸው እንዲመለሱ ማድረጉን ሁሉ ረሱ።
- ኤልያስ ወደ ንጉሥ አክዓብ ሄዶ "በፊቱ የቆምኩት የእስራኤል አምላክ ሕያው እግዚአብሔርን ከአፌ ቃል በቀር በእነዚህ ዓመታት ጠልና ዝናብ አይሆንም (ዝናብ አይዘንብም)።" አለው።
- ሰውም እንስሳውም የሚበላውና የሚጠጣው አይኖረውም አለ።
- በጉተራ ያከማቹት ምግብ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አለቀባቸው፤ ኤልያስ እግዚአብሔርን እስኪለምነው ድረስ ዝናብም አልዘነበም።

- ከሕፃን እስከ አዛውንት ድረስ ሁሉም በረሃብ ተሰቃዩ፡፡
- እግዚአብሔር ኤልያስን ተነስተህ ወደ ሩቅ ሥፍራ ሂድ አለው፡፡ "ከዚያም ከወንዙ ትጠጣለህ፤ቁራዎቹም ይመግቡህ ዘንድ አዝዣለሁ፡፡" አለው፡፡
- ቁራ ማለት በሰማይ የሚበር የተለየ ድምፅ የሚያወጣ ትልቅ ወፍ ነው፡፡
- ምግቡንም የሚያገኘው ትናንሽ ወፎችን በማደንና መሬት ላይ የወደቀ ምግብ በመፈለግ ነው፡፡
- ከፍ ብሎ ይበርና ትንሽ ወፍ ወይም ሌላ የሚበላ ነገር መሬት ላይ ካየ ፈጥኖ ወደ መሬት በመውረድ የሚበላውን ነገር በአፉ ይዞ ወደ ጐጆው ይመለሳል፡፡
- እግዚአብሔርም ለዚህ ወፍ ነበር ኤልያስን እንዲመግብ ትዕዛዝ የሰጠው፡፡
- እግዚአብሔር ኤልያስን ወደ ምሥራቅ ሄደህ በዚያ ተቀመጥ ብሎ አዘዘው፡፡
- ያ ቦታ ሰውም ተክልም የሌለበት አዕዋፋት ብቻ የሚኖሩበት ሥፍራ ነው፡፡
- ኤልያስም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ተቀብሎ ሄደ፡፡ ያደረገውም በጣም ረጅምና አድካሚ ጉዞ ነበር፡፡
- ከሸለቆው መሐል አንድ ትንሽ ምንጭና በመጨረሻም የሚያርፍበት ዋሻ አገኘ፡፡
- ያ ሥፍራ ንጉሥ አክዓብ ኤልያስን ሊያገኘው የሚችልበት ቦታ አይደለም፡፡
- ያ ቦታ ምንም ዓይነት ሰው የማይኖርበት ቦታ ነው፡፡
- ኤልያስ ብቻውን ከእግዚአብሔር ጋር በዚህ ቦታ ሆነ፡፡
- በአካባቢው ምንም ዓይነት ምግብ ስላልነበረ ሲርበው ምግብ እንዴት እንደሚያገኝ ግራ ገባው፡፡
- ቀኑም መሸ፡፡ ሊተኛ ሲዘጋጅ ቁራው በሰማይ በሮ የሚበላ ነገር ጣለለት፡፡ ኤልያስ የተወረወረለትን ምግብ አነሳ፡፡
- ሃሌ ሉያ! ብሎ እግዚአብሔርን አመሰገነ፡፡ ቁራው ይህንን ማድረጉ የሚገርም ነገር ነው፡፡
- አጋጣሚ ይሆን? ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም በድጋሚ ራሱ ቁራው ሊበላው የሚወደው ምግብ ነበር የወረወረው፡፡
- ኤልያስ በየጊዜው ከሰማይ ምግብ ሲያገኝ እግዚአብሔር "ቁራው እንዲመግብህ አደርጋለሁ" ብሎ ቃል የገባለትን አስተዋለ፡፡
- በሚቀጥለውም ቀን ተመሳሳይ ነገር ተከሰተ፡፡
- ጥዋትና ማታ ቁራዎቹ እንጀራና ሥጋ እያመጡለት ውሃውንም ከምንጩ ይጠጣ ነበር፡፡
- ይህም ግሩም ነገር በየቀኑ ቀጠለ ኤልያስም በእግዚአብሔር ደግነትና ጥበቃ ተደነቀ፡፡

**ጥያቄ** እግዚአብሔር ለምን ዝናብ እንዳይዘንብ አደረገ?

## ማጠቃለያ

- እንደ _______________ ኤልያስ ከንጉሡ ፊት ቀርቦ ጥፋቱን ነግሮት ማስጠንቀቁ ጉብዝናውን ያሳያል፡፡

  ሀ. ቅዱስ ማርቆስ    ለ. መጥምቁ ዮሐንስ    ሐ. ቅዱስ ሉቃስ
- ቁራው ኤልያስን ለመመገብ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እንደፈጸመ እንዲሁም _______________ ዮናስን በመዋጥና በመትፋት የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ፈጽሟል፡፡

## ተግባር

- የኤልያስና የቁራው ሥዕል አዘጋጅተው በቀለም እንዲቀቡ ያድርጉአቸው ፡፡
- ከተቻለ ልጆች በክፍል ውስጥ የቁራ ምስል በወረቀት የሚሠሩበት ቁሳቁስ ያቅርቡላቸው፡፡



በእግዚአብሔር የታዘዘው ቁራና ኤልያስ

## 46 ኛ ሳምንት
## ዳዊትና ጎልያድ

ዓላማ

- የበኩላችንን ጥረት ካደረግን እግዚአብሔር ከጐናችን እንደሚሆን መማር።

ጥቅስ

- "በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሀለሁ።" መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 17፥45።

ምንባብ

- መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ምዕራፍ 17 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ።

መግቢያ

- ያለፈውን ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- በጣም ጠንካራ ከሆኑ ሰዎች ማንን ታውቃላችሁ?
- ጠንካራ ወይም ኃይለኛ የሆኑት ለምንድን ነው?
- ኃይለኛና ጠንካራ ሰው ብታገኙ ምን ታደርጋላችሁ?
- የዛሬው ታሪክ ስለ አንድ ትልቅና ኃይለኛ ሰው ሲሆን ወጣቱ ዳዊት እንዴት እንዳሸነፈው እንማራለን።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑት እስራኤላውያን ከፍልስጤማውያን ጋር የማያቋርጥ ጦርነት ያደርጉ ነበር።
- ከፍልስጥኤም ተዋጊዎች መሐል አንደኛው በጣም ገገር የነበረ ሰው ነበር።
- በጮኸ ጊዜ በእስራኤላውያን ዘንድ ፍርሐት ይሰፍን ነበር።
- ሁለቱ ወገኖች በአንድ ተራራ ግራና ቀኝ በሸለቆ ተለይተው ተሰልፈው ነበር።
- በጊዜው የነበረው የእስራኤል ንጉሥ ሳኦል ይባል ነበር።
- ለረጅም ጊዜም ከፍልስጥኤማውያን ጋር ተዋጋ።
- ጎልያድ እስራኤልን የሚጠላ ግዙፍ ተዋጊ ነበር። እርሱን የሚቋቋም ማንም አልነበረም።
- ጎልያድ በደንብ የሠለጠነና የታጠቀ ተዋጊ ነው። ማንም ደፍሮ በፊቱ አይቆምም ነበር።
- የእሴይ ልጅ ዳዊት ከእሴይ ልጆች ሁሉ በጣም ትንሹ ነበር። ሌሎቹ የእሴይ ልጆች ጦር ሜዳ ሄደው ነበር።
- ዳዊት በጐች የሚጠብቅ እረኛ ነበር።
- በጐችን ማገድ በደንብ ያውቅበታል፤ ወደ ውሃ መጠጫ ይወስዳቸዋል። ከመስኩ ሣር እንዲግጡ ያደርጋል፤ከዚያም ወደ በረታቸው ይመልሳቸዋል።
- በጐችን ሊያጠቁ ከመጡ አንበሳና ድብ ጋር ተደባድቦ በጐችን አስጥሏል።
- ዳዊት የአንበሳ ልብ ቢኖረውም ምንም ዓይነት የጦር ሜዳ ልምድ የለውም።
- በጐልያድ የተነሳ በእስራኤላውያን ላይ ስለ ሚደርሰው ውርደት ብዙ ወሬ ይወራ ነበር።
- ዳዊት በወገኖቹ ላይ የሚደርሰው ውርደት እንዲቆም ይፈልግ ነበር።
- የዳዊት አባት እሴይ ጦር ሜዳ ላሉት ልጆቹ ስንቅ መላክ ፈልጎ ዳዊትን ላከው።
- ዳዊትም የጦር ሜዳን ሁኔታ ለማየት አጋጣሚ ተፈጠረለት።
- ወደ ጦር ሜዳውም ሄዶ ለወንድሞቹ ስንቁን አደረሰ።
- በፍልስጥኤማውያን ሰፈር ግዙፉን ጐልያድን አየው።
- ጎልያድ ያጠለቀው የብረት ቆብ (ኮፍያ) የያዘው ጦርና ጋሻ ግዙፍ ከመሆኑ የተነሳ ማንኛውም ሰው በቀላሉ ሊይዘውና ሊያሸንፈው አይችልም ነበር።
- ጉልያድ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በመድፈሩ ዳዊት በጣም ተናደደ።

- ዳዊት በንጉሥ ሳኦል ፊት ቀርቦ ጐልያድን ሊወጋ እንደሚፈልግ ገለጸ "ከአንበሳና ከድብ መንጋጋ ያዳነኝ እግዚአብሔር ከፍልስጥኤማውያንም እጅ ያድነኛል" አለው፡፡
- ንጉሥ ሳኦልም በዳዊት ጀግንነት ስለ ተማመነ የአንበሳ ልብ ያለህና በእግዚአብሔርም ጥንካሬ ያገኘህ ነህ አለው፡፡
- ዳዊት የራሱን ልብስ ለብሶ እንዴ ወደ ወንዝ ወረደና አምስት ድንጋዮችን ለቅሞ ከቦርሳው ጨመራቸው፡፡
- ዳዊትም ወደ ጐልያድ ሲጠጋ ጐልያድ ድፍረት መስሎ ተሰማው፡፡
- ግዙፍ ከሆነው ጐልያድ ፊት አንድ ትንሽ ዱላ የያዘ ወጣቱ ዳዊት በድፍረት ሲቆም "ይሄ ምን ማለት ነው?" እኔ ውሻ ነኝን? አለ ጐልያድ፡፡
- ዳዊትንም በል ወደኔ ቅረብ ሥጋህን የሰማይ አሞራዎች የምድር አውሬዎች መጫወቻ ነው የማደርገው ብሎ ዛተበት፡፡
- ዳዊትም ለጎልያድ ምንም አልመለሰለትም፤ለዛቻውም ቦታ አልሰጠውም፡፡
- ዳዊት በመቀጠል በድፍረትም "አንተ ጋሻ (መመከቻ) ይዘህ መጥተሃል፡፡ እኔ ግን በእግዚአብሔርና በተዳፈርከው የእግዚአብሔር ሠራዊት ስም ነው የመጣሁት፡፡ ዛሬ እግዚአብሔር በእጄ ይጥልሃል፡፡ ምድር ሁሉ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር መኖሩንም ይረዳል፡፡ እግዚአብሔርም የሚያድነው በጦርና በጐራዴ አይደለም፤ የእግዚአብሔር ውጊያ ስለሆነ በእጃችን ትወድቃለህ፡፡ " አለው፡፡
- ዳዊትም ምን ሳይፈራ በድፍረት ተጠጋውና አንደኛውን ድንጋይ ከቦርሳው አውጥቶ ወደ እርሱ በመጠጋት ላይ ወደ ነበረው ጐልያድ በሙሉ ኃይሉ ወርውሮ ግንባሩ ላይ መታው፡፡
- በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ተሰብስበው ግዙፉ ጐልያድ ወድቆ ሲዘረር ተመለከቱ፡፡
- ዳዊት ወደ ተጋደመው ፍልስጥኤማዊ ሮጦ በመሄድ የጐልያድን ጐራዴ መዞ አንገቱን መታው፡፡
- በዚሁ ውጊያው አበቃ፡፡ የግዙፉን ተዋጊያቸውን መውደቅ ባዩ ጊዜ ፍልስጥኤማውያን በፍርሃት ተውጠው ሸሹ፡፡
- እግዚአብሔር በወደደውና ባመነው በትንሹ ልጅ አማካኝነት ምን ያህል ታላቅ ነገር ማድረግ ይቻለዋል?

**ጥያቄ**


1. የእሴይ ልጅ ዳዊት የሁሉም ________________ ነበር፡፡ /ታላቅ/ ወይስ /ታናሽ/
2. ዳዊት ጐልያድን የገጠመው በጐራዴ ወይስ በድንጋይ ነው? በድንጋይ/
3. ዳዊት ጐልያድን ከመግጠሙ በፊት ከምን ዓይነት እንስሳት ጋር ነበር የታገለው? /አንበሳ ና ድብ/
4. ንጉሥ ሳኦል የዳዊት ጀግንነት እንዴት ነው የገለጸው? /የአንበሳ ልብ/

**ማጠቃለያ**

- በኢየሱስ ክርስቶስ ማንኛውንም ነገር ማድረግ እንችላለን፡፡
- ሙሉ እምነታችን በእግዚአብሔር ላይ ከሆነ እርሱ ለእኛ ይዋጋልናል፡፡
- ጥንካሬ ሲኖረን ከእግዚአብሔር ያገኘነው ነው፤ ደካማ ሆነን ሲሰማን ደግሞ ከመከራ እንዲጠብቀን በእግዚአብሔር እንተማመናለን እንበል፡፡

**ተግባር**

- የዳዊትና የጐልያድን ሥዕል ልጆቹ በከለር ይቀቡ፡፡
- ከተገኘ ለትምህርቱ ተስማሚ የሆነ ሥዕል ይዘው ወደ ቤታቸው ይሂዱ፡፡
- የዚህን ታሪክ የቪድዮ ፊልም ለልጆች ያሳዩአቸው፡፡



ዳዊትና ጎልያድ

## 47 ኛ ሳምንት
## ዳንኤልና የአንበሳው ጉድጓድ

ዓላማ

❖ እግዚአብሔር ልጆቹን ምንግዜም ይጠብቃል፡፡

ጥቅስ

❖ "አምላኬ መልአኩን ልኮ የአንበሶቹን አፍ ዘጋ፡፡" ትንቢተ ዳንኤል 6፥22፡፡

ምንባብ

❖ ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 6 ከቁጥር 16 እስከ 23፡፡

መግቢያ

❖ ያለፈውን ትምህርትና ጥቅስ መከለስ፡፡
❖ ልጆቹን ስድስት ኪሎ አንበሳ ግቢ ሄደው ያውቁ እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡
❖ ምን ዓይነት የዱር እንስሳ አይተው እንደሚያውቁ ይጠይቋቸው?
❖ አስፈሪ የሆኑና ትላልቅ ጥርስ ያላቸው እንስሳት እነማን ናቸው?
❖ አንበሶቹ የተዘጋባቸው ለምንድር ነው? ለምን አልተለቀቁም?

የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ

❖ በንጉሥ ብልጣሶር አዳራሽ የተሰበሰበው ሰው ሁሉ እየሳቀ እየጠጣና እየተጫወተ ነበር፡፡
❖ በድንገት ከሰማይ በመጣ እሳት የእግዚአብሔር ጣት በግርግዳው ላይ ጽሑፍ ጻፈ፡፡
❖ በአዳራሹ የነበሩ ሁሉ ተደናገጡ፤ግራ ተጋቡ፡፡
❖ አንዳቸውም የጽሑፉን ፍቺ ሊረዱ አልቻሉም፡፡ ነገር ግን ፍቺውን የሚያውቅ አንድ ሰው በቻ ነበር፡፡
❖ ዳንኤል እግዚአብሔር ለሕዝቡ የጻፈውን መልዕክት ፍቺ መረዳት ይችል ነበር፡፡
❖ ንጉሥ ብልጣሶርም ዳንኤልን ግርግዳው ላይ ያለውን ፍቺ እንዲፈታለት ላከው፡፡
❖ ብልጣሶርም በዳንኤልም ተደስቶ ከሶስቱ ገገርዎች መሐል አንዱ አደረገው፡፡

**ጥያቄ**

1. የንጉሡ ስም ማነው፡፡
2. የጽሁፉን ፍቺ ያወቀው ሰው ማነው?

❖ በዚያው ምሽት ንጉሥ ብልጣሶር በውጊያ ላይ ተገደለ፡፡
❖ ንጉሥ ዳርዮስም ነገሠ፡፡
❖ ንጉሥ ዳርዮስም ከሌሎቹ ገገርዎች ይልቅ ዳንኤልን ስለወደደው ሌሎቹ ገገርዎች ቀኑ፡፡
❖ ሁለቱ ገገርዎች በዳንኤል ላይ አሴሩበት፡፡ ዳንኤል እግዚአብሔርን የሚወድና የሚያመልክ መሆኑን ስለሚያውቁ ሁሉም ሰው ለሰላሳ ቀናት ንጉሡን ብቻ እንዲያመልክ ሕግ እንዲወጣ ያደርግ ዘንድ አሣመኑት፡፡
❖ ይህንንም ያልፈጸመ በአንበሣ ጉድጓድ ውስጥ እንዲጣልና እንዲገደል ይደረግ የሚል ሕግ ወጣ፡፡
❖ ሁለቱ ገገርዎች በዳንኤል ቤት ሲያልፉ ዳንኤል ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አዩት፡፡
❖ ወደ ንጉሡም በፍጥነት ሄደው ያዩትን ነገሩት፡፡
❖ ንጉሡ ዳንኤልን በጣም ይወደው ስለነበር በዚህ ወሬ በጣም ተረበሸ፡፡
❖ ሁለቱ ገገርዎችም ዳንኤል የወጣውን ሕግ መተላለፉን አስረግጠው አስረዱት፡፡
❖ ንጉሥ ዳርዮስም እያመነታ ዳንኤል ወደ አንበሳው ጉድጓድ እንዲጨመር አደረገ፡፡
❖ ዳንኤል ወደ ጉድጓዱ ከመግባቱ በፊት ንጉሥ ዳርዮስ "ሁልጊዜ የምታመልከው አምላክ እርሱ ያድንህ፡፡" ካለው በኋላ ዳንኤል ጉድጓዱ ተዘጋበት፡፡

ጥያቄ

1. አዲሱ ንጉሥ ማን ይባላል?
2. ዳንኤልን ይወደው ነበር ወይ?
3. አዲሱን ንጉሥ ለማሳሳት ሁለቱ ገገርዎች ምን አደረጉ?

- ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመልሶ ንጉሥ ዳርዮስ ለኀደኛው ለዳንኤል ሌሊቱን መሉ ፆመ።
- በዚያም ምሽት ምንም ዓይነት ዘፈን አልዘፈነም። ስለ ዳንኤል በመጨነቁ እንቅልፍ አልወሰደውም።
- በማግስቱም በጥዋት ዳንኤልን ለማየት ወደ አንበሳው ጉድጓድ ሄደ።
- ንጉሡም ጉድጓዱ ጋር በደረሰ ጊዜ ዳንኤልን ተጣርቶ "ሁልጊዜ የምታመልከው አምላክ አድኖሀልን?" አለው።
- ዳንኤልም ወድያውኑ "አምላኬ መልአኩን ልኮ የአንበሶቹን አፍ ዘጋ እነርሱም አልጉዱኝም።" በማለት መለሰለት።
- ንጉሡም በጣም ደስ አለው ዳንኤልንም ከአንበሶቹ ጉድጓድ እንዲያወጡት አዘዘ።
- ዳንኤልም ከጉድጓድ ወጣ፣ በአምላኩም ታምኖ ነበርና አንዳች ጉዳት አልደረሰበትም ነበር። ዳንኤል 6፥23

ጥያቄ

1. ንጉሡ ስለ ዳንኤል ተጨንቆ ነበር ወይ?
2. ዳንኤል ጉድጓድ ውስጥ በቆየበት ሌሊት ንጉሡ ምን አደረገ?
3. በማግስቱ ንጉሡ በጉድጓዱ ውስጥ ምን አገኘ?

ማጠቃለያ

- በእግዚአብሔር እስከ አመንን ድረስ እርሱ ይጠብቀናል።
- "አንተ ከኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም።" የዳዊት መዝሙር 23፥4።

ተግባር

- ልጆቹ የዳንኤልን ሥዕል በከለር ይቀቡ።
- ልጆቹ ወደ አንበሳ ግቢ ውሰዱአቸውና አንበሶችን ይዩ።



ነቢዩ ዳንኤል ወደ አንበሶች ጉድጓድ እንደ ተጣለ

## 48 ኛ ሳምንት
## ኤልያስና ባልቴትዋ

**ዓላማ**

- እግዚአብሔር ልክ እንደ ወላጆቻችን የሚጠብቀን መሆኑን መማር።

**ጥቅስ**

- "እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳል።" 2ኛ ቆሮንቶስ 9፥7።

**ምንባብ**

- መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ምዕራፍ 17 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ።

**መግቢያ**

- የበረከቶቻችን ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር ነው።
- ከእግዚአብሔር በጎ ነገር እንድናገኝ ወይም እንዲሰጠን እኛ እራሳችንን መስጠት መቻል አለብን።
- እግዚአብሔር አምላካችን በጣም ደግ ነው። የሰጠነውን አብዝቶ ይመልስልናል።

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- ኤልያስ ሁለተኛውን ትዕዛዝ ከእግዚአብሔር ተቀበለ።
- ለንጉሥ አክአብ ዝናብ መዝነቡን እንደሚያቆም አስጠነቀቀው።
- ምክንያቱም ንጉሡ በአል የሚባል ጣኦት ያመልክ ስለ ነበር ነው።
- የምግብ እጥረት እየተባባሰ መጣ። ሕዝቡ ተራበ። የሚበላም እንጀራ ጠፋ።
- በዚህ ክፉ ጊዜ እግዚአብሔር ኤልያስን ወደ አንዲት ባልቴት ላከው።
- እግዚአብሔርም አለው "ተነሥተህ በሲዶና አጠገብ ወዳለችው ወደ ሰራፕታ ሂድ በዚያም ተቀመጥ።" (መጽሐፈ ነገስት ቀዳማዊ 17፥9)
- ወደ ከተማይቱ በር በደረሰ ጊዜ አንዲት ሴት አገኘ። ውኃም እንድትሰጠው ጠየቃት።
- ሴትየዋ ባልዋ ሞቶባት ከአንድ ወንድ ልጅዋ ጋር ትኖራለች።
- የእግዚአብሔር ሰው የሆነው የኤልያስን ጥያቄ ተቀብላ ውኃ ሰጠችው።
- ሴትየዋም የመጨረሻዋን እራት ለማዘጋጀት እንጨት እየለቀመች ነበር።
- የእራት ሰዓት ስለ ደረሰ ኤልያስ እንጀራ እንድታቀርብለት ጠየቃት።
- ሴትየዋም አለችው "አምላክህ ሕያው እግዚአብሔርን! በማድጋ ካለው ከእፍኝ ዱቄት፣ በማሰሮም ካለው ከጥቂት ዘይት በቀር እንጀራ የለኝም። እነሆም ገብቼ ለእኔና ለልጄ እጋግረው ዘንድ በልተነውም እንሞት ዘንድ ጥቂት እንጨት እሰበስባለሁ።" አለችው።
- ኤልያስም "አትፍሪ ይልቅስ ሄደሽ እንዳልሽው አድርጊ አስቀድመሽ ግን ከዱቄቱ ለእኔ ታናሽ እንጐቻ አድርገሽ አምጪልኝ ከዚያም በኋላ ለአንቺና ለልጅሽ አድርጊ።" አላት።
- በዚህች ሴት ቤት በቂ ምግብ የለም። የቀራቸውም ለመጨረሻ ጊዜ ከልጇ ጋር ልትበላ ያሰበችው ብቻ ነበር።
- ቢሆንም ኤልያስም በመጀመሪያ ለርሱ እንድታቀርብለት ጠየቃት።
- ይህች ሴት ከዚህች ዓለም ላይ የቀራት እፍኝ ዱቄትና ጥቂት ዘይት ብቻ ነው።
- ይህች ጥሩ ሴት ከባድ ፈተና ውስጥ ገባች።
- ያለው በጣም ጥቂት ምግብ ቢሆንም የእግዚአብሔር ሰው የሆነው ኤልያስ በመጀመሪያ ለእርሱ እንድታዘጋጅለት ጠየቃት።
- ከሱ የሚተርፈው ደግሞ ለሷና ለልጅዋ አይበቃም። "ነገስ ምን እበላለሁ?" ብላ ተጨነቀች።
- ነገር ግን ለራሴ ብቻ አላስብም ኤልያስ እንዳዘዘኝ አደርጋለሁ ብላ በመጀመሪያ ለርሱ አዘጋጀች።

- ❖ በእግዚአብሐር ያላት እምነት አሸነፈ:: ለኤልያስ እንጀራውን ጋግራ ሰጠችው::
- ❖ ይህች ምስኪን ሴት የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ተማምና ለኤልያስ አስቀድማ እንጀራ በመጋገርዋ እግዚአብሔር በብዙ መንገድ እንደሚባርካት ኤልያስ እርግጠኛ ሆነ::
- ❖ መበለትዋ እግዚአብሔርን አምናለች:: በቀራት ጥቂት ዱቄት እንጀራ ጋገረች::
- ❖ በቀን አንድ ጊዜ ብቻ ይበሉ ስለነበረ ልጅዋ ሊበላ ወደ ቤት መጣ::
- ❖ ነገር ግን የተጋገረው እንጀራ ለነርሱ አለመሆኑን ሲረዳ ተገረመ:: እንጀራውም ተጋግሮ ለመቅረብ ተዘጋጅቷል::
- ❖ በድንገት ልጁ ደስ ብሎት እንዲህ አለ:: "እማዬ ተመልከቺ ለኛ ምግብ የሌለ መስሎኝ ነበር አሁን ግን ይኸው ሞልቷል::" አለ::
- ❖ አይደለም ልጄ የቀረውን ሁሉ ተጠቅሜበታለሁ አለችው::
- ❖ ልጁ ግን ይኸው አዲስ ዱቄት አለ አላት::
- ❖ መበለቲቱ ወደ ማድጋው ተመለከተችና ማመን አቃታት:: ማድጋው በዱቄት ማሰሮውም በዘይት ተሞልቷል::
- ❖ ልባቸው በሐሴት ተሞላ:: እንጀራ እስኪቀርብለት ድረስ የሚጠባበቀውን ኤልያስን ተመለከቱት::
- ❖ ኤልያስ የቀረበለትን እንጀራ ተመገበ:: መበለቲቱና ልጇም ደስ አላቸው እራታቸውንም በሉ::
- ❖ መበለቲቱ ኤልያስ ያላትን አምና ፈጸመች የእግዚአብሔርንም የተስፋ ቃል አመነች::
- ❖ በቀጣዮቹ ቀናቶች በሙሉ የዱቄት ማድጋውና የዘይት ማሰሮው ሙሉ ሆነው ቆዩ::
- ❖ እግዚአብሔር መበለቲቱን ረዳት::
- ❖ እግዚአብሔር በርሱ የሚታመኑትን ሁሉ ይረዳቸዋል:: በረከቱም ለሁሉም ይደርሳል::
- ❖ እግዚአብሔር አምስት ሺዎቹንና ሰባት ሺዎቹን በአምስት ዳቦና በሁለት ዓሣ መግቦ ነበር::
- ❖ እግዚአብሔር ትንሹን ድካማችንን ባርኮ ወደ ሰማያዊ ጸጋ ሊያደርሰን ፈቃዱ ስለሆነ በእግዚአብሔር ታመኑ::
- ❖ ለምንሰጠው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር በምድርና በሰማይ ይከፍለናል::
- ❖ መስጠት ብዙ ጥቅም አለው:: ሌሎችን ስለ ምናስደስትበት ብዙ በረከት እናገኝበታለን::
- ❖ በመስጠታችን የተነሳ እራሳችንን ከቁሳዊ ነገር ጋር ከማስተሳሰር እንለያለን::
- ❖ ለምሳሌ ለጓደኝነትን ከገንዘብና ከመጫወቻችን የበለጠ ቦታ መስጠት ማለት ነው::

**ጥያቄ**

1. ኤልያስ መበለቲቱን መጀመሪያ ሲያገኛት______________ጠየቃት:: /ውኃ/
2. መበለቲቱ በመጀመሪያ ለኤልያስ እንጀራ ለምን ጋገረች? /የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ስለ ተማመነች::/
3. መበለቲቱ ኤልያስን በመጀመሪያ በመመገቧ ምን ዓይነት በረከት አገኘች::/የማያልቅ ዱቄትና ዘይት/
4. መበለቲቱ ኤልያስን ለመቀበልና ለመመገብ ፈቃደኛ ሳትሆን ቀርታ ከልጇ ጋር የመጨረሻውን ምግብ በልታ ቢሆን ኖሮ ምን ይገጥማት ነበር?

**ማጠቃለያ**

- ❖ መበለቲቱ ለራስዋና ለልጅዋ የማይበቃ የቀራት ትንሽ ምግብ ነበር:: እግዚአብሔርን ስለ ተማመነች ለኤልያስ አስቀድማ እራት አዘጋጀችለት:: በዚህም የተነሳ በረከት አገኘች::
- ❖ የቤተክርስትያን አባቶች ሲጎበኙን ደስ ይለናል ወይ? ጉብኝታቸውን በጉጉት እንጠብቃለን ወይ? የእግዚአብሔርን ትዕዛዙን ለመከተል እንፈልጋለን ወይ?

**ተግባር**

- ❖ እናንተም ስታጠኑም ሆነ ፈተና ስትፈተኑ በእግዚአብሔር ተማመኑ::



ነቢዩ ኤልያስና ባልቴቲቱ

## 49 ኛ ሳምንት

## የአሮን በትር

ዓላማ

- እግዚአብሔር ሕዝቦቹን የሚጠብቅ መሆኑን መማር።

ጥቅስ

- "የመረጥሁት ሰው በትር ታቆጠቍጣለች።" ኦሪት ዘኍልቍ 17፥5።

ምንባብ

- ኦሪት ዘኍልቍ ምዕራፍ 17 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ።

መግቢያ

- ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ መከለስ።
- ዕፅዋት እንዴት እንደ ሚያድጉ ሕፃናትን ይጠይቋቸው።
- ዕፅዋት ዕድገታቸው በአግባቡ ተጠብቆ እንዲቆዩ ምን ልናደርግላቸው ያስፈልገናል?
- ዕፅዋት ያለ ውኃ ማደግ ይችሉ እንደ ሆነ ይጠይቋቸው።

የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ

- በበረሃ ለረጅም ዓመታት ቆይተዋልና ሙሴን ይከተሉ የነበሩት የእስራኤል ሕዝቦች በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ አጕረመረሙ።
- እግዚአብሔር የሚሠራውን ሥራ የሚያውቅ ቢሆንም ሕዝቡ ግን በርሱ ላይ የነበራቸው እምነት ቀዘቀዘ፤ በትዕግስትም መጠበቅ አቃታቸው።
- እግዚአብሔር ሕዝቡ ሳይናደዱ ወይም ሳይበሳጩ ሊንከባከባቸው ስለ ፈለገ ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው ጥበቃ የሚያደርግላቸውና የሚጸልይላቸው ሰው አዘጋጀላቸው።
- እግዚአብሔር ለሚወዳቸው ሕዝቡ ያለውን ዕቅድ ገለጸላቸው።

**ጥያቄ**

1. በበረሃ ይኖሩ የነበሩት ሕዝቦች እነማን ናቸው?
2. ሕዝቡ ያጕረመረሙት ወይም የተናደዱበት በምንድር ነበር?

- ሙሴም እግዚአብሔር ያዘዘውን ዕቅድ ሁሉ ይከተል ነበር።
- በመጀመሪያ ሙሴ ከእያንዳንዱ ነገድ ሽማግሌዎች ቤት አንድ አንድ በአጠቃላይም አሥራ ሁለት በትር ሰበሰበ።
- በመቀጠል እያንዳንዱ በትር የማን እንደ ሆነ ይታወቅ ዘንድ ስማቸውን በየበትራቸው ላይ ጻፈ።
- አሥራ ሁለቱንም በትር ወስዶ በመገናኛው ድንኳን አስቀመጣቸው።
- እግዚአብሔርም ሙሴን አነጋገረው። ከአሥራ ሁለቱ በትሩ ያቆጠቆጠችለት ሰው ካህን ሆኖ ሕዝቡን እንዲያገለግል የመረጠው መሆኑን ገለጸለት።
- ሙሴም ሳይተክላትና ውኃ ሳያጠጣት እግዚአብሔር ይንከባከባት ዘንድ ሌሊቱን ሁሉ ያችን በትር በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በማኖር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጸመ።

**ጥያቄ**

1. የእግዚአብሔር ዕቅድ ምን ነበር?
2. ሙሴ ስለመለሙችው በትር ያደረገው ምንድር ነው?

- በማለዳም ሙሴ በትርዋ የሆነችውን ያይ ዘንድ ወደ መገናኛው ድንኳን ሄደ።
- የአሮን በትርም ውኃ ሳያጠጡአትና ሳይኰተኵቱአት አበባ አውጥታ ለውዝም አፍርታ ተገኘች።

- ሙሴና የእስራኤልም ሕዝቦች ወዲያው አሮን ካህን ሆኖ ያገለግል ዘንድ እግዚአብሔር የመረጠው መሆኑን ተረዱ።

**ጥያቄ**

1. ሙሴ ወደ መገናኛው ድንኳን ሲሄድ ያየው ምን ነበር?
2. ያቆጠቆጠችውና የለመለመችው የማን በትር ነበረች?

**ማጠቃለያ**

- እግዚአብሔር ዘወትር ለሕዝቦቹ ዕቅድ ይኖረዋል እንጂ ችል ብሎ አይተዋቸውም።

**ተግባር**

- ሕፃናት ፍሬዎች አምጥተው እንዲተክሉና ውኃ እያጠጡ በየሳምንቱ የሚኖረውን ለውጥ እንዲመለከቱ ያድርጉአቸው።
- ለሕፃናት አንዳንድ ንጹሕ ወረቀት በመስጠት የበትር ሥዕል ስለው ስማቸውን እንዲጽፉበት ያድርጉአቸው፤ በሚቀጥለውም ሳምንት ስቲከር እንዲለጥፉበት ወይም አንድ ነገር እንዲያንጠለጥሉበት ያድርጉአቸው።



የለመለመችው የአሮን በትር

## 50 ኛ ሳምንት

## በለዓምና አህያው

**ዓላማ**

- የበለዓምንና የአህያውን ታሪክ መማር፡፡
- እግዚአብሔር ከወደደ እንስሳትን እንዲናገሩ ሊያደርጋቸው የሚችል መሆኑን መረዳት፡፡

**ጥቅስ**

- "እግዚአብሔርም የአህያይቱን አፍ ከፈተ፡፡" ኦሪት ዘኁልቁ 22፥28፡፡

**ምንባብ**

- ኦሪት ዘኁልቁ ምዕራፍ 22 እና 23 ከቁጥር 1 እስከ ፍጻሜ፡፡

**መግቢያ**

- ያለፈውን ትምህርትና ጥቅስ መከለስ፡፡
- በትምህርቱ ክፍለ ጊዜ የሚጠቀሙባቸውን የበለዓምንና የአህያይቱን ሥዕል ያዘጋጁ፡፡
- ሕፃናትን አህያ ምን እንደ ምትመስል፣ የአህያም ድምፅ ምን ዓይነት እንደ ሆነ ይገልጹ ዘንድ ይጠይቁቸው፡፡

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**

- በአንድ ወቅት የእግዚአብሔርን ሕዝቦች የማይወድድ ባላቅ የሚባል ንጉሥ ነበር፡፡
- ባላቅም በለዓም የሚባለውን ነቢይ እንዲጠሩለት አደረገ፡፡

**ጥያቄ**

1. የንጉሡ ስም ማን ነበር?
2. የነቢዩ ስም ማን ነበር?
3. ነቢይ ማለት ምን ማለት ነው?

- ነቢይ ማለት እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሊናገር የፈለገውን የሚገልጽ ማለት ነው፡፡
- ንጉሡ ባላቅ በለዓምን ጠርቶ የእስራኤል ሕዝቦች ደካማ እንዲሆኑልኝና ከዚህም ምድር አውጥቼ እንዳሳድዳቸው ርገምልኝ አለው፡፡
- በለዓምም የእስራኤልን ሕዝቦች ለመርገም በአህያው ተቀምጦ መንገድ ሲጀምር የሚያንጸባርቅ ልብስ የለበሰ የእግዚአብሔር መልአክ በአህያይቱ ፊት ቆመ፡፡
- አህያይቱም ሂ፣ ሂ፣ ሂ፣ ሃ ... እያለች አንድ እርምጃ መራመድ እንኳን አቃታት፡፡
- በለዓምም አህያይቱ ምን ሆነች ብሎ ተገረመ፣ የማትሄደው ለምንድር ነው? ብሎም ዱላ አውጥቶ በዱላ መታት፡፡
- ቢሆንም አህያይቱ ሂሃ...፣ ሂሃ...፣ ሂሃ... እያለች ባለችበት ቆመች መሄድም አልቻለችም፡፡
- ዳግመኛ አህያይቱ እንድትሄድ በለዓም በዱላ ቢነርታትም አህያይቱ ግን ሂሃ...፣ ሂሃ...፣ ሂሃ... አለች፡፡
- በለዓም አህያይቱ አልሄድም ብላለችና በጣም ተናደደ፡፡
- እንዳትሄድ ያደረጋትን በፊቱ የቆመውን መልአክ አህያይቱ እንጂ በለዓም አላየም ነበር፡፡
- በለዓም በጣም ስለ ተናደደ በጣም አብዝቶ አህያይቱን በዱላ ደበደባት፡፡
- እግዚአብሔርም የአህያይቱን አፍ ከፈተና "በየጊዜው የምትቀመጥብኝ አህያህ አይደለሁምን? በውኑ እንዲ አስቸግሬህ አውቃለሁን? አደርግ ዘንድ የምታዝዘኝን ሳላደርግልህ ቀርቼ አውቃለሁን?" አለችው፡፡
- በለዓምም በአህያይቱ ፊት የቆመውን የእግዚአብሔር መልአክ ማየት ቻለ፡፡
- አህያይቱን ሦስት ጊዜ መቷቷልና የእግዚአብሔር መልአክ በለዓምን ተቆጣው፡፡
- በሎዓምም ጥፋት ሠርቷልና ይቅርታን ጠየቀ፡፡

**ማጠቃለያ**

- እግዚአብሔር አህያን እንድትናገር ማድረግ ይችላል። ሰው መሥራት የማይችለውን ማንኛውንም ነገር እግዚአብሔር መሥራት ማድረግ ይችላል።
- በለዓም አህያይቱን ያለ አግባባ ስለ ደበደባት የእግዚአብሔር መልአክ ተቆጥቶታል፤ ስለዚህ እኛም ለእንስሳት የምናዝንና የምንከባከባቸው መሆን ያስፈልገናል።

**ተግባር**

- ለሕፃናት የመላእክትን ሥዕል አዘጋጅተው በቀለም እንዲቀቡ ያድርጉአቸው።
- ድመት ወይም ትንሽ ውሻ አምጥተው እንዴት ሊንከባከቡአቸው እንደሚገባ ያስረዱአቸው ለድመቷ ወይም ለውሻዋም ምግብና መጠጥ እንዲሰጡአቸው ያድርጉአቸው።



የእግዚአብሔር መልአክ በለአምን በመንገድ እንዳቆመው

ወስብሐት ለእግዚአብሔር::

## ዋቢ መጻሕፍት


* ሃብተማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)፣ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት፣ 1963 ዓ.ም
* ሃይማኖተ አበው፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1986 ዓ.ም.
* አባ መልከ ጼዴቅ (ሊቀ ጳጳስ)፣ ትምህርተ ክርስትና፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም፡፡
* አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1974 ዓ.ም፡፡
* ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓት አምልኮና የውጭ ግኝኙነት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም.
* ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትና ዛሬ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1990 ዓ.ም.
* ሉሌ መልአኩ (መምህር)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1997 ዓ.ም፡፡
* መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት)፣ መጽሐፈ ሐዲሳት ሠለስቱ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1989 ዓ.ም፡፡
* መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
* መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም፡፡
* መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
* መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም
* ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1988 ዓ.ም
* ዳኛቸው ካሳሁን (መልአከ ሰላም)፣ ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር፣ አዲስ አበባ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 2003 ዓ.ም.
* ደረጀ ጅማ (መጋቤ አእላፍ)፣ ምን ያስጨንቃችኋል ክፍል ፪፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2002 ዓ.ም፡፡
* መጽሐፍ ቅዱስ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም
* ሐረገ ወይን ቸርነት፣ ሴትና አህያ፣ አዲስ አበባ፣ 2005 ዓ.ም፡፡
* ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ዶ/ር)፣ ጠቅላላ የቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም.
* ጎሩይ ኤርምያስ (መምህር)፣ መዝገበ ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም
* የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ 1996 ዓ.ም፡፡
* ቸርነት አበበ (መምህሩ)፣ የመጽሐፍ ቅድስ ጥናት፣ አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም
* H.G. Bishop Moussa@ The Characteristics of Orthodox Teaching@ Bishopric of Youth@ Harmony Press, 2007.
* H.G. Gishop Mouusa, An Introduction to the New Testament, Bishopric of youth, Dar EL Geel Press, 2001.
* H.G. Bishop Raphail, The Meaning of Miracles, Bishopirc of Youth, 2010.
* Sunday School Curriculum, Grade 1 to Grade 12. The Coptic Orthodox Diocese of The Southern USA.
* Sunday School Lessons, Class 1 to Class 10, E.O.T.C Latin America Diocese.

* ኅሩይ ኤርምያስ (መምህር)፣ መዝገበ ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም
* የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ 1996 ዓ.ም።
* ቸርነት አበበ (መምህሩ)፣ የመጽሐፍ ቅድስ ጥናት፣ አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም
* H.G. Bishop Moussa@ The Characteristics of Orthodox Teaching@ Bishopric of Youth@ Harmony Press, 2007.
* H.G. Gishop Mouusa, An Introduction to the New Testament, Bishopric of youth, Dar EL Geel Press, 2001.
* H.G. Bishop Raphail, The Meaning of Miracles, Bishopirc of Youth, 2010.
* Sunday School Curriculum, Grade 1 to Grade 12. The Coptic Orthodox Diocese of The Southern USA.
* Sunday School Lessons, Class 1 to Class 10, E.O.T.C Latin America Diocese.



ዋ.ጋ፡-60